# የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ የመምህር ማኑዋል

ሚያዝያ 2008 ዓ.ም.

ትምህርት ሚኒስቴር

አዲስ አበባ

## ማውጫ

1. መግቢያ ... 5
1.1. የማኑዋሉ አጠቃቀም ... 6
2. የኦቲዝም ችግር ምንነትና መንስኤዎች ... 8
2.1. የኦቲዝም ችግር ምንነት ... 8
2.2. የኦቲዝም ችግር መንስኤዎች ... 9
3. የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ልጆች ለይቶ ማወቂያ (Identification and Assessment) ዘዴዎች ... 10
3.1. በልዩ ትምህርት ቤት የሚማሩት ልጆች ... 11
3.1.1. በሁለት ዓመት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች ... 11
3.1.2. ከሁለት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች ... 12
3.2. በመደበኛ ትምህርት ቤት የሚማሩ ልጆች ... 12
3.2.1. ከጉርምስና ዕድሜ ክልል በፊት (pre-teenage years) የሚገኙ ልጆች ... 13
3.2.2. በጉርምስና ዕድሜ ክልል (teenage years) የሚገኙ ልጆች ... 13
4. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ዘዴዎች (Intervention Strategies) ... 15
4.1. መግቢያ ... 15
4.2.1. ተግባቦትና ቋንቋ (communication and language) የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ... 15
4.2.2. የባህሪይና የስሜት ዕድገት ችግሮች (Behavioral and Emotional problems) ... 28
4.2.3. የአዕምሮአዊ ዕድገት (cognitive development) ችግር ... 30
4.2.4. በመማር-ማስተማር ሂደት ወቅት የሚፈጠሩ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው ... 31
4.2.5. ተገቢ ሥነ-ፆታዊና ተያያዥ ጉዳዮች ዕድገት ችግር (problems in sexuality) ... 36
4.2.6. ከሁኔታዎች ጋር በመጣጣም የራስን ህይወት መምራት (Developing Adaptive/Coping Skills) 37
4.2.7. የአካል እንቅስቃሴ ብቃትና የስሜት ህዋሳት አጠቃቀም ክህሎትን ማሳደግ ... 40
5. አካቶ ትምህርት የኦቲዝም ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ... 42
5.1. ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድን (daily lesson plan) መጠቀም ... 42
5.2. የሥርዓተ ትምህርት ይዘትና የትምህርት ተግባራትን ማስማማት ... 43
5.3. የማስተማር ዘዴዎችን ማስማማት (Differentiation of Teaching Stratgies) ... 43
5.4. የተማሪዎች በጋራ የመማማር ዘዴዎችን ማስማማት (Differentiation of Students' Co-operative Learning) ... 44
5.5. በጋራ (team) የማስተማር ዘዴዎችን (collaborative teaching methods) በማስማማት መጠቀም ... 45

5.6. የመማር-ማስተማር አጋዥ (መርጃ) መሣሪያዎችን (teaching aids) ማስማማት ........................ 45
5.7. የክፍል ውስጥ አካባቢን ምቹና ተስማሚ ማድረግ (classroom environment modification) ..... 46
5.8. በመማር ማስተማር ሂደት በጋራ የመሥራት ዘዴዎች (cooperative learning methods) መጠቀም ........................................................................................................................ 48
5.9. የተማሪዎችን የትምህርት ቅስሞሽ ምዘናን ማስማማት ................................................ 49
6. የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሐ ግብር መጠቀም (Individualized Educational Program)......... 51
6.1. የነፍስወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብር እንዴት ታቅዶ ይከናወናል? ................................... 51
6.2. የነፍስወከፍ ትምህርት መርሃ-ግብር ቡድን አባላት የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ............................ 52
6.2.1. ተማሪው/ዋ/ ....................................................................................................... 52
6.2.3. የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር/ተወካይ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ..................................... 53
6.2.4. የክፍል ወይም የትምህርት ዓይነት መምህር የሥራ ድርሻና ኃላፊነት .................................... 53
6.2.5. የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህር /ተዘዋዋሪ መምህር የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ......................... 53
7. የሌሎች ባለሙያዎች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት .......................................................... 55
7.1. የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን ስብሰባ .................................................... 55
7.2. የነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሃ ግብርን ማዘጋጀት ........................................................ 56
7.2.1. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ብቃት (competence) ........................................... 56
7.2.2. በትምህርት ቤት የተማሪውን ሁኔታና የመማር ችግሮች መግለጫ ....................................... 56
7.2.3. የነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሃ ግብር የአጭርና ረጅም ጊዜ ግቦች ...................................... 57
7.3. የነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሃ ግብር ክንውን ዘዴዎች ................................................... 58
7.3.1. የቁሳቁሶች አቅርቦት ............................................................................................ 58
7.3.2. አደረጃጀትና የትምህርት ቅስሞሽ አካባቢን ማስማማት .................................................. 58
7.3.3. በትምህርት ቤት ውስጥና ከትምህርት ቤት ውጭ የሚደረግ ድጋፍ ...................................... 58
7.3.4. ውጤቶችና የትምህርት ቅስሞሽ ምዘና ...................................................................... 59
7.4. የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር አተገባበር (Implementation) .................................. 59
7.5. የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን መመዘን ......................................................... 61
7.6. የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር የምዘና መርሆዎች ................................................. 61
7.7. የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ሰነድን መፈራረም ................................................ 62
8. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ዕቅድና ክንውን፣ ጠቃሚ ምክር/መረጃ (Tips for Teachers of Students with Autism) ............................................................................ 63
9. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ላይ መደረግ ያለባቸውና መደረግ የሌለባቸው ተግባራት (Do's and Don'ts During Teaching of Students with Autism) ........................................... 65

10.የትምህርት ቤት ማኅበረሰብ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ........ 67
10.1.የትምህርት ቤት አመራር ........ 67
10.2.የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የያዘ ቡድን ተግባራት ........ 69
10.3.የመደበኛ ክፍል መምህር ........ 69
10.4.የድጋፍ መስጫ ማዕከል (Resource Centers) ........ 70
10.5.ጋይዳንስ ካውንስለር (ለ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) ........ 70
10.6.ተዘዋዋሪ መምህር ........ 71
ዋቢዎች (References) ........ 73

# 1. መግቢያ

ትምህርት ለሁሉም ዜጎች በዕኩልነት ተደራሽ መሆን ያለበት ሰብዓዊ መብት ከመሆኑም ባሻገር ድህነትን በማጥፋት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሣይንሳዊ ዕድገትን ለማስመዝገብ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ከዚህም ባሻገር ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በሀገሪቱ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል መሣሪያ መሆኑ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በመታመኑ በ1986 ዓ.ም. በተዘጋጀው የሀገራችን የትምህርት እና የሥልጠና ፖሊሲ ንዑስ አንቀፅ 2.2.3. ላይ የአካል ጉዳተኞችና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎችን እንደየችሎታዎቻቸውና ፍላጎቶታቸው ማስተማር አስፈላጊ መሆኑ በግልፅ ሰፍሯል፡፡

ይህን የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መነሻ በማድረግና የምዕተ ዓመቱን የትምህርት ለሁሉም ግቦች ውጤታማ ለማድረግ በ1998 ዓ.ም በሀገሪቱ የመጀመሪያ የሆነው የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስትራቴጂ በትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

በስትራቴጂው ትግበራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን በመቅረፍና የታዩ ክፍተቶችን በመሙላት ከወቅቱ የሀገሪቱ የልማት ፍላጎት አንጻር ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች እንደየችሎታዎቻቸውና ፍላጎቶታቸው የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ለማስቻል አዲስ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ተነድፎ ከሐምሌ 2004 ዓ.ም ጀምሮ በትግበራ ላይ ይገኛል፡፡ በስትራቴጂው ውስጥ ከተካተቱት ዋና ዋና ተግባራት መካከል የመማሪያ- ማስተማሪያ መጻሕፍት ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ማዘጋጀት አንደኛው የትኩረት አቅጣጫ ሲሆን የነፍስ ወከፍ ትምህርት (Individual Educational Program) መርሀ ግብርም በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ይካተታል፡፡

ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የአካል ጉዳተኞችና የመማር ችግር ያለባቸው ተማሪዎች በአካቶ ትምህርት ሥርዓት ውስጥ የመማር ችግሮቻቸውን በማገናዘብ እንደየፍላጎቶቻቸውና ችሎታዎቻቸው የትምህርት እና ስልጠና አቅርቦት እንዲዘጋጅላቸው ትኩረት ቢሰጣቸውም፣ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑትና ከፍተኛ ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች በልዩ ትምህርት ቤቶች ወይም በመደበኛ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ ልዩ ክፍሎች ውስጥ የትምህርት አገልግሎት እንደሚሰጣቸው ስትራቴጂው በተጨማሪ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ዓይነት የትምህርት መርሐ ግብር ሊታቀፉ ከሚገባቸው መካከልም የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ይገኙበታል፡፡

የኦቲዝም ችግር በተማሪዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የማህበራዊ ግንኙነት፣ ተግባቦት እና ባህሪ ችግር የሚያስከትልና በዚህም ሳቢያ በትምህርት አቀባበል ላይ ጉልህ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖውን የሚያሳርፍ ክስተት ቢሆንም፣ በሁሉም ደረጃዎች በሚገኙ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ መጠነኛ የሆነ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ይገኛሉ::

በመሆኑም፣ በአካቶ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በመማር ላይ የሚገኙና ቀላል የሆነ የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች የትምህርትና ሥልጠና እኩልነትን እውን በማድረግ እንደችሎታቸውና ፍላጎታቸው በእኩልነት የትምህርት አቅርቦቱ ተቋዳሽ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ይህ ማኑዋል ተዘጋጅቷል።

ማኑዋሉ የተዘጋጀበት ዋና ዓላማ መጠነኛ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች በትምህርት ቤትና በክፍል ውስጥ እንደችሎታቸውና ፍላጎታቸው እንዲማሩ በማድረግ የተጀመረውን የሀገሪቱን ትምህርት ፍትሐዊነትና ተደራሽነትን በማስቀጠልና የትምህት ጥራትን ዕውን ማድረግ ነው።

## 1.1. የማኑዋሉ አጠቃቀም

ዉድ መምህር!!! ይህ ማኑዋል በዋነኝነት ቀላል የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ለማስተማር በእጅጉ ይረዳዎታል። በዉስጡ ያሉት በርካታ ቁም ነገሮች፣ የልጆቹን ትምህርት ዉጤታማ ለማድረግ በእጅጉ ይጠቅማሉ። ማኑዋሉን ለመጠቀም የሚከተሉትን ጠቃሚ ምክሮችን ቢከተሉ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ውጤታማ ይሆናሉ::

1ኛ. ማኑዋሉን ከመጀመሪያ ጀምሮ በጥንቃቄ አንብበዉ ያልተረዱት ነገር ካለም ማስታወሻ በመያዝ ይህን ማኑዋል ላዘጋጀው አካል ጥያቄ ያቅርቡ።

2ኛ. ማኑዋሉ ዋና ዋና ጉዳዮችን ካልሆነ በስተቀር ጥቃቅን በሆኑ የኦቲዝም ጉዳዮች ዙርያ የተሟላ ምላሽ ላይሰጥ ስለሚችል ተጨማሪ ጽሁፎችን ማንበብ፤ ባለሙያዎችን ማነጋገርና መወያየት ጠቃሚ ነዉ።

3ኛ. ማኑዋሉ ዉስጥ መካተት ኖሮባቸዉ ያልተካተቱ ጉዳዮች ካሉና በትግበራ ላይ መምህራን በጣም የተቸገሩበትና መፍታት ያልቻሉት ጉዳይ ካለ፣ በጽሁፍ ማኑዋሉን ላዘጋጀዉ ክፍል መላክ ጠቃሚ ነዉ። ይህን ማድረጉ ወዲያዉኑ ምላሽ ለማግኘት ከመርዳቱም ባሻገር፣ ማኑዋሉ ሲሻሻል ለማካተት ይረዳል።

4ኛ. በትምህርት ቤቱ ወይም በአከባቢዉ የሚገኘዉ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ባለሙያ ስለማኑዋሉ ይዘት ለመምህራን፣ ለወላጆችና ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በስልጠና መልክ ማስተላለፍ ይጠበቅበታል።

5ኛ. ማኑዋሉ በማንኛውም ወቅት ከመምህር መለየት የለበትም። ማኑዋሉ ቤተመጻሕፍት የሚቀመጠዉ ትርፍ ሲሆን እንጂ ዋናዉ ዓላማዉ መምህራን በየዕለት ተግባራቸዉ እንዲጠቀሙበት ለማድረግ ነዉ።

6ኛ. በዚህ ማኑዋል መሠረት መምህር የሚለዉ ቃል ሁለቱንም ፆታ የሚመለከት ነዉ።

ማኑዋሉ በአስር ክፍሎች ዙሪያ ተደራጅቶ የቀረበ ሲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ፣ የማኑዋሉን ዓላማና አጠቃቀም ይዟል፣ ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ የኦቲዝም ችግር ምንነትና መንስኤዎችን ያብራራል በSስተኛው ምዕራፍ ላይ የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ሕፃናት ለይቶ ማወቂያ (Identification and Assessment) ዘዴዎች ቀርበዋል። በአራተኛው ምዕራፍ ላይ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ሕፃናት አያያዝ ዘዴዎች (Intervention Strategies) ይዳሰሳሉ። በምዕራፍ አምስት የአካቶ ትምህርት የኦቲዝም ችግር ላለባቸው ተማሪዎች የሚለው ርዕስ ይቀርባል። ምዕራፍ ስድስት የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብር መጠቀም (individualized Educational Program) የሚለውን ይዘት ያብራራል። ምዕራፍ ሰባት የሌሎች ባለሙያዎች የሥራ ድርሻና ኃላፊነትን ይገልጻል። ምዕራፍ ስምንት የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ዕቅድና ክንውን፣ ጠቃሚ ምክር/መረጃ (Tips for Teachers of Students with Autism) የሚለውን ጭብጥ ይዳስሳል። በምዕራፍ ዘጠኝ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ላይ መደረግ ያለባቸውና መደረግ የሌለባቸው (Do’s and Don’ts During Teaching of Students with Autism) ተግባራት ይቀርባሉ። የመጨረሻው ምዕራፍ የሚመለከታቸው ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት የስራ ድርሻና ኃላፊነት ላይ ትኩረት ያደርጋል።

ከዚህም በተጨማሪ በአባሪነት የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ዕቅድ ክንውን፣ለይቶ ማወቂያና መገምገሚያ መሣሪያዎች እንዲሁም ቅፆች በሞዴልነት ቀርበዋል። እነዚህ ጭብጦችና ዘዴዎች መንገድ ለመምራት ቢቀመጡም ፍጹም ተደርገው የሚወሰዱ ሳይሆኑ እንደተጨባጭ ሁኔታው እየተሻሻሉ የሚተገበሩ ናቸው። ስለሆነም ይህ የመምህር ማኑዋል ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት እንደ ነባራዊ ሁኔታው ዝርዝር ማዘጋጀትና ማቀድ እንደሚያስፈልግ ከወዲሁ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል።

# 2. የኦቲዝም ችግር ምንነትና መንስኤዎች

## 2.1. የኦቲዝም ችግር ምንነት

ኦቲዝም በአምዕሮ ተግባር ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር የተወሳሰበ የነርቭ ሥርዓት ችግር ሲሆን ልጆች ያዩትን፣ የሰሙትንና በስሜት ያገኙትን ከመረዳትና ከማስረዳት የሚገድብ ነው። ይህ ደግሞ በልጆቹ ላይ ከፍተኛ የሆነ የማህበራዊ ግንኙነት፣ የተግባቦት እና የባህሪ ችግር ያስከትላል።

የአሜሪካን የስነልቡና ባለሙያዎች ማኅበር (American Psychological Association) እንዳስገነዘበው (2008) ኦቲዝም ልጆች ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሦስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ የሚከሰት ከፍተኛ የዕድገት ችግር ሆኖ የተግባቦትና የማህበራዊ ግንኙነት ችግርና የሌሎችን ስሜት መረዳት ያለመቻል ባሕርይ ያለባቸውን ይመለከታል።

በተመሣሣይ መልኩ የአሜሪካን የስነአዕምሮ ባለሙያዎች ማኅበር (American Psychiatric Association, 2014) ኦቲዝም የዕድገት ችግር መሆኑን በማስገንዘብ፡

- የተግባቦትና የማህበራዊ ግንኙነት ችግር፣
- የተገደበ፣ ተደጋጋሚ እና ግለሰባዊ ቅርጽ ያለው ባህሪ፣ ፍላጎት እና ድርጊት፣
- በአምዕሮ ተግባር ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር የተወሳሰበ የነርቭ ሥርዓት ችግር መሆኑን ጠቅሷል።

ማኅበሩ ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ልጆች ከቀላል እስከ ከፍተኛ የአዕምሮ ዕድገት ችግር እንዳለባቸው አስነብቧል። ማኅበሩ የተለያዩ የመረጃ ምንጮችና የጥናት ውጤቶች በመጥቀስ እንደዘገበው ከሆነ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ልጆች ከላይ የተጠቀሱት የተለያዩ ችግሮች ተጠቂ ቢሆኑም ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ወይም ከ0.5-10% የሚሆኑት ልጆች አንዳንድ ክሂሎትና ችሎታዎች ሊኖራቸው እንደሚችል ጠቅሷል።

ከዚህም ባሻገር Autism Savant ተብለው የሚታወቁት የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ልጆች:-

- በአንዳንድ ችሎታዎች ተሰጥኦ፣
- ጠቃሚና ጠቃሚ ያልሆኑ ክስተቶችና ተግባራትን የማስታወስ ችሎታ፣
- በዕይታ ያገኙትን መረጃ (visual information procesining) በጥልቀት የመጠቀም ችሎታ፣
- አንዳንድ ነገሮች ላይ ከፍተኛ ትኩረት የማድረግ ችሎታ እንዳላቸው ተገልጿል::

ከትርጉሙ ለመረዳት እንደሚቻለው የኦቲዝም ችግር የተለያዩ ደረጃዎች ያሉት ሲሆን ከትምህርት አቅርቦት አንፃር ደግሞ ችግሩ ያለባቸው ልጆች በሁለት ዋና ዋና የትምህርት ዕገዛ

ሥርዓት ሊከፈሉ ይችላሉ። እነሱም ከፍተኛ ጉዳት ያለባቸው ልጆች ሆነው በልዩ ትምህርት ቤቶች ወይም በመደበኛ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ ልዩ ክፍሎች ውስጥ የትምህርት አገልግሎት የሚሰጣቸው እና መጠነኛ ጉዳት ያለባቸው ልጆች ሆነው በአካቶ ትምህርት ሥርዓት ውስጥ የመማር ችግሮቻቸውን በማገናዘብ እንደየፍላጎቶቻቸውና ችሎታዎቻቸው የትምህርት እና ስልጠና አቅርቦት የሚዘጋጅላቸው ናቸው።

በመሆኑም፣ ይህ ማኑዋል የተዘጋጀው በሁሉም ደረጃዎች በሚገኙ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአካቶ ትምህርት ሥርዓት ውስጥ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ለሚገኙ መጠነኛ የሆነ የኦቲዝም ችግር ላለባቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን የትምህርት ዕገዛ ለማድረግ ነው።

## 2.2. የኦቲዝም ችግር መንስኤዎች

ለኦቲዝም ችግር መንስኤ ይሆናሉ ተብለው የተለያዩ መላምቶች ሲዘነዘሩ የቆዩ ቢሆንም አሁንም በእርግጠኝነት ለይቶ ማወቅ ቀላል እንዳልሆነ የመስኩ ምሁራን ያስገነዝባሉ። የሕፃናት የአዕምሮ ሕመም ሀኪሞች (child psychiatrists) እንደሚያስረዱት የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ሕፃናት በምርመራ ሂደት ለይቶ ማወቅ የሚቻል ቢሆንም መንስኤውን ግን በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም። በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ዓቢይ ቁም ነገር ግን የኦቲዝም ችግር በዕርግማን፣ በዕርኩስ መናፍስት፣ እንዲሁም እናትና አባት በሠሩት ኃጢአት ምክንያት ወደ ልጆች የሚተላለፍ ክስተት አለመሆኑን ነው።

## 3. የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ልጆች ለይቶ ማወቂያ (Identification and Assessment) ዘዴዎች

National Autism Center እ.ኤ.አ. በ2009 ባወጣው ጽሑፍ ሁሉም ልጆች በተለያዩ ጊዜያት በቋንቋ ዕድገት፣ በተግባቦትና በሌሎች ባሕሪያት አንድ ዓይነት የዕድገት ሂደትን ሊከተሉ እንደማይችሉ አስገንዝቦ ብዙሃኑ ልጆች ግን ተመሣሣይና ጤናማ የሆነ የዕድገት ሂደት የሚያንፀባርቁ መሆኑን አስምሮበታል።

ማዕከሉ በመቀጠልም ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ልጆች በቋንቋና ማኅበራዊ ግንኙነት ክሂሎት ዕድገት ከዕድሜ ዕኩዮቻቸው በተለየ ሁኔታ የሚዘገዩ መሆናቸውን ጠቅሷል። ከእነዚህ የዕድገት ችግር ካለባቸው ልጆች መካከል የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ይገኙበታል።

ከላይ ለማስገንዘብ እንደተሞከረው፣ ኦቲዝም ካለባቸው ልጆች መካከል አብዛኛዎቹ የተግባቦት፣ በቋንቋ በመጠቀም መግለጽ እና በቋንቋ የተገለጸውን መረዳት ችግሮች አሉባቸው። መጠኑ እና አይነቱ ቢለያይም ሁሉም የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ልጆች የማህበራዊ ግንኙነትና የባሕርይ ችግር አለባቸው። ራስን የመቆጣጠር፣ ስሜትን የመቆጣጠር፣ ከሁኔታዎች ጋር ራስን በማለማመድ ፍላጎትን መግለጽና መጠቀም፣ የሌሎችን ስሜትና ፍላጎት በመረዳት መግባባት፣ ወዘተ ችግሮች ይታይባቸዋል።

ከዚህ በተጨማሪም አብዛኞቹ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ልጆች የነገሮችንና ክስተቶችን ግንኙነት ወይም ትስስር ምክንያትና ውጤት ለይቶ የማወቅ፣ መሰረታዊ የሆኑ የትምህርት ቅስሞሽ ዕውቀትና ክህሎት ችግር ለምሳሌ የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የተለያዩ የሂሳብ ስሌቶች ችግር፣ የመለካት ችግር፣ በማየትና በመጠየቅ የመረዳት፣ የማህበራዊ ሳይንስ፣ መሰረታዊ ዕውቀት፣ ክህሎትና ሌሎች ችግሮችንም ሊያንጸባርቁ ይችላሉ።

ሌላው የሚያሳዩት ዓቢይ ችግር ከሁኔታዎች ጋር በመጣጣም የራስን ህይወት መምራት (developing adaptive/coping skills) አለመቻል ለምሳሌ በምርጫ ተግባራትን የማከናወን፣ በራስ ውሳኔ መንቀሳቀስ (መተግበር)፣ አቅዶ መተግበር፣ የጊዜ አጠቃቀም፣ ችግሮችን ለይቶ ለችግሮቹ መፍትሄ የመፈለግ ክሂሎት ማጣት ነው። እንዲሁም ህግንና ደንብን ተከትለው ከአቻዎቻቸው ወይም ሌሎች ጋር በመጫወት ራሳቸውን የማዝናናት፣ ከማህበረሰቡ ጋር ተስማምተው የመኖር ችግር ይታይባቸዋል። በተጨማሪም አብዛኞቹ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ልጆች የግል ንጽህናን የመጠበቅ፣ በተገቢው ሁኔታ የመመገብ፣ በስርዓት የመጸዳዳት፣ የአለባበስ፣ በዕቅድ ተግባራትን የማከናወን፣ ከአደጋ ራስን የማዳን (የመከላከል)፣ ወዘተ ችግሮች ሊታይባቸው ይችላል።

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ልጆች ተገቢ የሆነ ሥነ-ፆታዊና ተያያዥ ጉዳዮች ዕድገት ችግሮች (problems in sexuality) ለምሳሌ የራሳቸውን የአካል ክፍል ጥቅምና ተግባር የመለየት ችግር ፣ በሥነ-ፆታዊ (Sexual) ህይወት ውስጥ የማህበረሰቡን ደንብና ባህል መጠበቅ አለማወቅ፣ የግል ህይወትን (privacy) አለማወቅ፣ ሥነ-ፆታዊ የሆኑ የህብረተሰብን ህግና ደንብ የመከታተል፣ ወዘተ ችግሮች ይታይባቸዋል፡፡

የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ልጆች ለይቶ በማወቅና አስፈላጊውን ችግር የመቀነስ ወቅታዊ ዕገዛ (early inervention) በማድረግ ሊያጋጥማቸው የሚችለውን ችግር ለመቀነስ ሕፃናቱ የሚያሣዩትን ባሕሪያት ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ልጆች በሕክምናና በሌሎች ዘዴዎች በመለየት ችግሩ እንዳለባቸው በዕርግጠኝነት መናገር የሚቻለው በሦስት ዓመት ዕድሜያቸው ላይ ነው፡፡ ምልክቶቹ በአንዳንድ ልጆች ላይ ከውልደት ጀምሮ የሚከሰቱ ሲሆን በተወሰኑት ላይ ደግሞ እንደማንኛውም ልጅ ከሦስት ዓመት በፊት ጤናማ የዕድገት ሂደትን ጠብቀው ካደጉ በኂላ ከ18 እስከ 36 ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ በድንገት ሊታዩባቸው ይችላሉ፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ልጆች በሁለት ዋና ዋና ደረጃዎች ይከፈላሉ እነሱም ችግራቸው ከፍተኛ በመሆኑ በልዩ ትምህርት ቤት የሚማሩ እና መጠነኛ ችግር ያለባቸው ሆነው ከዕድሜ ዕኩዮቻቸው ጋር በመደበኛ ትምህርት ቤት የሚማሩ ናቸው፡፡

## 3.1. በልዩ ትምህርት ቤት የሚማሩት ልጆች

ችግራቸው ከፍተኛ በመሆኑ በልዩ ትምህርት ቤት የሚማሩት ልጆች የሚያንጸባርቁት ዋና ዋና ባሕሪያት የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 3.1.1. በሁለት ዓመት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች

ከሌሎች የዕድሜ ዕኩዮቻቸው ጋር ሲነጻጸሩ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ልጆች በሁለት ዓመት ዕድሜአቸው አንዳንድ ባሕሪያትን ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ:

- ከሌሎች ሕፃናትና በአካባቢያቸው ከሚያገኟቸው ሰዎች ጋር አለመጫወት፣
- ከሰው ጋር ዓይን ለዓይን መተያየት (eye contact) አለመቻል፣
- የሚፈልጉትን ዕቃ በእጅ በማመልከት ማሣየት አለመቻል፣
- በእጃችን የምናመላክታቸው ነገሮችን ማየት አለመቻል፣
- በሁለት ቃላት ዓረፍተ ነገር መሥራት አለመቻል፣
- ለጥያቄ ወይም ሌላ ንግግር መልስ አለመስጠት፣

- ተደጋጋሚ የሆኑ ለምሳሌ እጅን ወደ ላይና ታች የማውለብለብ፣ የመሽከርከር ባሕሪይ ማሣየት፣
- በአሻንጉሊቶች መጫወት አለመቻል፣
- ባልተለመደ ሁኔታ በተረከዝ መራመድ ይገኙበታል።

### 3.1.2. ከሁለት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች

ከሁለት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ክልል የሚገኙት ልጆች የሚከተሉትን ባሕሪያት ሊያሳዩ ይችላሉ።

- ከሌሎች ሕፃናትና በአካባቢያቸው ከሚያገኟቸው ሰዎች ጋር አለመጫወት፣
- ከሰው ጋር ዓይን ለዓይን መተያየት (eye contact) አለመቻል፣
- የሚፈልጉትን ዕቃ በእጅ በማመልከት ማሣየት አለመቻል፣
- ልጆች ሲያናግዷቸው ያልተለመደ ምላሽ መስጠት፣ ወይም ምንም ምላሽ አለመስጠት፣
- እየተጫወቱ ባሉት አሻንጉሊት ወይም ሌላ መጫወቻ ዕቃ በመመሰጥ ለሌሎች በአካባቢያቸው ላለው ነገር ትኩረት አለመስጠት፣
- ትኩረት ሰጥተው የሚያከናውኑትን ተግባር ሲያቋርጧቸው ወይም ሲረብሿቸው መከፋት፣
- ተደጋጋሚ የሆኑ ለምሳሌ እጅን ወደ ላይና ታች የማውለብለብ፣ የመሽከርከር ባሕሪይ ማሣየት፣
- በቆሙበት ወይም በተቀመጡበት በሰውነታቸው ወደ ፊት ወደ ኋላ መሄድ፣
- በሌሎች ልጆች የተለመደን ድምፅ መጥላት፣
- ከሌሎች ሰዎች ጋር መነካካትና መተቃቀፍን መጥላት፣
- አንዳንድ ጠረኖችንና ጣዕሞችን መጥላት ናቸው።

## 3.2. በመደበኛ ትምህርት ቤት የሚማሩ ልጆች

መጠነኛ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ልጆች ዕገዛ እየተደረገላቸው በሁሉም መደበኛ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ የክፍል ደረጃዎች ላይ ትምህርታቸውን መከታተል ይችላሉ። በሁሉም የዕድሜ ክልል የሚገኙ መጠነኛ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ልጆች የሚከተሉትን ዋና ዋና ባሕሪያት ወይም ቀላል ምልክቶችን ሊያሳዩ ይችላሉ።

### 3.2.1. ከጉርምስና ዕድሜ ክልል በፊት (pre-teenage years) የሚገኙ ልጆች

በመጀመሪያዎቹ ከጉርምስና ዕድሜ በፊት በሚገኙት ዓመታት የኦቲዝም ችግር በአንዳንድ ልጆች ላይ ጉልህ የሆነ ተፅዕኖ ሳያሳይ በጉርምስና ዕድሜ መጀመሪያ ወቅት አካባቢ የሚከተሉት ቀላል ምልክቶች ሊከሰቱ ይችላሉ።

- ከሰው ጋር ዓይን ለዓይን መተያየት (eye contact) አለመቻል፣
- ጥቂት ሰዎችን ብቻ መቅረብ፣
- የሌሎችን ችግር መረዳትና ድጋፍ ማድረግ አለመቻል፣
- ተራ አለመጠበቅ፣
- በአካባቢው ከተለመደው ወጣ ባለ መንገድ ማውራት፣
- በሰውነት በታገዘ ወይም በምልክት (gesture) በመጠቀም ከሰዎች ጋር መግባባት አለመቻል፣
- ቃላቶችን መደጋገምና በተወሰኑ ርዕሶች ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ፣
- በደስታ ወይንም በንዴት ወቅት ያልተለመደ የሰውነት እንቅስቃሴ ማሳየት፣
- የውይይት ሥነ ሥርዓት አለማወቅ ናቸው።

### 3.2.2. በጉርምስና ዕድሜ ክልል (teenage years) የሚገኙ ልጆች

በጉርምስና ዕድሜ በሚገኙት ዓመታት የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ልጆች የሚከተሉትን ዋና ዋና ባሕሪያትን ሊያሳዩ ይችላሉ።

- ከሰው ጋር ለዓይን ለዓይን መተያየት (eye contact) አለመቻል፣
- ስሜትን የመግለፅ ችግር፣
- ከፍተኛ ድምፅና አንዳንድ ጠረኖችን መጥላት፣
- ጓደኝነት መመሥረት አለመቻል፣
- ቀጥተኛ ያልሆኑ ንግግሮችን መረዳት አለመቻል: ለምሳሌ ቀልዶችን፣ ሽሙጦችንና ተቃራኒ የሆኑ ዓረፍተ ነገሮችን፣
- የሌሎችን ሰዎች ስሜት፣ ሀሳብና ፍላጎት መረዳት አለመቻል፣
- ግትርነት፣
- በኅብረተሰቡ ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ሃሳብ መስጠት ወይም ባሕሪይ ማሳየት ለምሳሌ በቃል ወይም በመጨባበጥ መደበኛ ሰላምታ ከመስጠት ይልቅ ዝም ብሎ በሆነውም ባልሆነውም ሰዎችን በኃይል በማቀፍ ሰላምታ መስጠት፣

- በውይይት ወቅት ፍላጎታቸውን የሚመለከቱ ጭብጦች ላይ ብቻ ሀሳብ መስጠት፣
- መካከለኛና ከመካከለኛ ደረጃ በላይ ወይም ከፍተኛ የሆነ የአዕምሮና አስተሳሰብ ችሎታ መኖር፣
- ፅሑፍ (hand writing) መጥላት፣
- በሰውነት ማጎልመሻ (sport)ተግባራት ደካማ መሆን፣
- ተደጋገሚ የሆነ የድብርት ፀባይ ማሳየት፣
- ብዙ ጊዜ ከትምህርት ቤት መቅረት፣
- ረቂቅ ነገሮችን መረዳት አለመቻል፣
- በሚያከናውኑት ነገር ላይ በመመሰጥ ለሌሎች በአካባቢያቸው ላለው ነገር ትኩረት አለመስጠት ናቸው።

# 4. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ዘዴዎች (Intervention Strategies)

## 4.1. መግቢያ

በአጠቃላይ፣ ኦቲዝም ችግሩ ባለባቸው ተማሪዎች ላይ አካላዊ (physical)፣ አዕምሮታዊ (cognitive)፣ ማህበራዊ (social)፣ ስነ-ልቦናዊ (psychological) ዕውቀትና ክህሎት እድገት (academic knowledge and skills development) ላይ ከፍተኛ የሆኑ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ያሳድራል። በመሆኑም እነዚህ ተማሪዎች ተገቢ የሆነ ችግሩን የመቀነስ (intervention) ዕገዛ ያስፈልጋቸዋል። ችግሩን የመቀነስ እገዛ ተግባርም በትምህርት ቤቶችና ከትምህርት ቤቶች ውጪ ለምሳሌ ከቤተሰብና አካባቢ ጋር በትብብር የሚደረግ ሊሆን ይገባዋል (Missouri Autism Guidelines Initiative, 2012)።

አንዳንድ ችግርን በመቀነስ እገዛ የተገኙ ውጤቶች (intervention results) እንደሚያመለክቱት የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የትምህርት ቅስሞሽ ውጤትና ክህሎት ችሎታ መሻሻል፣ የማህበራዊ መስተጋብር ችሎታ መሻሻል፣ የመግባባትና ቋንቋ ክህሎት መሻሻል፣ ራስን በራስ የመምራት ችሎታ መሻሻል፣ ችግሮችን ለይቶ በማወቅ ለችግሮቹ መፍትሄ የመፈለግ ክህሎት መሻሻል፣ የተስተካከለ የአካል ዕድገትና የአካል ብቃትና ክህሎትን ለማሻሻል የሚያስችሉ ክሂሎች እንዲያዳብሩ ማድረግ ተችሏል።

የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የሁለንተናዊ ዕድገት ተጠቃሚ በመሆን ብቁና አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ለማስቻል ችግርን የመቀነስ እገዛ (Intervention) ሥራ፣ አስፈላጊ የሰው ኃይልና የግብዓት ዕገዛ ያስፈልጋል:: በግብዓትነት ታሳቢ ከሆኑት መካከልም ደረጃውን ጠብቆ የተዘጋጀ የመምህር ማኑዋል አንደኛው ነው:: የዚህ ማኑዋል ዓላማም መጠነኛ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎችን እንደየችሎታዎቻቸውና ፍላጎቶቻቸው በማስተማር ብቁና አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ማድረግ ነው:: በመሆኑም የችግሮቹን መንስኤዎች በጥናት በመለየት ችግሮችን ለመፍታት የሚከተሉትን የመማር-ማስተማር ዘዴዎች መጠቀም ያስፈልጋል።

## 4.2. የመማር-ማስተማር ስነ-ዘዴዎች

### 4.2.1. ተግባቦትና ቋንቋ (communication and language) የመማር-ማስተማር ዘዴዎች

#### 4.2.1.1.ትዕዛዝ (instruction) የመቀበል ችግር

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የመምህራንን ወይም የሌሎችን ትዕዛዝ የመቀበልና የመተግበር ችግር ሊያሳዩ ይችላሉ። ለዚህ ችግር መነሻ ምክንያቶች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ:- በሌላ ነገር ላይ ትኩረት ማድረግ፣ አንድ ቃል ወይም ሃሳብ በመያዝ ወደ

መደምደሚያ መድረስና ሌላ ሃሳብ አለማዳመጥ ወይም አለመረዳት፣ የትዕዛዙን ትርጉምና ምንነት መረዳት አለመቻል፣ ትዕዛዝ የሚሰጠው አካል በሚፈጥረው ስህተት ወይም ግድፈት ምክንያት በመናደድ ሌላ ዝርዝር ትዕዛዝ መከተልን ማቋረጥ፣ ትዕዛዝ መከተል በሚያስከትለው ውጤት አለመደሰት፣ የትዕዛዝ ቋንቋን መረዳት አለመቻል፣ በፍጥነት በሰዓቱና በቦታው ያለውን ሁኔታ መረዳት አለመቻል፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማዎች**

- የዕይታ (visual)፣ የማዳመጥ (auditory) ወይም ሌላ የትኩረት መስጫ ዘዴዎችን በመጠቀም ትዕዛዝ ማስተላለፍ፡፡ ይህን አንድ ለአንድ የትኩረት መስጫ ዘዴዎችን በመጠቀም ማለማመድ ይቻላል፣
- የቃላት ወይም በሌላ የድምፅ መስጫ ዘዴዎች ምልክት በመጠቀም ትኩረት ሊሰጥበት በሚገባ ነገር ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ፣
- በቀጥታ ማስተማር (direct teaching)፣ ሞዴል (model) በመጠቀም፣ በሚና ጨዋታ (role-play)፣ በቴፕ ሪከርድንግና በቪዲዮ ሪከርዲንግ በመታገዝ፣ በቀጥታ የማስተማር ዘዴ መከተል፣
- ካልገባቸው እንዲጠይቁና እንዲረዱ ማበረታታት፣
- መዝሙር፣ ተረትና ምሳሌ ወዘተ በመጠቀም ትዕዛዝ የመከተል ጥቅምና ጉዳትን ማስረዳት፣
- ትዕዛዝ መቀበልን በሥዕል፣ በድራማ፣ በእንቅስቃሴ ወዘተ እንዲያሣይ/ታሣይ/ ማለማመድ፣
- የተባለውን እንዲደግሙ በማድረግ በማስተማር የማስታወስ ችሎታቸውን ማዳበር፣
- ትዕዛዝን በትንሽ፣ በትንሹ በመከፋፈል (breaking in to small parts) መካከለኛና ረዥም ትዕዛዝ እንዲረዱ ማለማመድ፣
- የተለያዩ መርጃ መሣሪያዎችን ለምሳሌ የእይታ (visual) የመንካት (tactile) የድምጽ (audio)፣ ወዘተ በመጠቀም ከትዕዛዝ ጋር ግንኙነት እንዲኖራቸው ማለማመድ፣

**4.2.1.2. ስማቸው ሲጠራ የመሮጥ ወይም የመሸሽ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች**

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ስማቸው ሲነሳ ወይም ሲጠራ ሊሮጡ ወይም ሊሸሹ ይችላሉ፡፡ ለዚህም የተለያዩ መንስኤዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡- መጥፎ ልማድ፣ ከሰው ጋር የመገናኘት ፍርሃት፣ ትዕዛዝ ወይም ሌላ ነገር ይሰጡኛል የሚል ፍርሃት፣ በመሮጥ ወይም በመሸሽ መደሰት፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማዎች**

- ያለምንም ቁጣና ስድብ በፍቅር ልጁን/ጅቷን ወደ ቦታው/ዋ በመመለስ ስሙ/ሟ ሲጠራ መልስ እንዲሰጥ/ድትሰጥ የተለያዩ ማበረታቻዎች (reinforcers) በመጠቀም ማስረዳት፣ ለምሳሌ፡- የሚወደውን/ምትወደውን በመሸለም፣ በቃላት በማሞገስ ወዘተ፣
- ስሙ/ሟ ከተጠራ በኋላ ትዕዛዝ አለማስከተል፣ ይህ ተግባር ችግሩ እስኪቀንስና እስኪወገድ ድረስ መቀጠል አለበት፣
- የአባሮሽና የመሸሽ ጨዋታዎችን በግልፅና በተጨባጭ ምሳሌዎች (concrete examples) በመጠቀም ማስተማር፡፡

**4.2.1.3. የጊዜና የተግባር ሠሌዳ ላይ በማተኮር (attention) መረዳት ያለመቻል ችግር**

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ጊዜና የተግባራት ዝርዝር ሰሌዳ በማየትና በማንበብ የመረዳት ችግር ሊኖርባቸው ይችላል፡፡ ከችግሩ መንስዔዎች መካከል የሚከተሉት ሊካተቱ ይችላሉ፡፡ለምሳሌ በዓይን የሚታዩ ምልክቶች ተጨባጭ ነገሮች ስላልሆኑ ወይም ረቂቅ (abstract) ስለሆኑ የመረዳት ችግር፣ ወይም እነዚህን አይነት የመግባባት ዘዴ በማየት የመረዳት ልምድ አለመኖር፣ ወይም ብዙ ዓይነት የመረጃ ምንጮች ወይም ምልክቶች በአንድ ላይ በመቅረባቸው በተናጠል ትኩረት ሰጥቶ መረዳት አለመቻል ሊሆን ይችላል፡፡

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- የምልክቶችን ምንነት፣ አጠቃቀምና ትርጉም በተማሪዎቹ የመረዳት ችሎታ ደረጃ መሰረት ማስተማር፣ ምልክቶችን ተጨባጭ ከሆኑት አጠቃቀም በመጀመር ረቂቅ ፅንሠ ሃሳቦችን (abstract conceptst) ደረጃ በደረጃ ማስረዳት:: ለምሳሌ፡- የቀለም መቀቢያ፣ ባለቀለም ሥዕል ወይም ፎቶ ግራፍ፣ ጥቁርና ነጭ ቀለም መሥመር፣ ወዘተ መጠቀም፣
- ምልክቶችንና ትርጉማቸውን የተለያዩ የስሜት ህዋሳትን በመጠቀም እንዲለዩ ማድረግ፣
- የተግባራት የሰሌዳ ፕሮግራም (activity schedule) ሁል ጊዜ እንዲጠቀሙ መርዳት፣
- የተግባራት ሰሌዳ ፕሮግራሙን በመንደፍና በመወሰን ተማሪው/ዋ/ እንዲሳተፍ/ድትሳተፍ ማበረታታት፣
- የተለያዩ የጊዜ ሰሌዳ አጠቃቀሞችን በአንድ ጊዜ አለማድረግ፣ ለምሳሌ የጠዋትና የከሰዓት በኋላን ለብቻ ማድረግና መጠቀም::

### 4.2.1.4. የሰውነት እንቅስቃሴ ቋንቋን (body language) የመረዳት ችግር

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የሰውነት እንቅስቃሴ ቋንቋን የመረዳት ችግር ሊገጥማቸው ይችላል፡፡ የዚህ ችግር መንስዔዎች ከብዙዎቹ በጥቂቱ የዓይን ጥቅሻን፣ በጣት የማወዛወዝን፣ ጭንቅላት የመነቅነቅን፣ ፊት የመጨፍገግን፣ የመጨበጥ፣ የመተቃቀፍ ወዘተ ምንነትን የመረዳት ችግር ሊሆን ይችላል::

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- በምልክት ቋንቋ ለምሳሌ በሰውነት እንቅስቀሴ ቋንቋ(body language) የመግባባት ዘዴዎችና ትርጉም በምሳሌ በማስደገፍ እያሰሩ ማሳየት፣ ይህ የመግባቢያ ቋንቋ ከባህል ባህል፣ ከልምድ ልምድ ሊለያይ ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ራስን በመነቅነቅ የመግባባት ትርጉም ምንነትንና አስፈላጊነትን ማስረዳት፡፡

### 4.2.1.5. ተቀባይነት በሌለው ደረጃ ሰዎችን መቅረብ

አንዳንድ የኢቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ሌሎችን ለማነጋገር ወይም ለተለያዩ ጉዳዮች ሰዎችን በጣም ይቀርባሉ፡፡ በመቅረባቸው የተነሣ ሊጋጩም ይችላሉ፡፡ የዚህ ችግር ምክንያት ከሚከተሉት አንዱ ወይም ሁሉም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሰዎችን በምን ያህል ርቀት በመቅረብ ማነጋገር እንደሚቻል ህግና ሥርዓት አለማወቅ ወይም በሰዎች ላይ የተመለከቱት አንድ ነገር ስቧቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ፀጉር፣ ጢም፣ የተቀቡት ሽቶ፣ ማርኳቸው ለመንካት ወይም ለማሽተት ፈልገው ሊሆን ይችላል::

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- ሰዎችን መቅረብ ህግና ሥርዓትን በማህበራዊ ምሳሌዎች(social stories)፣ በማስመሰል (simulation)፣ በሚና ጨዋታ (role-play) ወዘተ በመጠቀም ማስተማር፣
- የክፍል አቻዎቻቸውን በሞዴልነት በመጠቀም ሰዎችን ቀርቦ የማነጋገር ልምምድ ማድረግ፣
- እይታ ፍንጭ (visual clues) በመስጠት ህግና ሥርዓትን በመደጋገም ማስረዳትና ማለማማድ፡፡

### 4.2.1.6. የመደጋገም (echolalia) ችግር

አብዛኞቹ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ቃላትን፣ ሐረግን፣ ጥያቄዎችን ወይም ትዕዛዝን ሊደጋግሙ ይችላሉ፡፡፡ የዚህ ችግር መንስዔዎች ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በፍጥነት የመረዳት ችግር ስላለባቸው መደጋገምን አማራጭ መጠቀም፣ ወይም ለሰሙት መረጃ በመደጋገም መመለስ መፈለግ፣ ወይም ለንግግር ቃላት ወይም ሐሳብ መልስ በፍጥነት

ማመንጨት አለመቻል፣ ወይም ቃላትን በተገቢው ቦታ አደራጅቶ መናገር አለመቻል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- ተማሪው/ዋ ለጥቂት ሰኮንድ (ለምሳሌ 10 ሰኮንድ) በመጠበቅ መደጋገም ከመጀመሩ በፊት ጥቂት ቃላት መናገር እንዲጀምር/ትጀምር ማለማመድ፣
- ተማሪው/ዋ በንግግር(conversation) ላይ እንዲቆይ/ድትቆይ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም፡፡ ለምሳሌ በምልክት እንዲያሣዩ፣ በሥዕል ወይም በተግባር እንቅስቃሴ መልስ እንዲሰጡ በማድረግ ቀስ በቀስ መደጋገምን ማስወገድ እንዲለማመዱ ማድረግ፣
- ተማሪው/ዋን አጭር መልስ የሚፈልጉ ዓረፍተ ነገሮችን ማስተማር፣
- ተማሪው/ዋን አንዳንድ ፅንሰ ሐሳቦችን (concepts) ለማስተማር የስሜት ህዋሳትን በመጠቀም ሳይደጋግም/ትደጋግም የተግባቦት ዕውቀትና ክህሎትን የማስፋት ዘዴ መጠቀም፣
- ሞዴል የሆኑ የክፍል አቻዎችን በመጠቀም ማለማመድ፡፡ ለምሳሌ የአንተ ስም ከበደ ነው፣ የእኔ ስም ግን አጊቱ ነው ወዘተ መጠቀም፣
- በመደጋገም ተግባቦት ችግርን እንደ ማስተማሪያ ስልት መጠቀም:: አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ቃላትን፣ ሐረግን ወዘተ የመደጋገም ባሕሪይ ይኖራቸዋል፡፡ ይህን የመደጋገም ችግር እንደማስተማሪያ መጠቀም ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ህግንና ሥርዓትን በመጨመር ተማሪው በመደጋገም እንዲማር ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ ዘዴ በተለይ በንግግር ወጌሻ (speech theraplist) ድጋፍ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡

### 4.2.1.7. የማህበረሰቡን ባህል በመከተል የመግባባት ችግር

አብዛኛዎቹ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የማህበረሰቡን ባህልና ወግ በመከተል የመግባባት ችግር ይታይባቸዋል፡፡

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማዎች**

- የማህበረሰቡን ባህል በተለያዩ የመግባቢያ ዘዴዎች ማሣወቅ፣
- የዕለት-ተዕለት ህይወት/ ተግባራት (daily activities) ውስጥ ይህን ተግባር ማካተት፣
- በሚጨበጥ(concrete) አገላለጽና በምሳሌ የማህበረሰቡን ባህል ተከትሎ የመግባባት ተግባር ማሣየት፡፡ ለምሳሌ፣ ህግን ጽፎ በመለጠፍ፣ በማህበረሰቡ በታወቁና በተለመዱ ተረትና ምሳሌዎች በመጠቀም ማስረዳት፣በተጨማሪም የማህበረሰቡን ባህልና ወግ

በመከተል የመግባባት ክህሎት በትምህርት ቤትና በአካባቢው እንዲለማመዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት::

### 4.2.1.8. በስፋት የተለመዱ (common) የተግባቦት ችግሮች

አብዛኛዎቹ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የተለያዩ የተግባቦት ችግሮች ሊታይባቸው ይችላል። ለምሳሌ አንዳንዶቹ ራሳቸውን ለመግለፅ ሲፈልጉ ሌላ ሦስተኛ ወገን ተውላጠ ስም ሊጠቀሙ ይችላሉ። እኔ ለማለት እሱ፣ እሷ ወይም እነሱ እያሉ ሊናገሩ ይችላሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ በማህበረሰቡ ተቀባይነት የሌለው የድምፅ አወጣጥ ለምሳሌ በጣም ከፍተኛ ወይንም ሊሰማ የማይችል ዝቅተኛ ወይም ለማዳመጥ የሚያስቸግር ፈጣን ንግግር ሊሆን ይችላል:: አንዳንዶቹ ደግሞ ተግባቦት ይጀምሩና ምልልሱን ያቆሙታል ወይም የመቀጠል ችግር ይታይባቸዋል።

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- የተለያዩ የመርጃ መሳሪያዎችንና የመማር-ማስተማር ዘዴዎችን ለምሳሌ በቀጥታ በግልጽና በቀላል ምሳሌ በመጠቀም ማሳየት፣
- በሚና ጨዋታ(role-play)፣ በቪድዮ(video)፣ በድምፅና(audio) የዕይታ (visual) የማስተማሪያ ዘዴዎች መጠቀም፣
- ለክፍል አቻዎቻቸው ስለ የኦቲዝም ችግር ዕክል ያለባቸው ልጆች የተግባቦት ችግርና ጠንካራ ጎኖችን ማስረዳት፣
- አጭርና ቀላል የሆኑ የተግባቦት መልመጃና ልምምድ ዘዴዎችን መጠቀም፣
- የቃላት አጠቃቀምና የጎደለውን ቃል የመሙላት ዘዴ መጠቀም፣
- የተለያዩ ጥቄዎችን በአጭርና ደረጃ በደረጃ የመመለስ ልምምድ በተግባር ማካሄድ፣
- የእይታ(visual)፣ የድምፅ (auditory)፣ ወዘተ ምልክት ወይም ፍንጭ (hint) መጠቀም::
- አዳምጦ በመረዳት መግባባትን ማስተማር። በዚህ ጊዜ በአይን በሚታይ ምልክት (visual clue) በመስጠት ትኩረት እንዲያገኙና እንዲያዳምጡ መርዳት፣
- መረጃውን አጭርና ግልጽ በሆነ መልኩ መስጠት፣
- የተለመዱ ተረትና ምሳሌዎች (folklore) በመጠቀም ተግባራትን ወይም ሁኔታዎችን ማስረዳት፣
- የአዳዲስ ቃላት ትርጉም (vocabulary) በተለየያ ዘዴዎች ማስተማር። ለምሳሌ በሚታይ፣ በሚዳሰስ፣ በሚሰማ፣ ወዘተ ተግባራት በመጠቀም፣

- መግለጽ/መግባባት ለሚቸግራቸው ተማሪዎች ያላቸውን የተወሰነ በንግግርና ንግግር ባልሆኑ (non-verbal) የመግባባት ዘዴዎችን በማበረታታት ወደ ተሻለ ደረጃ ማሳደግ::

**4.2.1.9. የማህበራዊ ግንኙነትና - ባህሪ ዕድገት (psycho - social) ችግሮች**

ከሌሎቹ ጋር ለመጫወት አለመፈለግ: አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ከሌሎች ጋር በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ተቀላቅሎ መጫወት ወይም መሥራት አለመፈለግ (ራስን ከሌሎች ማግለል) ባህሪይ ይታይባቸዋል:: ለዚህ ችግር መነሻ ከሚከተሉት አንዱ ወይም ተደራራቢ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

- የራሣቸውን ፍላጎት የሚያሟላ ለብቻቸው ማከናወን የሚፈልጉት ወይም ስሜታቸውን ሊያረካ የሚችል ነገር መኖር፣
- ከለሎች ጋር የመግባባት ችግር፣ ወይም
- ከሌሎች ጋር የመቀላቀል ፍርሃት ሊሆኑ ይችላሉ።

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- ተማሪውን/ዋን ሊያስደስት የሚችል ጨዋታ በመምረጥ ከሌሎች ጋር እንዲጫወት/ድትጫወት ማበረታታት፣
- ተማሪው/ዋን ከክፍል መምህሩ ወይም ረዳት መምህሩ ጋር እንዲጫወት/ድትጫወት ማለማመድና ቀስ በቀስ ከሌሎች አቻዎቹ ጋር እንዲቀላቀልና እንዲጫወት/ድትጫወት ማበረታታት፣
- ተማሪውን/ዋን ቀስ በቀስ በጋራ በማጫወት ማህበራዊ ግንኙነት ክሂሉን/ክሂሏን ማሳደግ::

**4.2.1.10. ሌሎች ሲያዝኑ ወይም ሲከፉ የመሣቅ ወይም ስሜት አልባ የመሆን ችግር**

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የሌሎችን ሰዎች የመደሰት ወይም የመከፋት ስሜት የመለየት ችግር ሊኖርባቸው ይችላል። አንዳንዶቹ ደግሞ ሆነ ብለው የመጉዳት ወይም ችግሩን የማባባስ ሁኔታ ሊያሣዩ ይችላሉ። ምክንያቱም ከሌሎች የሚያዩት ስሜት የሚያስገርም ወይም ግራ የሚያጋባ ወይም የሚስፈራቸው ሊሆን ስለሚችል ነው። ሌላው ደግሞ የሌሎችን ስሜት ማባባስ ስለሚያስደስታቸው ሊሆን ይችላል።

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- የሌሎች ሰዎችን የስሜት ሁኔታና ሊያስከፏቸው የሚችሉትን ነገሮች በምሳሌዎች በመታገዝ ማስረዳት፣
- የሌሎች ሰዎችን የመደሰት ፣የመከፋት፣ የመጎዳት፣ ወዘተ ስሜቶችን ምንነትና ትርጉም ማስረዳት።

- ሌሎች ሰዎች ሲከፉና ሲጎዱ መደረግ ያለባቸውን፣ የቃላት አመራረጥ፣ ስሜታቸውን የመጋራት ዘዴ ፣ወዘተ ማስተማር፡፡
- ሆነ  ብለው ሌሎች ሰዎችን ለመጉዳት ወይም ለማስከፋት የሚጥሩትን የኢቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች  ደግሞ በመቅጣት ወይም በማስፈራራት ሣይሆን፣ በፍቅር ህግንና ስርዓትን ማሳወቅ፣
- የምክር አገልግሎት (counseling) መስጠት፣
- ስሜቶች የሚገለጹበት የመርጃ መሣሪያዎች (ስዕል፣ ቪዲዮ) መጠቀም፣
- በተጨማሪም ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዴት ስሜትና ፍላጎትን መጋራት እንደሚችሉ በምሳሌና በተግባር ማስረዳት፡፡

### 4.2.1.11. የሌሎች ሰዎች ስሜት መለዋወጥ ወይም አቀራረብ ለመጉዳትና ለማስከፋት እንደሆነ አድርጎ የማሰብ ችግር

አንዳንድ የኢቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የክፍል አቻዎቻቸው፣ መምህራን ወይም ሌሎች ሰዎች  እነሱን ለማጥቃት ወይም ለመጉዳት ጥረት እያደረጉ ነው በማለት አላስፈላጊ ግጭት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ምክንያታቸው ለምሳሌ የምፈልገውን ትከለክለኛለች፣ የምፈልገውን ለማድረግ አትፈቅድልኝም፣ የማልፈልገውን እንዳደርግ ታደርገኛለች በሚል አስተሳሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ ለእንደዚህ ዓይነት ችግሮች መንስዔዎች ከሚከተለኩት ውስጥ አንዱ ወይም ሁሉም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሌሎች እንዴትና ለምን ገፅታቸው እንደሚለዋወጥ አትኩሮት ባለመስጠት ወይም የሌሎችን ሰዎች ስሜትና እንቅስቃሴያቸው ከራሣቸው ፍላጎትና እንቅስቃሴ ጋር የተገናኘ ነው ብሎ የማሰብ ሊሆን ይችላል፡፡

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- የሌሎች ሰዎችን ስሜትና እንቅስቃሴ ከእነሱ ፍላጎት ወይም ሥራ ጋር ግንኙነት ሊኖረው እንደማይችል በሞዴሎች፣ በተጨባጭ ምሳሌዎች፣ የተለያዩ የመርጃ መሣሪያዎችን፣ ወዘተ በመጠቀም  ማስተማር፣
- እንደዚህ ዓይነት ችግሮችን ምሳሌ በማድረግ ሚና በመተካት (role-play)፣   በማስመሰል (simulation)፣ ወዘተ በመጠቀም ማስተማር፣
- እንደዚህ ዓይነት ችግሮች ሲፈጠሩ ተማሪውን/ዋን/ በተረጋጋ መንፈስ በማረጋጋት ሁኔታዎችን በማስረዳት ከላይ የተጠቀሱና ሌሎች ዘዴዎችን መጠቀም፡፡

### 4.2.1.12. የሌሎችን ሰዎች ድርጊትና ባህሪይን የመተቸት ችግር

የዚህ ችግር ዋና ምክንያት የተለመዱ ማኅበራዊ ሕግጋትን አለማክበርና ከሕግጋቱ ውጭ የሆኑ ነገሮችን (exceptionalities) አለማወቃቸው ሊሆን ይችላል፡፡

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- የህግ አከባበርና ከህግ ውጭ የሆኑ ነገሮችን (exceptionalities) በምሳሌ፣ የመርጃ መሣሪያዎች በመጠቀም፣ ወዘተ ማስረዳት፣
- በሚና ጨዋታ (role-play) ዘዴ ማስተማር፡፡ ለምሳሌ ተማሪው በሕግ የመመራትና የመተቸት ሚናና የተቀባይነትን ሚና እንዲጫወት በማድረግ በሕግ የማይገዙና የማይተቹ ነገሮችን ማስተማር፣
- የመተቸት ወይም የማብጠልጠል ነገር ሌሎችን ሰዎች እንደሚጎዳ በምሳሌ በማስረዳትና ሌሎችም ዘዴዎች መጠቀም፡፡

**4.2.1.13. ከአንድ ሰው ላለመለየት (የመጣበቅ) ፍላጎት ወይም የመጥላት ችግር**

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ከአንድ ሰው ያለመለየት ፍላጎት ሊታይባቸው ይችላል፡፡ ለምሳሌ ግለሰቡን ሲያዩ አብሮ የመጫወት፣ ሙሉ ትኩረቱን የማግኘት ፍላጎት፣ በግለሰቡ ላይ ሙሉ ትኩረት የማድረግ ፍላጎት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ምክንያቶችም ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በሕፃንነታቸው ያደጉት በአንድ ሰው ድጋፍ ከሆነ ከዚህ ሰው ውጭ ሌላ መቅረብ አይፈልጉም፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር መቀላቀል ጉዳት እንደሚያስከትል በማሰብ ወይም የሌሎችን ባህሪይ አለማወቅ ሊሆን ይችላል፡፡

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- ተማሪው መቅረብ የሚፈልገው ሰው ጋር ሌሎችን በመቀላቀል ከሌሎች ሰዎች ጋር መቅረብን ቀስ በቀስ ማለማመድ፣
- በማህበረሰብ ውስጥ የተለመዱ እና ለደረጃው የሚመጥኑ ተረትና ምሳሌዎችን (folklores) በመጠቀም ጓደኝነት ወዘተ የመመስረትና ጓደኛ የመሆን ህግ፣ ተራ በተራ የመነጋገርና የመተሳሰብ ልምድ፣ ወዘተ ማስተማር፣
- ከላይ የተጠቀሱ ተግባራትን በክፍል ውስጥ፣ በት/ቤት ውስጥ እንዲሁም በቤተሰብና በማህበረሰብ ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የተለያዩ የመርጃ መሣሪያዎችን በመጠቀም ስለሚጠላው ሰው ጥሩ ባህሪያትና ተግባራት ማስረዳት፣
- ተማሪውን/ዋን/ ከሚጠላው /ከምትጠላው/ ሰው በማራቅ አዲስ ትኩረት እንዲያገኙ በማድረግ ማለማመድና ማረሳሳት፣
- የሚጠላው/ምትጠላው ሰው ተማሪውን/ዋን/ በምንም ዓይነት ሊጎዳ እንደማይፈልግና እንደሚወደው(ዳት) ማስረዳትና ሌሎችንም ዘዴዎች መጠቀም ያስፈልጋል::

4.2.1.14. የሌሎችን የግብዣ ወይም የደስታ ሥርዓት አለመቀበል

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የአቻዎቻቸውንና የሌሎችን ሰዎች የግብዣ ወይም ሌላ የደስታ ሥርዓትን የመረበሽ ፍላጎት ሊያሣዩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የልደት ቀን ሥነ-ሥርዓት፣ የክብር በዓል ሥርዓት ወዘተ፡፡ በዚህ ወቅት የሚከናወኑ ተግባራትን ለምሳሌ ሻማ ማጥፋት፣ አንዳንድ ስጦታዎችን ለራስ የመውሰድ ወዘተ ችግር ሊያሣዩ ይችላሉ፡፡ ከችግሩ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የግብዣ ወይም የደስታ ሥርዓት የማክበርን ሕግ ወይም የማክበርን ጥቅም ያለማወቅ ሊሆን ይችላል፡፡

የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ

- የተለያዩ ክብረ በዓላትን፣ የልደት በዓል አከባበርን ወዘተ በተለያዩ ዘዴዎች ማስረዳት፡፡ ይህንን ተግባር ሚና ጨዋታን (role-play) በመጠቀም፣ ማህበራዊ ተረትና ምሳሌዎችን (folklores) በመጠቀም፣ የጊዜ አቆጣጠርና ትርጉምን በማሳየት፣ ወዘተ በተጨባጭ ምሳሌዎችና ተግባራት ማስተማር፣
- እንዲሁም የአንድን ሰው የልደት ቀንና የሌሎች በዓላትን አከባበርን በዓሉ ከመድረሱ በፊት ክፍል ውስጥ (ቤት ውስጥ) በሚና ጨዋታ (role-play)፣ ሞዴል በመጠቀም፣ ወዘተ ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡

4.2.1.15. ያለመሳሳት (ያለመሸነፍ) ፍላጎት ችግር

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አንድን ተግባር በተሣካ ሁኔታ ማከናወን ወይም ጨዋታን በማሸነፍ መደምደም የማይችሉ ከሆነ ለመሳተፍ ፍቃደኛ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ከተሸነፉም አደገኛ ባህርይ ሊያሣዩ ይችላሉ፡፡ ለዚህ ችግር ምክንያቶቹ የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በማሸነፍ ህግ ብቻ የመሥራት፣ ክብርን የማስጠበቅ፣ የበታችነት ስሜት፣ ሽንፈትን መፍራትና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ

- ተማሪውን/ዋን ጨዋታ ለማህበራዊ ግንኙነትና ለደስታ ምንጭ እንደሆነና ሁል ጊዜ ማሸነፍ እንደማይቻል በምሳሌዎች ማለማመድ፣
- እንደሁኔታው ማሸነፍና መሸነፍ፣ መሣሣትና በትክክል መሥራት ሊኖር እንደሚችል በጨዋታ ማለማመድ ያስፈልጋል፣ ጨዋታውን በሚለማመድበት ወቅትም አሸናፊና ተሸናፊውን በማቀያየር ማለማመድ፣
- ተማሪው/ዋ ለራሱ/ሷ ያለውን/ላትን አመለካከት (self-esteem) ማሳደግ፡፡

### 4.2.1.16. ሌሎች ሰዎችን የመውደድ ወይም የማቅረብ (affection) ፣ የመቃወም ወይም ያለቦታው የመፈለግ (seeking inappropriately) ችግር

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ሰዎችን የመውደድና የማቅረብ ፍላጎት ይቃወማሉ፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በአላስፈላጊ ቦታና ጊዜ ሰዎችን የመውደድ ወይም የማቅረብ ፍላጎት ይሻሉ፡፡ ለዚህ ችግር ምክንያቱ ሰዎችን የችግር፣ የደስታና የትኩረት ምንጭ አድርጎ በመውሰድ የሚከሰት ባሕሪይ ነው ፡፡

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- በዚህ ዙሪያ ማህበራዊ ተረትና ምሳሌ፣ የሚና ጨዋታ (role-play) በመጠቀም ማስረዳት፣
- ተማሪውን/ዋን ሌሎች ሰዎች እንደሚወዱት/ዷትና የመንከባከብ ፍላጎት እንዳላቸውና የሚያቀርቡት/ቧት መሆኑን በተጨባጭ ተግባርና ምሳሌ ማሣየት፣
- ተማሪውን/ዋን ሌሎች ሲቀርቡት/ቧት ምንም ጉዳት እንደማይደርስበትና/ባትና ተገቢ የሆነ መቀራረብ በተገቢው ጊዜ እንደሚያስፈልግ ለማስረዳት ፍቅር(መውደድ) የሚገለፅባቸው ድርጊቶችን እንደየሁኔታዎቹ በመለዋወጥ ማለማመድ (ማቀፍ መሳም፣ መጨበጥ ወዘተ.)፡፡

### 4.2.1.17. ሌሎች የማህበራዊ መስተጋብር ክሂሎት (social interaction skills) ችግሮች

የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውን የሚከተሉትን ዋና ዋና የማህበራዊ መስተጋብር ስርዓት እንዲለማመዱ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ተራ መጠበቅ ፣ በተራ መናገር፣ ከአንድ ርዕስ ወደ ሌላ ርዕሰ ጉዳይ በሥርዓት መሸጋገር፣ ንግግርን ወይም ምልልስን በስርአት ማጠናቀቅ፣ንግግርን ወይም ማህበራዊ መስተጋብርን መጀመር፣ እንደ ሁኔታው መናገር፣ እንደሁኔታው መቃወም ወይም መስማማት፣ አስፈላጊ ሲሆን ዝም ማለት ወይም መናገር ናቸው::

### 4.2.1.18. በአቻዎቻቸው አማካኝነት ማህበራዊ ህይወት ማስተማር

አብዛኛዎቹ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎችን በአቻዎች እገዛ አማካኝነት ዋና ዋናዎቹን የማህበራዊ መስተጋብር ስርዓት ማስተማር ይቻላል፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን ዘዴዎች መጠቀም ይቻላል፡፡

- ተማሪው/ዋ የሌሎችን የአቻዎች ትኩረት የማግኘት ዘዴዎችን እንዲጠቀም/ትጠቀም መርዳት፣
- በአቻዎች አማካኝነት በተማሪው/ዋ ላይ የማህበራዊ ግንኙነት (social interaction) ክሂሎት እድገት እንዲፈጠር ማነሳሳት፣

- ተማሪው/ዋ የተለያዩ የመጫወቻ ዓይነቶችን በማፈራረቅ ከአቻዎች ጋር እንዲጫወት/ድትጫወት ማበረታታት፣
- ተማሪው/ዋ የማህበረሰቡን ባሕሪይ ሞዴል በማድረግ ከአቻዎች ጋር መጫወት እንዲለማመድ/ድትለማመድ ማድረግ፣
- በተማሪው/ዋ ደካማ ጎን (weaknesess) ሣይሆን በታየው ጠንካራ ጎን (strengthes) ላይ ማተኮር፣
- ተማሪው/ዋ ከአቻዎቹ ጋር ቃለ-ምልልስ (conversation) እንዲያደርግ/ድታደርግ ማበረታታት፣
- ተማሪው/ዋ ከአቻዎቹ/ቿ ጋር ተራ በመጠበቅ የማህበራዊ ግንኙነትን አሠራሮችን እንዲለማመድ/ድትለማመድ ማድረግ፣
- ተማሪው/ዋ ለአቻዎቹ/ቿ ጨዋታዎችን ወይም ሁኔታዎችን እንዲተርክ/ድትተርከ ማበረታታት፣
- ተማሪው/ዋ ከአቻዎቹ/ቿ ጋር ሚና በመተካት (role-play) የመማር ዘዴ ላይ እንዲሣተፍ/ድትሣተፍ ማበረታታት፡፡

4.2.1.19. ጓደኝነት የመመሥረት ክህሎትን የማሣደግ ዘዴ

አብዛኛዎቹ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ጓደኛ የመመሥረትና ጓደኝነትን የማክበር ወይም ጠብቆ የማቆየት ችግር ይታይባቸዋል፡፡ ስለዚህ ወላጆችና መምህራን የእነዚህን ተማሪዎች ጓደኛ የመመሥረት ክህሎት ሊያሣድጉ ይገባል፡፡ ከእነዚህ ዘዴዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ተማሪው/ዋ ጓደኛ መመሥረት እንዲለማመድ/ድትለማመድ መርዳትና ማበረታታት፣
- በቤተሰብ አካባቢ ያሉ አቻዎች ከተማሪው/ዋ ጋር እንዲጫወቱ ማበረታታት፣
- ተማሪው/ዋ ከጓደኞቹ/ቿ ጋር እንዴት እንደሚጫወት/ምትጫወትና እንደሚደጋገፍ/ምትደጋገፍ እንዲያይና/ድታይና እንዲለማመድ/ድትለማመድ ማድረግ፣
- ተማሪው/ዋ ከጓደኞቹ/ቿ ጋር ጨዋታዎች ላይ እንዲሣተፍ/ድትሣተፍ ማበረታታት፣
- ጓደኞቹ/ቿ የተማሪውን/ዋን ባሕሪይና ሌሎች ሁኔታዎች እንዲረዱ ማድረግና አዎንታዊ አመለካከት እንዲያሣድጉ ማበረታታት፣
- ተማሪው/ዋ ከጓደኞቹ/ቿ ጋር እንዲዝናናድትዝናና የተለያዩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

በተጨማሪም ማህበራዊ ግንኙነት ስናስተምር የሚከተሉትን ክሂሎት ማሳደግ ይገባል፡፡

- ቀላል፣ የተለመደና ግልጽ የሆነ የማህበራዊ ግንኙነት ክህሎት በመጀመር ደረጃ በደረጃ ማህበራዊ ግንኙነትን ማሳደግ፣
- ተፈጥሮአዊ በሆነ አካባቢ(natural setting)፤ ተገቢ የሆነ ምልክት ወይም ፍንጭ መስጠት፣
- በማህበረሰቡ በታወቁ ተረትና ምሳሌዎች (folklores) በመጠቀም አዳዲስ ተግባራትን ለማስተዋወቅ፣ የሌሎችን ባሕሪይ ለማሳየት፣ እንደቦታውና ሁኔታዊ ማህበራዊ ግንኙነትን ማስተማር፣
- በማህበረሰቡ በታወቁ ተረትና ምሳሌዎች (folklore) በመምህሩን ወይም በተማሪዎች ሲነበብ ተማሪው/ዋንና/ መምህሩን በመከተል ማንበብ ይችላል/ ትችላለች፡፡ ስለሆነም በየቀኑ እንዲያነብ በማድረግ ማህበራዊ ግንኙነት (መስተጋብር) ማስተማር ይቻላል፡፡
- **መልስ መጠበቅ-** ይህን በዕይታ ምልክቶች፣ በሥዕል፣ በቃላት ወዘተ በመጠቀም ማለማመድ፣
- **ተራ ጠብቆ የመነጋገር** /ተግባቦት (communication)- ይህ ተግባር ተረትና ምሳሌዎች (folklores) በመጠቀም፣ ፎቶግራፍን በመጠቀም፣ እንዲሁም ተራ በመጠበቅ መነጋገርን በተግባር በማለማመድ ማስተማር ይቻላል፣
- **ከአንድ ተግባር ወደ ሌላ ተግባር ሽግግር (transition from one activity to another activity)** -ይህን ምልክት በመስጠት፣ተረትና ምሳሌዎች (folklores) በመጠቀም ማስተማር፣
- **በንግግር ወቅት ከአንድ ሐሳብ ወደ ሌላ ሐሳብ መቀየር-** የእይታ ፍንጭ (visual clue)፣የጊዜ ገደብ፣ ወዘተ በመጠቀም ከአንድ ሐሳብ ወደ ሌላ ሐሳብ ሽግግር ማስተማር፣
- **ንግግርን ወይም ጨዋታን ማቆም ወይም መጨረስ-** ይህን ተግባር የሌሎች ተማሪዎችን (ጓደኞችን) እንቅስቃሴ መሠረት በማድረግ ማቆም፣ የሰዓት ገደብ መጠቀም፣
- **ግንኙነትን (ንግግርን) መጀመር-** ሌሎችን እንዴት መቅረብ እንዳለበት/ባት፣ አንድ ነገር መጠየቅን፣ ወደ ጨዋታ መግባት፣ ሰላምታ መስጠት፣ ግንኙነቱ አስፈላጊ ካልሆነ ወይም አስደሳች ካልሆነ መተውን ወዘተ ማስተማር፣
- እንደ አስፈላጊነቱ ንግግርን ወይም ጨዋታን መቀየር (being flexible in communication)::

### 4.2.2. **የባህሪይና የስሜት ዕድገት ችግሮች** (behavioral and emotional problems)

#### 4.2.2.1.**የጠብ አጫሪነት** (aggressive behavior problem) **ችግር**

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የጠብ አጫሪነት ችግር ይታይባቸዋል:: ለምሳሌ የመደባደብ፣ የመሳደብ፣ የመናከስ፣ ንብረት የማውደምና የመሳሰሉት ናቸው። የዚህ ችግር መንስዔ የተለያየ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ቁጣን፣ ፍርሃትን፣ ብስጭትን፣ መከፋትን ፣ ወዘተ ከቁጣ ውጭ በሌላ መንገድ መግለጽ አለመቻል፣ ወይም የሌሎችን ትኩረት በቁጣ ማግኘት (በዚህ መንገድ አግኝተው ከሆነ በዚያው መቀጠል)፣ ወይም ከማይፈልጉት ወይም ከማያስደስታቸው ተግባር ለመሸሽ ይህን እንደ አማራጭ ይጠቀማሉ።

**የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- የተማሪዎቹን የጠብ አጫሪነት ተግባር የሚያነሳሱ ነገሮችን ማጥናትና መቀነስ፣
- ተማሪዎቹ ከጠብ አጫሪነት ተግባር በኋላ የሚያሣዩትን ባህሪንና የሚያገኙትን ውጤት በማጥናት ችግሩን ማስወገድ/ መቀነስ፣
- ተማሪዎቹ የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት የሚችሉበት ሌላ ተቀባይነት ያለው ባሕሪይ ማስተማር (ለምሳሌ እጅ በማውጣት መጠየቅ ፣ በጽሑፍ መጠየቅ፣ ወዘተ)፣
- የመማር-ማስተማር ሂደትንና የክፍል ውስጥ አካባቢን በተማሪው ፍላጎትና ችሎታ መሠረት ማስተካከል፣
- ከወላጆችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በችግሩ መፍትሔ ላይ ትኩረት በማድረግ መሥራት::

#### 4.2.2.2.**የቅጽበታዊ ቁጣ ችግር** (tantrums)

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የቅጽበታዊ ቁጣ (tantrums) ችግር ይታይባቸዋል:: ለምሳሌ ተማሪው አንድ ነገር ሲያይ ወይም ሲሰማ በቅጽበት በመቆጣት፣ በማልቀስና በመጮህ አላስፈላጊ የሆነ የባህሪ ችግር ሊያሳይ ይችላል:: የችግሩ መንስዔዎች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላል። ለምሳሌ አይቻልም ወይም ትክክል አይደለም የሚሉትን ቃላት ከሰዎች ቢሰማ ሰዎቹ ሆን ብለው ጉዳት ሊያደርሱበት እንደሆነ መገመት፣ የፈለገውን ነገር በቁጣ ማግኘት እንደሚችል ማመን (ከልማድ የተገኘም ሊሆን ይችላል)፣ በቁጣ የማይፈልገውን ተግባር ወይም ድርጊት ማስወገድ እንደሚችል ማመን (ከልማድ የተገኘም ሊሆን ይችላል)፣ ወይም ሌላ ችግር ሊሆን ይችላል።

**የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

በተማሪው/ዋ ላይ ቁጣ የሚያስነሱ ቃላትን ወይም ተግባራትን አለመጠቀም። ነገር ግን በሌላ ዘዴ ትክክል አለመሆኑን ወይም አይቻልምን ማስረዳት (ለምሳሌ፡ እስኪ እናረጋግጠው፣ በሌላ መልኩ እንየው፣ ወዘተ የሚሉ ቃላትን መጠቀም)፣

- በቁጣ ሣይሆን የፈለጉትን ነገር የማግኘት አማራጭ ዘዴዎችን ማስተማር (ለምሳሌ፡ እጅ በማውጣት መጠየቅ፣ አስተያየት በመስጠት መጠየቅ፣ ወዘተ)፣
- ይህን ተግባር በሞዴል፣ በሚና ጨዋታ (role-play)፣ በተረትና ምሳሌ (foklore) ወዘተ፣ በመጠቀም ማስተማር፣
- አንዳንዴ የተማሪውን/ዋን የቁጣ ድርጊቶች ችላ በማለት ማለፍና የሚፈልገውን/ምትፈልገውን ነገር በቁጣ ምክንያት እንዳያገኝ/ድታገኝ ማድረግ፣
- ከተማሪው/ዋ ወላጆችና ተገቢ ባለሙያዎች(professionals) ጋር በትብብር በመሥራት ለችግሩ የመፍትሔ እርምጃ መውሰድ።

4.2.2.3.**የፍርሃት ወይም የጭንቀት ችግር** (anxiety problem)

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የፍርሃት ወይም የጭንቀት ችግር ይታይባቸዋል:: በመሆኑም የዚህን ችግር ለመፍታት የሚከተሉትን የማስተማሪያ ዘዴዎች መጠቀም ያስፈልጋል።

**የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- በተማሪው/ዋ ከእውነታው የራቀ አስተሳሰብ ችግር ካለ በማጥናት እውነታውን እንዲለማመድ/ድትለማመድ ማድረግ፣
- ተማሪው/ዋ ቀስ በቀስ የሚያስፈራውን/ራትን ነገር እንዲለማመድ/ድትለማመድ (ለምሳሌ፡- ከአንድ ጓደኛ ጋር፣ ከሁለት ወይም ሶስት ጓደኛ ጋር፣ ከአንድ ትንሽ ቡድን ጋር፣ ከክፍል ተማሪዎች ጋር፣ ብዙ ህዝብ ባለበት እንዲጫወት/ድትጫወት በማለማመድ፣)፣ማድረግ
- ተማሪው/ዋ የቤት ስራ ወይም ሌላ ተግባር ለመስራት የሚፈራ/ምትፈራ ከሆነ በቀላል ጥያቄና ተግባር ቀስ በቀስ የአሰራር ልምድን ማዳበር፣
- ሌሎች ተማሪዎችን በችግሩ ዙሪያ በሞዴልነት በመጠቀም(በህዝብ ፊት መናገር፣መዝፈን፣ወዘተ) ተማሪውን/ዋን ማለማመድ፣
- ከተማሪው/ዋ የሚፈለገው አዎንታዊ ባህሪይ ሲታይ ማበረታቻ መስጠት/መሸለም/::

### 4.2.3.የአዕምሮአዊ ዕድገት (cognitive development) ችግር

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ከፍተኛ የሆነ የአዕምሮ ብስለት ውስንነት (cognitive) ችግር ይታይባቸዋል። በመሆኑም የዚህን ችግር ለመፍታት የሚከተሉትን የማስተማሪያ ዘዴዎች መጠቀም ያስፈልጋል።

**የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- ተማሪው/ዋ ፍንጭ (clue) በመጠቀም አንድ ነገር መረዳት እንዲችል/ድትችል በተለያዩ ተግባራትና በተጨባጭ ምሳሌዎች ማስረዳት፣
- ተማሪው/ዋ ረቂቅ የሆነ (abstract) ሐሳብንና ቋንቋን በማህረሰቡ ህግና ሥርዓት እንዲጠቀም/ድትጠቀም በተለያዩ ተግባራትና በተጨባጭ ምሳሌዎች ማስረዳት፣ ልምምድ እንዲያደርግም/ድታደርግም ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ተማሪውን/ዋን ረቂቅ የሆነ ሐሳብ ማመንጨት፣ መተንተን፣ በምክንያት ማስደገፍ፣ በምሳሌና በተለያዩ ቀላል የሆኑ ተግባራት ማስተማር፣
- ለተማሪው/ዋ የሌሎችን ሰዎች ስሜት በመረዳት መጋራት፣ ስሜትንና ፍላጎትን የማካፈል ክህሎትን በተለያዩ ተግባራት፣ ምሳሌዎችና ልምምዶች ማዳበር፣
- ተማሪው/ዋን አቅዶ የመተግበር፣ ተግባራትን በሥርዓት የማከናወን፣ ችግርን በተቀናጀ መንገድ የመፍታት ዘዴዎችን ማስተማር::

በተጨማሪም የሚከተሉትን የመማር-ማስተማር ዘዴዎች መጠቀም ያስፈልጋል::

- በትኩረት ማሰብና የመሥራት፣
- ትኩረት መቀያየር፣
- ምክንያትና ውጤት መለየት፣
- ለምን፣ እንዴት፣ ወዘተ፣ የመሳሰሉ ጥያቄዎች መመለስ፣
- የአንድን ነገር እንድምታ መረዳት (understand inference)፣
- አንድን መረጃ ከሌላው ጋር ማዛመድ፣
- ከድርጊቱ ወይም ከሁኔታው በመነሣት ለወደፊቱ ሊከሰት የሚችል ነገርን መገመት፣
- ቁሳቁስን በመጠን፣ በዓይነት ወዘተ ማደራጀት፣
- ተግባራትን በመጠን፣ በዓይነት፣ በጠቀሜታ ወዘተ ማደራጀት፣ ማዛመድ፣
- በምርጫና በውሳኔ ተግባራትን፣ ፍላጎትን ወዘተ፣ ማከናወን፣
- ተግባራትን በማስረዳት ወደ ትንንሽ ተግባራት መከፋፈል፣
- በማስመሰል መጫወት፣

- የተለያዩ የተግባቦት መሣሪያዎችን በመረዳት እንደሁኔታው የሰዎችን ስሜት መረዳት፣ መግባባት፣ ወዘተ፣
- ከጊዜ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጽንሰ ሃሳብ (concepts) ለምሳሌ ዛሬ፣ ነገ፣ አምና፣ የሚቀጥለው ዓመት ወዘተ መረዳት፣
- ቀላልና ውስብብስብ ትዕዛዝን በመጠቀም መረዳት፣
- የሰዎችን የስሜት ዓይነቶችና ትርጉማቸውን መለየት፣
- የሰዎችን ዝምድና፣ የሃሳብ ቅደም ተከተል፣ የሁኔታዎችን ቅደም ተከተል ወዘተ ግንኙነትና ምንነት መረዳት፣
- የነገሮችን ባሕሪያት መለየት (ለምሳሌ አሉታዊ፣አዎንታዊ፣ ጠቃሚ፣ ጠቃሚ ያልሆኑ፣ ወዘተ መለየትና መጠቀም)፣
- የራስን ተግባርና እንቅስቃሴ በመቆጣጠርና በመገምገም ማስተካከል።

### 4.2.4. በመማር-ማስተማር ሂደት ወቅት የሚፈጠሩ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው

#### 4.2.4.1. ክፍል ውስጥ የመግባት ፍላጎት አለመኖር

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ትምህርት ቤት የመግባት ፍላጎት የላቸውም። ይህ ችግር የሚከሰተው ከሚከተሉት በአንዱ ወይም ተደራራቢ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል። ተማሪው/ዋ/ በትምህርት ቤት የሚስደስተው/ታት/ ነገር አለመኖር፤ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ መሥራት/ ማድረግ የማይፈልገው/የማትፈልገው/ ነገር ሊኖር ይችላል። ወይም ከቤተሰብ ተለይቶ/ታ/ ላለመዋል፤ ወይም ሌላ ችግር (ለምሳሌ በዕለቱ ያጋጠመው የስሜት መረበሽ፣ በቤት ውስጥ የተለመዱ እንቅስቃሴዎች፣ መንገድ መቀየር ወዘተ. )ሊሆን ይችላል።

**የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- ተማሪውን/ዋን በትምህርት ቤት ያሉ የሚያውቃቸውን ሰዎች፤ የተለመደ የሚያስደስት ተግባር ወዘተ ማስታወስና ማነሳሳት፤
- ተማሪው/ዋ ትምህርት ቤት ሲገባ/ስትገባ በሚወደው ነገርና በፍቅር መቀበል፤
- ተማሪው/ዋ ትምህርት ቤት ገብቶ በክፍል ውስጥ ወይም ሌላ ቦታ አንድ ነገር ከቤት እያመጣ/መጣች እንዲያስቀምጥ/ድታስቀምጥ ማድረግና ሽልማት መስጠት፤
- የመጀመሪያውን ክፍለ ጊዜ ተማሪውን/ዋን በሚያስደስት ወይም ተማሪው/ዋ በሚወደው/ምትወደው ነገር መጀመር፤
- ወላጆችና ት/ቤቱ በተማሪው/ዋ የትምህርት ቤት ችግርና መፍትሔዎቻቸው ላይ አብረው እንዲሰሩ ማድረግ፤

- ወላጆችና ት/ቤቱ  የመረጃ ልውውጥ ዘዴ (communication book) በመጠቀም የተማሪውን/ዋን ችግሮች ለመቀነስና ብሎም ለማስወገድ የተለያዩ የመማር-ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም::

4.2.4.2. **ከክፍል የመሸሽ** (running away) **ችግር**

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ቢገቡም ከመምህራን መሸሽ ሊፈልጉ ይችላሉ። የችግሩ መንስዔዎች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ ሌሎች ሮጠው ሲይዛቸውና ሲያባብሏቸው ለመደሰት፣ ሰዎችን በመቃወም ድርጊት ለመርካት፣ በመሮጥ በሚገኝ የደስታ ስሜት፣ በክፍል ውስጥ የሚሰጥ ተግባርን ላለመሥራት ዕድል ለማግኘት፣ በት/ቤት ውስጥ በሚያስደስተው አካባቢ ወይም ነገር ላይ ለመቆየት መፈለግ፣ ወይም ሌላ ችግር ሊሆን ይችላል።

**የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- በቅርብ ርቀት በመከታተል ተማሪው/ዋ እንዳይሮጥ/ትሮጥ መከላከል፣
- ተማሪው/ዋ በእጆቹ/ቿ አንድ የሆነ ነገር ይዞ/ዛ እንዲሄድ/ድትሄድ ማድረግ (በእጅ የሚያዘው ነገር ተማሪዎቹን የማይጎዳ  መሆን አለበት)፣
- የመሮጥ ውድድር ደንብ በማውጣት መጠቀም፣
- መሮጥ የሚቻለው መቼና ለምን እንደሆነ ማስተማርና ህግ ሲያከብር/ስታከብር ደግሞ ማበረታታት፣
- ተማሪው/ዋ ሮጦ/ጣ ከሄደ/ች በኋላ ሄዶ/ዳ ማግኘት የሚፈልጋቸውንና /ምትፈልጋቸውንና የሚወዳቸውን/ምትወዳቸውን ነገሮች በክፍል አካባቢ ማድረግ (የሚቻል ከሆነ)፣
- የተማሪው/ዋ የመሮጥ ችግር ሲቀንስ ወይም የተሰጠውን/ጣትን ህግ ሲያከብር/ስታከብር ማበረታታት  (ሽልማት መጠቀም)::

4.2.4.3. **ክፍል ውስጥ በአንድ ነገር ላይ ትኩረት የማድረግ ችግር (ህፀፀ ጥሞና)**

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ክፍል ውስጥ በአንድ ነገር ላይ ትኩረት የማድረግ ችግር አለባቸው:: ለዚህ ችግር መከሰት የተለያዩ ምክንያቶችን ማንሳት ይቻላል:: በተፈቀደላቸው ቦታ በመቀመጥ የሚሰጣቸውን ተግባር አለመሥራት፣ በክፍል ውስጥ በሚገኝ አንድ ነገር በመመሰጥ (ለምሳሌ በድምፅ፣በእንቅስቃሴ፣በመብራት፣ ወዘተ) የተሰጣቸውን ተግባር አለማከናወን ሊሆን ይችላል።

**የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- ተማሪውን/ዋን ክፍል ውስጥ በቅደም ተከተል መከናወን ባለባቸው ተግባራት ዙሪያ ማለማመድ፣
- ተማሪው/ዋ በቅደም ተከተል የሚሠሩ ተግባራትን ዝርዝር ይዞ/ዛ እንዲገባ/ድትገባ ማድረግ፣
- ለተማሪው/ዋ አስደሳች የሆኑ ተግባራትን በቅደም ተከተል ማቅረብ፤
- በቅርብ ርቀት በመከታተል ተማሪው/ዋ በተመደበበት/ችበት ቦታ እንዲቀመ/ድትቀመጥ ማድረግና ተግባሩን/ሯን ሲያከናውን/ስታከናውን ማበረታታት፣
- ለተማሪው/ዋ የክፍል ውስጥ አቀማመጥና ሌሎች ቁሳቁሶችን ተመሣሣይ ማድረግ (ከተቻለ የተማሪውን/ዋን ትኩረት የሚስብ የተለየ ነገር እንዳይኖር ማድረግ)፣
- ተማሪው/ዋ ወደ መቀመጫው/ጫዋ በቀጥታ ሄዶ/ዳ እንዲቀመጥና/ድትቀመጥና ወደ ተፈላጊው ተግባር እንዲገባ/ድትገባ የልምምድ ተግባር ማሠራትና ተግባሩን/ሯን ሲያከናውን/ስታከናውን ማበረታታት፡፡

4.2.4.4. **ተረጋግቶ በመቀመጥ ትምህርትን መከታተል ያለመቻል ችግር**

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተረጋገቶ በመቀመጥ ትምህርት የመከታተል ችግር አለባቸው:: የመምህራንን ትዕዛዝ አለመቀበል፣ በሥርዓት የሚሠራ ተግባር አለማከናወን፣ ያለ በቂ ምክንያት በክፍል ውስጥ መዟዟር፣ በአጠገባቸው የሚንቀሳቀስ ተማሪ ካለ ወይም ተግባራቸውን የሚቃወም ካለ የመጮህ ወይም የመሮጥ ባሕሪይ፣ ወዘተ ችግር አለባቸው:: ለእነዚህ ችግሮች መከሰት የተለያዩ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል:: ለምሳሌ መታዘዝ አለመፈለግ ወይም ሥራ መሥራትን አለመፈለግ፣ የሚሸት ነገር (ለምሳሌ ሽቶ፣ ቡና ወዘተ) በክፍል ውስጥ ካሉ መቃወም (ጥላቻ)፣ አንድ ነገር መሥራት ወይም ማድረግ ምን ውጤት እንዳለው አለመገንዘብ፣ ወይም ሌላ ችግር ሊሆን ይችላል፡፡

**የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- ተማሪዎቹን በሚያስደስቷቸው ተግባራት ወይም ጨዋታዎች ትምህርቱን መጀመርና ተግባራዊ ሲያደርጉ ማበረታታት፣
- ሌሎች ሰዎች በተማሪው/ዋ አጠገብ ሆነው መሥራትን ተማሪው/ዋ የሚቃወም/ምትቃወም ከሆነ ተማሪውን/ዋን ቀስ በቀስ በመቅረብ ማለማመድ፣
- ተማሪው/ዋ የሚፈለገውን ተግባር ሲያከናወን/ስታከናውን የሚያስደስተውን/ታትን ተግባር ወይም ሌላ ነገር በመፍቀድ እንደማበረታቻ መጠቀም፣

- ተማሪው/ዋ የሚፈለገውን ቀላል ተግባር ሲያከናወን/ስታከናውን ቀስ በቀስ የተግባሩን ክብደትና የመሥራት ደረጃ በመጨመር የማበረታታትን ተግባር መቀጠል፡፡

#### 4.2.4.5. የቤት ሥራና ሌሎች የተሰጡ ተግባራን ለመስራት ፍቃደኛ ያለመሆን ችግር

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የቤት ሥራና ሌሎች የተሰጡ ተግባራትን ላለመስራት የመቃወም ችግር አለባቸው፡፡ ለምሳሌ የተሰጡ ተግባራትን ለማከናወን ፍቃደኛ አለመሆን፣ ቢሰራም በጥራትና በጊዜ አለመስራት፣ ለሚሰጠው ውጤት ወይም ሽልማት ግድየለሽ መሆን፣ ወዘተ ችግሮች ይታይባቸዋል፡፡ ለዚህ ችግር መከሰት የተለያዩ ምክንቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ የተሰጡ ተግባራትን የማከናወን ጥቅምና ጉዳት አለመረዳት፣ የተሰጡ ተግባራትን ከማከናወን ይልቅ በሌላ በሚያስደስታቸው ተግባር መሳተፍን እንደ ዋና ተግባር መቁጠር፣ የተሰጡ ተግባራትን ማከናወን ሌሎችን የሚያስደስት ወይም የሚያስከፋ መሆን አለመሆኑን አለመረዳት፣ (የትምህርት ተግባራት በት/ቤት እንጂ በቤትም የሚከናወኑ መሆኑን አለመረዳት) ወይም በሌሎች ምክንያቶች ሊሆን ይችላል፡፡

**የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- የሚሰጡ ተግባራትን በተማሪዎች የዕውቀትና ክህሎት ደረጃ ማመጣጠን፣
- የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል (learning style) በመጠቀም ተግባራትን እንዲያከናውን ማበረታታት፣
- የቤት ሥራቸውን ከወላጅ ጋር በመተባበር እንዲሠሩና እንዲበረታቱ መርዳት፣
- ተማሪዎች መማር ወይም ማሻሻል የሚፈልጉትን በማጥናት በውሳኔው ማሳተፍ፣
- ተማሪዎች በራስ የመተማመን መንፈስ እንዲያሳድጉ ማበረታታት፣
- በቤት ሥራ ተግባራት ክንውን ተሳትፎ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን በመፈተሽ ማስወገድ ወይም መቀነስ፡፡

#### 4.2.4.6. አንድን ተግባር ሳያቋርጡ በትኩረት የመሥራት ወይም መከታተል (perseverates) ችግር

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አንድ ነገርን ሳያቋርጡ በትኩረት መሥራት ወይም የመከታተል ችግር ይታይባቸዋል፡፡ (ለምሳሌ የአሻንጉሊት ጎማ ማሽከርከር፣ ፊሽካ መንፋት፣ ወዘተ) በተከታታይና ያለማቋረጥ ያከናውናሉ፡፡ ለዚህ ችግር መከሰት የተለያዩ ምክንቶችን ማንሳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማፈራረቅ መሥራት አለመቻል፣ አንድ ተግባር ላይ ትኩረት ማድረግ የደስታ ስሜት ስለሚፈጥርላቸው የማያስደስታቸውን ተግባር ለማድረግ ወይም በሌሎች ምክንያቶች ሊሆን ይችላል፡፡

**የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- ተማሪው/ዋ ያለ ማቋረጥ የሚጫወተውን/ምትጫወተውን ወይም የሚሠራውን /ምትሠራውን ተግባር ካከናወነ/ች በኋላ ሌሎች የተለያዩ የጨዋታ ዓይነቶችን እንዲማር/ድትማር ማድረግ፣
- በተማሪው/ዋ የተለያዩ የጨዋታ ዓይነቶች የመጫወት ችሎታና ፍላጎት መሠረት የጨዋታ ዓይነቶችን ከቀላል ወደ ከባድ ደረጃ በደረጃ ማሳደግ፣
- በተማሪው/ዋ በብዙ አቻዎች የሚዘወተሩ ጨዋታዎችና ተግባራትን ተማሪው/ዋ እንዲለማመድ/ድትለማመድ ከተማሪው፣ ከወላጅና ከአቻዎች ጋር በትብብር መሥራት፣
- መጫወቻውን ለማበረታቻ (reinforcement) መጠቀም::

**4.2.4.7. በአዋቂዎች ላይ ጥገኛ የመሆን ችግር (dependency on adults)**

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች በአዋቂዎች ላይ ጥገኛ ሊሆኑ ይችላሉ:: ለምሳሌ መምህር እስካለ ድረስ መማር/መከታተል ነገር ግን ከዓይናቸው ወይም ከአጠገባቸው ሲርቅ አለመማር/አለመታዘዝ/መቃወም:: የዚህ ችግር መንስዔዎች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ፡- ተማሪዎቹ ከመምህሩ በስተቀር ሌሎች ሰዎችን አምኖ ያለመቀበል ችግር፣ ተማሪዎቹ ከለመዱት ሰው ውጪ የሌሎች ሰዎችን ቋንቋና አቀራረብ መልመድ አለመቻል፣ ከአንድ ለምሳሌ ከመምህሩ ብቻ እንጂ ከሌላ ሰው ጋር ለመቅረብ የራሱ የሆነ ውሳኔ ወይም ህግ እንዳለው የማሰብ ወይም ሌላ ችግር ሊሆን ይችላል።

**የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- ተማሪው/ዋ የለመደው/ችው አዋቂ ሰው (መምህር) በተማሪው አካባቢ በተለያየ አቅጣጫ እንዲቀሳቀስ በማድረግ ቀስ በቀስ ከዕይታና ከቅርበት መራቅን ማለማመድ፣
- ተማሪውን/ዋን በትንንሽ ቡድኖች ውስጥ በማሳተፍ በትብብር የማስተማር(cooperative learning strategies ) ዘዴዎች እንዲማር/ድትማር ማበረታታት፣
- ተማሪው/ዋን አንድን ተግባር በሚፈለገው መልኩ ሲያከናወን/ስታከናውን የለመደው/ችው ሰውም ሆነ ሌሎች ማበረታቻ እንዲሰጡ በማድረግ የተለያዩ ሰዎችን ቋንቋና አቀራረብ እንዲማር/ድትማር ማበረታታት፣
- የተማሪው/ዋ አቻዎችን እንደ ሞዴል በመጠቀም በአዋቂዎች ላይ አለመጠን ጥገኛ መሆንን አለማበረታታት (discouraging dependency on adults)፣
- ተማሪው/ዋ እርዳታ ሲፈልግ/ስትፈልግ ከሌሎች አዋቂዎችና ከአቻዎቻቸው እንዴት እገዛ (support) ማግኘት እንደሚችል/ምትችል ማስተማር::

4.2.4.8. **ከአንድ ተግባር ወደ ሌላ ተግባር የሚደረግ ሽግግርን መቃወም** (problems related with transition from one activity to another activity)

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ከአንድ ተግባር ወደ ሌላ ተግባር ሽግግር ትዕዛዝ ሲኖር የመቆጣት ወይም የመቃወም ባሕሪይ ይታይባቸዋል:: የዚህ ችግር መንስዔዎች ሊለያዩ ይችላሉ። ለምሳሌ የተጀመረውን ተግባር ካላለቀ ሌላ አዲስ ተግባር መጀመር ከባድ እንደሆነ ማሰብ፣ ወደ ሌላ ተግባር መሸጋገርን አስፈሪ ተግባር አድርጎ ማየት፣ ወይም ወደ ሌላ ተግባር መሸጋገር ከሌሎች ጋር ያለመስማማትን ወይም ጥላቻን ያመጣል ብሎ ማሰብ (ከልማድ የመጣ ሊሆን ይችላል፣ ወይም ከሚቀየረው ተግባር ወይም አካባቢ ጋር ያለመመጣጠን ችግር (ለምሳሌ የመንቀሳቀስ፣ የማሽከርከር፣ የመፃፍ ወዘተ፣ ተግባራት ሊያስቸግሩ ስለሚችሉ) ወይም ሌላ ችግር ሊሆን ይችላል።

**የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- ተማሪው/ዋ የተግባራት ክንውን የጊዜ ሰሌዳ እንዲጠቀም/ድትጠቀም ማስተማር፣
- ከተግባር ወደ ተግባር ሽግግርን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የሽግግር እንቅስቃሴዎችንና ቁሳቁሶችን መጨረስ፣ ማንሳት፣ ወዘተ፣ ምልክት በማሳየት የሽግግር ወቅት መሆኑን ለተማሪው/ዋ ማሳወቅ፣
- ራስን በመቆጣጠር ለተግባራት ሽግግር ዝግጁ የመሆን ዘዴን ለተማሪው/ዋ ማስተማር (ከባለሙያዎች ለምሳሌ ከመምህራንና ካውንስለሮች ጋር መሥራት)፣
- ከተግባር ወደ ተግባር ሽግግርን ለተማሪው/ዋ በሞዴል ተማሪዎች ፣ ወዘተ ማስተማር፣
- በጨዋታ፣ በቤት ከቤተሰብ ጋርና በተለያዩ ቦታዎች ይህን ተግባር(የተግባራት ሽግግር) ከወላጆችና ከሌሎች ጋር በጋራ በመሥራት የተማሪውን/ዋን ክህሎት ማሳደግ።

4.2.5. **ተገቢ ሥነ-ፆታዊና ተያያዥ ጉዳዮች ዕድገት ችግር** (problems in sexuality)

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች/ልጆች ለምሳሌ የራሳቸውን የአካል ክፍል ጥቅምና ተግባር የመለየት ችግር፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ራስን በራስ በወሲብ የማርካት ተግባር (masturbation) ሊፈፅሙ ይችላሉ። ለዚህ ችግር መነሻው ብዙ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ በስሜት የመርካት ፍላጎት፣ ውጥረትን የማርገብ ፣ የመሰልቸት/ የድብርት ስሜት ለማቃለል፣ በቀጣዩ ምን መስራት እንዳለበት ያለማወቅ ችግር ሲያጋጥም፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል።

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- ሥነ-ፆታዊ የአካል ክፍልን (sexual organ) ጥቅምና ተግባር ማስረዳት፣

- ምን ዓይነት አከባቢና ጊዜ በመጠቀም ተማሪው/ዋ ተቀባይነት የሌለው ወሲባዊ ተግባር እንደሚፈፅም/ምትፈፅም ማረጋገጥ፣
- ለተማሪው/ዋ የማህበረሰቡን ሥነ-ፆታዊ (sexual) ደንብና ባህል መጠበቅ አስፈላጊነትን ማሳወቅ፣
- መምህራን ከወላጆች ወይም ከአሳዳጊዎች ጋር በመመካከር ስለ ሥነ-ፆታዊ (sexual behavior) የመማር-ማስተማር ዘዴ ዕቅድ ማውጣትና መተግበር፣
- የስሜት ውጥረት ወይም የድብርት ችግር ካለ ችግሩን ለማስወገድ ሌላ ምቹና ተስማሚ አማራጭ ተግባራትን በመጠቀም ተማሪውን/ዋን ማለማመድ፣
- በማህበረሰቡ ተቀባይነት ባለው መልኩ ወሲባዊ ተግባር የትና መቼ መፈፀም እንዳለበት ማስረዳት::

### 4.2.6. ከሁኔታዎች ጋር በመጣጣም የራስን ህይወት መምራት (developing adaptive/coping skills)

#### 4.2.6.1. ራስን በራስ የመምራት (self-direction and management) ዕውቀትና ክህሎትን ማሳደግ

አብዛኛዎቹ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ራስን በራስ የመመምራት (self-direction and management) ችግር ይኖርባቸዋል። የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ራስን በራስ የመምራት ክህሎት እንዲያዳብሩ ለማስቻል ባለሙያዎች የሚከተሉትን ራስን በራስ የመምራት ዘዴዎችን ተማሪዎቹ እንዲያዳብሩ ማስተማር ይኖርባቸዋል።

**የመማር - ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- ተማሪው/ዋ ያለማንም ድጋፍ ነገሮችን የመምረጥ ዕውቀትና ክህሎትን እንዲያዳብር/ድታዳብር ማስተማር፣
- ተማሪው/ዋ አስፈላጊ ቁሳቁሶችን የማግኘትና የመጠቀም ክህሎትን እንዲያሳደግ/ድታሳድግ ማለማመድ፣
- ተማሪው/ዋ በፍላጎት የመስማማትና የመምረጥ ክህሎትን እንዲያዳብር/ድታዳብር ማስተማር፣
- ተማሪው/ዋ ዓላማና ግብ የመወጠን ክህሎትን እንዲያሳደግ/ድታሳድግ ማድረግ፣
- ተማሪው/ዋ ጊዜን በአግባቡና በዕቅድ የመጠቀም ልምድ እንዲያዳብር/ድታዳብር ማድረግ፣

- ተማሪውን/ዋን ችግሮችን የመለየትና ለችግሮች መፍትሔ የመስጠት ስልት የማስተማር እንዲሁም፣የራስን ውስንነትና ችሎታን ለይቶ የማወቅ ብቃትን ማስተማር ይኖርባቸዋል፡፡

**4.2.6.2. ነገሮችን በደረጃ (label) በተመሳሳይ፣ በመጠን፣ ወዘተ፣ የመለየት ዕውቀትና ክህሎትን የማዳበር ዘዴዎችን ማስተማር**

**የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

**ለተማሪው/ዋ፣-**

- ለምሳሌ፡ ነገሮችን፣ ሰዎችን፣ ድምጽን፣ ስሜትን፣ ቀለማትን፣ ቁጥሮችን፣ ወዘተ በደረጃ መለየት፣
- መዘመር፣ የእንስሳትን ድምጽ በማስመሰል (ለምሳሌ የበግ ድምጽ፣ የውሻ ድምጽ፣ የሌሎችንም ድምጽ)፣ መናገር ወይም የመሙላት ዘዴ ማስተማር፡፡
- የጥያቄ መነሻ ቃላትን (Wh Questions) ለምሳሌ፣ ለምን፣ የት፣ ወዴት፣ እንዴት ወዘተ በመጠቀም መጠየቅና መመለስን ማስተማር፣
- ተመሳሳይ ነገሮችን፣ ተመሣሣይ ሥዕሎችን፣ ተቃራኒ ነገሮችን፣ ቁጥሮችን፣ ወዘተ ማዛመድ ማስተማር፣
- በመጠን፣ በቀለም፣ በባሕሪይና በጥቅም ወዘተ፣ የመለየት ዘዴን ማስተማር፣
- የነገሮችን ቅደም ተከተል ማስተማር፡፡ ለምሳሌ በመጠን ቅደም ተከተል፣ ወዘተ፣
- ቁጥርንና መጠንን ማስተማር፡፡ ለምሳሌ ብዙ፣ ትንሽ (ጥቂት)፣ ሁሉም፣ ምንም፣ መጠንን ወዘተ፣
- ማወዳደርና ማመጣጠንን ማስተማር፡፡ ለምሳሌ ትልቅ፣ትንሽ፣ ረዥም፣አጭር፣ ወዘተ
- አራቱን መሰረታዊ የሂሳብ ስሌቶችን ማስተማር፡፡

**4.2.6.3. ራስን የመንከባከብና የመጠበቅ ዕውቀትና ክህሎት ማሳደግ**

**የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

**መምህራን፣-**

- ምግብ በሰዓቱ መመገብ፣ ምግብ አብስሎ መብላት ወዘተ በማስተማር የተማሪውን/ዋን ዕውቀትና ክህሎት ማሣደግ፣
- የአለባበስ ሥርዓት ዕውቀትና ክህሎትን ማሣደግ፣
- የአመጋገብ ሥርዓት ዕውቀትና ክህሎት ማሣደግ፣
- የመፀዳዳት ሥርዓት ዕውቀትና ክህሎት ማሣደግ፣

- የግልና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ ዕውቀትና ክህሎትን ማሣደግ ይጠበቅባቸዋል::

**4.2.6.4. ለየዕለት-ተዕለት ህይወታቸው የሚያገለግሉ ዕውቀትና ክህሎትን ማሳደግ የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- የራሳቸውን ስም የመለየት ዕውቀትና ክህሎት ማስተማር፣
- የቀን አቆጣጠርና የተግባር ክንውን ሰሌዳ የመጠቀም ዕውቀትና ክህሎት ማስተማር፣
- መፀዳጃ ቤትን በምልክት መለየት፣የትራፊክ ምልክቶችንና ህጎችን ዕውቀትና ክህሎትን ማስተማር፣
- ካርታን በመጠቀም ነገሮችን የመለየትና የመጠቀም ዕውቀትና ክህሎትን ማስተማር፣
- የግብይት ሥርአት ማወቅና የማከናወን ዕውቀትና ክህሎት ማስተማር፣
- የገንዘብ ልውውጥ አጠቃቀም ዕውቀትና ክህሎትን ማስተማር፣
- የመለኪያ መሣሪያዎች ዓይነቶችና አጠቃቀም ዕውቀትና ክህሎት ማስተማር፣
- የትውልድ ቀንና ዘመን ወዘተ የመለየት ዕውቀትና ክህሎትን ማስተማር::
- በመጠየቅ (ለምሳሌ፣ ምግብ፣ ውሀ፣ ወዘተ) የማግኘት ክህሎትን ማሳደግ፣
- የመግባባት (የመደራደር/ የመስማማት፣ ወዘተ) ክህሎትን ማሳደግ፣
- ተቃውሞን በአግባቡ የመግለፅ (ለምሳሌ የታዘዙትን ያለመስራት፣ ወዘተ) ክህሎትን በማስተማር የተግባቦት ክህሎትን ማሳደግ፣
- አስተያየት የመስጠት/ የሚያምኑበትን የመግለጽ የተግባቦት ክህሎትን ማሳደግ፣
- ሰላምታ በመለዋወጥ የተግባቦት ክህሎትን ማሳደግ::

**4.2.6.5. የመዝናኛና የጊዜ ማሳለፊያ ዘዴዎችን የመጠቀም ዕውቀትና ክህሎት ማሳደግ የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- በሚወዱት የስፖርት ዓይነቶች ማሣተፍ፣
- በተለያዩ የሥነ ጥበብ ሥራዎች (ምሳሌ፣ ሥዕል፣ ሙዚቃ ፣ወዘተ ) ማሣተፍ፣
- በተለያዩ ትይዕንቶች(ምሳሌ ቲያትር፣ ሲኒማ፣የቴሌቪዥን ፕሮግራም፣ ወዘተ) ማሣተፍ፣
- የተለያዩ የጨዋታ ዓይነቶች ላይ (ለምሳሌ፡- ቪዲዮ፣ ኳስ ጨዋታ ወዘተ) ማሣተፍ፣
- ህግንና ደንብን ተከትለው ከአቻዎቻቸው ወይም ከሌሎች ጋር በመጫወት ራሳቸውን የማዝናናት ክህሎትን ማስተማር::

**4.2.6.6. በማህበረሰብ (community) ውስጥ የመሣተፍ ዕውቀትና ክህሎትን ማሳደግ የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- የማህበረሰብ/ህዝብ ትራንስፖርት አጠቃቀም ዕውቀትና ክህሎትን ማስተማር፣፣

- የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን መጠቀም። ለምሳሌ፣ የመዝናኛ ቦታ፣ ባንክ፣ቴሌፎን፣ የመድሃኒት መደብር፣ ወዘተ አጠቃቀም ዕውቀትና ክህሎትን ማስተማር፣
- የትራፊክ ህግና ደንብ መከተል ዕውቀትና ክህሎት ማስተማር፣
- በሆቴሎች(ሬስቶራንቶች) የምግብ ምርጫ፣ትዕዛዝ መስጠት፣ክፍያ ሥርዓት ወዘተ ዕውቀትና ክህሎትን ማስተማር።

### 4.2.7. የአካል እንቅስቃሴ ብቃትና የስሜት ህዋሳት አጠቃቀም ክህሎትን ማሳደግ

አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የአካል ብቃት ችግር ሊኖርባቸው ይችላል። መምህራን የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ክህሎትን በሚከተሉት ነጥቦች ላይ በማተኮር ለማስተማ መሞከር ይኖርባቸዋል።

**የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ**

- በአግባቡና በትክክል የመቀመጥ፣ የመጓዝ፣ የመዝለል፣ ክህሎትን ማሣደግ፣
- የሰውነት ክፍሎችን ሚዛን በመጠበቅ የመንቀሳቀስ ክህሎትን ማሣደግ፣
- የሰውነት ክፍሎች ሚዛን አጠባበቅና ጥንካሬ ክህሎትን ማሣደግ::
- ሁለንተናዊ የሰውነት እንቅስቃሴ (gross motor) ክህሎትን በማስመሰል (imitation) ማስተማር። ለምሳሌ የአይንና የእግርን (eye-foot coordination) እንቅስቃሴን በማቀናጀት ሁለንተናዊ የሰውነት እንቅስቃሴ ክህሎትን እንዲያዳብሩ ማድረግ፣
- የሰውነት ክፍሎች (fine motors) እንቅስቃሴ ክህሎት በማስመሰል (imitation) ማስተማር (ለምሳሌ የእርሳስ አያያዝና የአፃፃፍ ስልትን ማስተማር)፣
- የድምጽና የንግግር ክህሎትን በማስመሰል ማስተማር። ለምሳሌ፡ ድምጽን ቃላትን እና ሐረጋትን (phrases) ማስመሰል እንዲማሩ ማበረታታት፣
- ተከታታይነት ያላቸውን እንቅስቃሴዎች በማስመሰል(imitation) ማስተማር። ለምሳሌ፤ በመሮጥ በመጀመሪያ ቆም ማለት ከዚያም ምልክት ሲሰጥ መሮጥ፣
- ሥዕልና የመሳሰሉትን በማስመሰል በመሳል የአካል እንቅስቃሴ ክህሎትን እንዲያዳብሩ ማድረግ፣
- የእጅ ጽሑፍን በመጠቀም በተገቢ የጽሑፍ ዓይነቶች የመግባባት እውቀትና ክህሎትን ማዳበር ይጠበቅባቸዋል።

በተጨማሪም አንዳንድ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የስሜት ሕዋሳትን በመጠቀምና በማቀናጀት የመጠቀም ችግር ስለሚታይባቸው መምህራንና ባለሙያዎች፣

- ዓይን በሚያየው አቅጣጫ ሂዶ መያዝ ወይም መንቀሳቀስን ማስተማር፣
- ድምጽ በሚሰማበት አቅጣጫ ዞሮ በማየት የመረዳት ክህሎትን ማዳበር፣ እንዲሁም
- በስሜት ሕዋሳት ወደ አንጎል የሚሄድ መረጃን በማብላላት ትርጉም መስጠት፣ ወዘተ ክህሎትን ማዳበር፣
- አፍንና ሌሎች የንግግር ክፍሎችን በማሰልጠን መናገር የመቻል ክህሎትን ማዳበር፣
- የተለያዩ የመርጃ መሣሪያዎች ለምሳሌ (picture exchange communication system) ዘዴዎች በመጠቀም የተግባቦት ክህሎትን ማዳበር ማስተማር ይኖርባቸዋል፣
- የሰውነት ማጎልመሻ ተግባራትን በየዕለት ተግባራት ውስጥ በማካተት ተማሪዎቹን በየቀኑ ማሣተፍ።

# 5. አካቶ ትምህርት የኦቲዝም ችግር ላለባቸው ተማሪዎች

መጠነኛ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች እንደማንኛውም ሰው በመደበኛ ትምህርት ቤት የመማር ችሎታም ሆነ መብት አላቸው፡፡ በመሆኑም ትምህርት ቤቶች በአካቶ ትምህር አማካኝነት በፍላጎታቸውና ችሎታቸው መሠረት ማስተማር ይጠበቅባቸዋል፡፡ የአካቶ ትምህርት የኦቲዝም ችግር ላለባቸው ተማሪዎች በርካታ ጥቅሞችን ይሰጣቸዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል:-

- የትምህርት ቅስሞሽ መሻሻል (improvement in academic achievement)፣
- ከአቻዎቻቸው ጋር እንዲማሩ በማድረግ የማህበራዊና ተግባቦት ክህሎትን የማዳበር ዕድል ይሰጣቸዋል፣
- ለራሳቸው ያላቸው አመለካከት (self concept) ይሻሻላል፣
- የአድሎና መገለል (reduces stigma and discrimination) ችግርን ይቀንስላቸዋል፣
- የኦቲዝም ችግር የሌለባቸው ተማሪዎች ለኦቲዝም ችግር አዎንታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል፡፡

የጥናት ውጤቶች እንደሚጠቁሙት ከሆነ የኦቲዝም ችግር ካለባቸው ተማሪዎች መካከል የአዕምሮ ብስለት (cognitive ability) ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑትና በችሎታቸው ላቅ ያለ ተሰጥኦ ያላቸው ከአካቶ ትምህርት በተጨማሪ ልዩ ክፍልና የመርጃ ማዕከል ያስፈልጋቸዋል፡፡ ሆኖም ግን በመካከለኛ የአዕምሮ ዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በአካቶ ትምህርት ቢማሩ ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## 5.1. ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድን (daily lesson plan) መጠቀም

መምህራንና ባለሙያዎች ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ (daily lesson plan) ሲያዘጋጁ በአንክሮ ሊታሰብባቸው የሚገባቸው ጉዳዩች የሚከተሉተ ናቸው:-

- የተማሪውን /ዋን/ የመማር ፍላጎትና ችሎታ መሠረት በማድረግ የትምህርት አቀራረብና ማስተማር ዘዴዎችን ለመጠቀም ማቀድ፣
- ሊታዩ የሚችሉ የባሕሪይና ተያያዥ ጉዳዮች ለውጥን ለመቋቋምና የመማር-ማስተማር ሂደትን ምቹ የማድረጊያ ዘዴዎችን በታሳቢነት በመጠቀም ማቀድ፣
- ዕቅዱን ከባለድርሻ አካላት ጋር ለምሳሌ ወላጆች፣ የልዩ ፍላጎት መምህር፣ የሥነ-ልቦና ባለሙያ ወዘተ ጋር በጋራ ማቀድ (ከተቻለ)፣
- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር (Individualized educational plan) መጠቀም፡፡ ለምሳሌ:- ተማሪው /ዋ/ በከፍተኛ ደረጃ ለውጥ የሚያስፈልገው በማህበራዊ ክህሎት ችግር መዳበር ላይ ከሆነ/ች በዚህ ዙሪያ የነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሃ-ግብርን መጠቀም፣

- የተማሪውን /ዋን ውጥረት ወይም ፍርሃት ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ዕረፍት መስጠትን የዕቅዱ አካል ማድረግ፣
- የክፍልና የሌሎች ሥርዓትና ህግን በቀጥታ በተግባራዊ ምሳሌዎች ለማስረዳት ማቀድ፣
- የመማር ፍላጎትን  መሰረት በማድረግ በሚመቻቸው መልኩ ማቀድ ለምሳሌ፡ መፃፍ የማይችል ተማሪ በመቅረፀ ድምፅ እንዲማር ወይም ሌሎች ዘዴዎች መጠቀምን የዕቅዱ አካል ማድረግ፣
- መልካም ባሕሪይና ተፈላጊ ተግባራት ሲከናወኑ የማበረታት ሂደትን የዕቅዱ አካል በማድረግ ማቀድ።

## 5.2. የሥርዓተ ትምህርት ይዘትና የትምህርት ተግባራትን ማስማማት

የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የሥርዓተ ትምህርት ይዘትንና (contents) የትምህርት ተግባራትን የመረዳት ችግር ስለሚኖርባቸው ማስማማት (adaptation) ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር ነባራዊ ሐቅ (facts) ፣ ጽንሰ ሐሳብ (concepts) ፣ ሥርዓት (principles) ፣ አመለካከትን (attitudes) ወዘተ ማስማማት የግድ ይላል። ይዘትንና የትምህርት ተግባራትን በቀላሉ ለማስተማር የሚከተሉት ምሳሌዎች ጠቃሚ ናቸው።

- ተጨባጭ (concrete) የሆኑ ምሳሌዎችን መጠቀም፣
- በቀላሉ በሚነበብ መልኩ ማቅረብ፣
- በተደጋጋሚ አንድን ጽንሰ ሐሳብ ማስተማር፣
- ይዘትን በቀላሉ በሚያስረዳ መልኩ ለምሳሌ ቴፕሪኮርደር መጠቀም፣ ሥዕልና ፖስተሮችን መጠቀም፣ ቪዲዮ (video) እንዲመለከቱ በማድረግ ማስተማር፣
- የተማሪው/ዋ/ን የህይወት ዳራ (background information) በመጠቀም ማስተማር፣
- ተማሪው/ዋ/ መረዳት የማይ/ትችለው ይዘት ከሆነ በሌላ ተመጣጣኝ ይዘት መተካት ወይም በቀላል አቀራረብ ማቅረብ፣
- የትምህርቱን ይዘት መጠንና ብዛት በመቀነስ በቀላል አቀራረብ ማስተማር፣
- ተማሪው/ዋ/ መማር የሚገባውን/ትን ነገር በመቀነስ ቀስ በቀስ የትምህርት ቅስሞሽ መጠንን መጨመር።

## 5.3. የማስተማር ዘዴዎችን ማስማማት (differentiation of teaching stratgies)

መምህራን የተለያዩ የቡድን ትብብር የማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች በትምህርት ቅስሞሽ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይችላሉ። የአካቶ

ትምህርት መምህራን የሚከተሉትን የማስተማር ዘዴዎች በማስማማት እንደሁኔታውና እንደአስፈላጊነቱ መጠቀም ይገባቸዋል፡፡

- ሁሉም ተማሪዎች በንቃት እንዲሣተፉ ያለ ቡድን ወይም በጥንድ ቡድን ማስተማር፣
- አንድ - ለአንድ የማስተማር(አንድ መምህር አንድን ተማሪ በመርዳት የማስተማር ዘዴ)ዘዴን መተግበር፣
- ትንሽ የቡድን አባላትን አንድ ላይ በማድረግ ማስተማር፡፡ ይህ በትንሽ ቡድን የማስተማር ዓይነት ከሚከተሉት ውስጥ ሊመደብ ይችላል፡፡
    - ✓ ተመሣሣይ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች አንድ ላይ በማቧደን (same ability grouping)፣
    - ✓ የተለያየ ዓይነት ፍላጎት ወይም ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች አንድ ላይ በማቧደን (heterogeneous grouping)::

**ማስታወሻ፡-** የተለያዩ የቡድን (የጋራ) የማስተማር ዘዴዎችን በምንጠቀምበት ጊዜ ተማሪዎቹ የሚከተሉትን መመዘኛዎች መከተላቸውን መቆጣጠር ወይም መከታተል ይገባል፡፡

- እያንዳንዱ የቡድን አባል ለቡድኑ ትምህርት ዓላማና ግብ መሣካት የራሱን ድርሻ መወጣቱን፣
- እያንዳንዱ የቡድን አባል በቡድኑ የጋራ መማር ላይ ኃላፊነት መወጣቱን፣
- እያንዳንዱ የቡድን አባል በትብብር የመወያየት፣ ችግር የመፍታት፣ ወዘተ ተግባራት ላይ የራሱን ድርሻ መወጣቱን፣
- እያንዳንዱ የቡድን አባል በጋራ ሲማሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመለየት የራሳቸውን፣ አስተዋጽኦና የቡድንኑ አስተዋጽኦ መመዘን መቻላቸውን ወዘተ::

## 5.4. የተማሪዎች በጋራ የመማማር ዘዴዎችን ማስማማት (differentiation of students' co-operative learning)

እንደሌሎቹ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎችም በትምህርት ቅስሞሽ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉት በጋራ መማር ሲችሉ ነው፡፡ ለዚህም የተለያዩ በጋራ የመማሪያ ዘዴዎችን መተግበር ይቻላል፡፡ እነሱም፡-

- የአቻ መማማር ዘዴ (peer tutoring)፣
- እርስ በርስ በመረዳዳት መማማር ዘዴ (reciprocal teaching method) ፣
- በቡድን ችግር ፈቺ የመማማር ዘዴ (group problem solving method)፣ ወዘተ መጠቀም ናቸው፡፡

## 5.5. በጋራ (team) የማስተማር ዘዴዎችን (collaborative teaching methods) በማስማማት መጠቀም

በአካቶ ትምህርት ክፍል ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን በጋራ (በመተባበር) የማስተማር ዘዴዎችን ሊጠቀሙ ይገባል፡፡ በጋራ የማስማር ዘዴዎች ለመምህራን ብዙ ጥቅሞች ያስገኛሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

- ዕውቀትና ክህሎትን በመጋራት ለማስተማር፣
- የተለያዩ ለመማር ማስተማር የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ለመጋራት፣
- ለተማሪዎችና ለወላጆች በጋራ የመሥራት ምሳሌ ለመሆን ናቸው፡፡

ስለዚህ መምህራን ከተለያዩ የባለድርሻ አካላት ጋር እንደሁኔታውና አስፈላጊነቱ በጋራ የማስተማር ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር ይገባቸዋል፡፡ በመሆኑም፣

- ✓ ከልዩ ፍላጎት መምህራን፣
- ✓ ከወላጆች፣
- ✓ ከሥነ-ልቦና ባለሙያዎች፣
- ✓ ከተለያዩ ቴራፒስቶች (ለምሳሌ፣ የቋንቋና ንግግር፣ የተግባራት ልምምድ/occupational፣ ወዘተ) ጋር በጋራ መሥራት ይገባቸዋል፡፡

## 5.6. የመማር-ማስተማር አጋዥ (መርጃ) መሣሪያዎችን (teaching aids) ማስማማት

ሁሉም የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች እንደችሎታቸውና ፍላጎታቸው መማር እንዲችሉ የመርጃ መሣሪያዎችን ማስማማት ያስፈልጋል፡፡

ለምሳሌ፡-

- በቀላሉ እንዲነበብ ማጉላት (larger print) ፣
- በአካባቢ የሚገኙ ቁሳቁስ መጠቀም፣
- በድምጽ (spoken) የሚቀርብ ትምህርትን በጽሑፍም ጭምር ማስተማር፣
- በጽሑፍ ብቻ የሚቀርብ ከሆነ በመነካካትና በድምፅ (auditory) እንዲሰማ ሆኖ የሚቀርብበት ዘዴን መጠቀም፣
- የተለያዩ የመረጃና ግንኙነት ቴክኖሎጂ (information communication technology (ICT) ውጤቶችን በመጠቀም እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

የሚከተሉትን የዕይታ ማስተማሪያ ዘዴዎች (visual teaching strategies) መጠቀም፡-

- ሥዕልና ሌሎች የዕይታ መማሪያ ቁሳቁሶችን በመጠቀም መማር፣ መግባባት እና ራስን የመቆጣጠር (self- control) ዘዴዎችን መተግበር፣
- አላስፈላጊ ድምጽና የእይታ መርጃ መሣሪያዎችን አለመጠቀም ምክንያቱም የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ትኩረትን የሚሻሙ ነገሮች ስለሚረብሻቸው ነው፡፡ ለዚህም የግራፍ ምልከቶችን፤ ተጨባጭ የሆኑ በዕይታ የመማሪያ መሣሪያዎችን መጠቀም፡፡ ለምሳሌ ዕለታዊ መርሃ-ግብር፣ የተግባራት ቼክሊስት፣ የቀን አቆጣጠር መርሃ-ግብር፤ የመሳሰሉትን የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ባሉበት ክፍልና ት/ቤት አካባቢ ጉልህ ሆኖ በሚታይበት አካባቢ በመለጠፍ መጠቀም፡፡
- የክፍል ውስጥ ህግ፣ የተግባራት ክንውን ትዕዛዝ ወዘተ በዕይታ የመማሪያ ቁሳቁስ መርጃ መሣሪያዎች መጠቀም፡፡

**ማስታወሻ:-** የዕይታዊ መርጃ መሣሪያ የባሕሪይ ችግርን ለመቆጣጠር የሚረዱና (ለምሳሌ ህግና ሥርዓት፣ ሥዕላዊ መግለጫ ተገቢ ፣ ወዘተ) በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያላቸው ባሕሪያትን የሚያሣዩ መሆን አለባቸው፡፡

የሚከተሉትን የየቀኑ ተግባራትን (daily activities) የሚያሣይ ፕሮግራም በመተግበር:-

- የተማሪዎቹን የመሰልቸትና የመደበር(depression) ስሜትን የሚያስወግዱ ተግባራትን መጠቀም፣
- የተግባቦትን መርጃ መሣሪያ (augmentative communication tools) ዘዴ በመጠቀም የተግባቦት ክህሎት ማሳደግ፡፡ ይህ ተግባር በመምህራንና በወላጆች እንዲሁም በሙያው ዕውቀት ባላቸው ሰዎች ስምምነት መሠረት መሆን አለበት፡፡ ከተግባቦት መርጃ መሣሪያዎች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ የሰውነት እንቅስቃሴ ምልክትን (gesture) ለምሳሌ የጣት ምልክቶችን መጠቀም፣ የአይን እንቅስቃሴ ምልክት መጠቀም፣ ሥዕል (pictures) መጠቀም፣ ሌሎችንም ምልክቶች መጠቀም ፣
- የአጋዥ ቴክኖሎጂ ውጤት ለምሳሌ ጽሑፍን ወደ ንግግር የሚቀይር ቴክኖሎጂ፣ ወዘተ መጠቀም፡፡

## 5.7. የክፍል ውስጥ አካባቢን ምቹና ተስማሚ ማድረግ (classroom environment modification)

የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ አካባቢን ምቹና ተስማሚ በማድረግ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን የመማር-ማስተማር ዘዴዎች መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

- የማይቀያየሩ የዕቃዎችና ሌሎች መሣሪያዎች አቀማመጥን ማስተካከል፣
- መርጃ መሣሪያዎችና ሌሎች የመማሪያ-ማስተማሪያ ማቴሪያሎች ያለ ችግር እንዲያገኟቸው በሚያውቋቸው ቦታዎች ላይ ማስቀመጥ፣
- ከእነሱ ምን እንደሚጠበቅና በሚቀጥለው ድርጊት ምን እንደሚከሰት እንዲገምቱ ለማድረግ የክፍል ውስጥ አካባቢን ምቹና ተስማሚ ማድረግ ያስፈልጋል::

ከዚህ በተጨማሪ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የስሜት ህዋሳት ላይ ችግር የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን በማጤን የማስተካከያ ስትራቴጂዎችን መጠቀም:-

- የተማሪዎች እይታን(visual) የሚረብሹና የማይመቹ ሁኔታዎች ካሉ ማስተካከል፣
- የተማሪውን የእይታ ትኩረትን መቀያየር፣ መገንዘብና የእይታውን ትኩረት በሚስብ ደረጃ ማስተካከል፣
- የተማሪውን የመስማት (listening) ችሎታ የሚረብሹ ነገሮች ካሉ መለየትና ማስተካከል ወይም ማስወገድ፣
- የተማሪውን/ዋን የመስማት ትኩረት የመቀያየር ደረጃ በመለየትና ትኩረት በማድረግ የመስማት ክህሎት እንዲያሳድግ ማድረግ፣
- ግድግዳውንና አካባቢውን በአንድ አይነት ቀለም መቀባት ወይም በካርቶን ወይም በሌላ ነገር መሸፈን፣
- የእይታን ትኩረት የሚረብሹ ነገሮችን መቀነስ ወይም ከተማሪው እይታ በመከለል አስፈላጊ ሲሆን ብቻ መጠቀም፣
- የመጫወቻ መሣሪያዎችን ቁጥር መቀነስ እና ቀስ በቀስ በሌሎች መቀየር፣
- እይታን የሚያውክ ለምሳሌ የፍሎረሰንት አምፑል የሚሰጠውን ብርሃን መቀነስ ወይም ሌላ ተስማሚ የሆነ የብርሃን ምንጭ በመጠቀም ክፍልን ወይም አካባቢን ተስማሚና እርጋታ ያለው ማድረግ፣
- ተማሪውን/ዋን ተስማሚ በሆነ የክፍል ውስጥ አካባቢ ማስቀመጥ፣
- የድምጽ ሁከት የሚፈጥር ነገርን መቀነስ፣ ለምሳሌ በመጋረጃ፣ ድምጽን መቀነስ በሚያስችል ነገር በመከላከል፣ ወዘተ ድምጽን መቀነስ፣
- በእያንዳንዱ የመማሪያና በሌሎችም አካባቢዎች ተማሪው ዘና የሚልበትን ሁኔታ፣ መፍጠር:: ይኸውም የመጫወቻ ቦታ መፍጠር፣ የመዝናኛ ቦታ ማመቻቸት፣ ፀጥታ የሰፈነበታ ቦታ መጠቀም፣ ወዘተ::

- ተማሪው/ዋ ነገሮችን በመነካካት (tactile learning) የመማር ዝንባሌ ማሳደግ:: ነገሮችን በመነካካት አላስፈላጊ ባሕሪያትን የሚያሣይ ከሆነ ጥንቃቄ ማድረግና ትኩረት የሚስቡ ነገሮችን ማስወገድ፣
- የመማሪያ ተግባራትን (learning activities) በተማሪው የመረዳት አቅም ደረጃ (level of understanding) ማቅረብ፣
- የመማር-ማስተማር ተግባራትን (teaching-learning activities) በአጭርና ለተማሪው ትርጉም በሚሰጥ መልኩ ማስተካከል፣
- ተጨባጭና ተግባራዊ የሆኑ ምሳሌዎችን መጠቀም:: ምሳሌ ስንጠቀም አዲስ ነገር ለማሳወቅ አዲስ ባልሆነ አካባቢ መጠቀም፣
- አዲስ ተግባርና አዲስ አካባቢ ከሆነ የእይታና ሌሎች የመርጃ መሣሪያዎችን በመጠቀም ማሳወቅ/ ማስተማር፣
- ተማሪው/ዋ ልዩ ተሰጥኦ ካለው/ላት ተሰጥኦውን በመለየት ማበረታታትና በተሰጥኦው/ዋ ዙሪያ ባለሙያ በማማከር ተሰጥኦውን/ዋን እንዲያሳደግ/ድታሳድግ ማስተማር::

## 5.8. በመማር ማስተማር ሂደት በጋራ የመሥራት ዘዴዎች (cooperative learning methods) መጠቀም

- በጋራ (teamwork) የመሥራት ዘዴን ማበረታታት:: ለምሳሌ በጋራ ሲሰሩ አንዱ የቡድን መሪ፣ ሌላው ፀሐፊ፣ ሌላው አቅራቢ፣ ወዘተ ሆነው ሁሉም እንዲሣተፉ ማድረግ፣
- በቡድን ማስተማር ጊዜ የቡድን አባላት ቁጥር ቢበዛ ከ5 እስከ 7 እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ተማሪዎቹ ምን ምን መማር እንዳለባቸውና የመማር ዘዴዎችን በጽሑፍና በቃል ማቅረብ፣
- በተቻለ መጠን የሚማሩትን ተግባር መጠንና ክብደት ተመጣጣኝ ማድረግ፣
- የሚማሩትን ተግባር መጠን መቀነስና የሚሠሩ ተግባራትን በትንንሽ ክፍሎች በመክፈል ደረጃ በደረጃ ማስረዳት፣
- አዳዲስ ጽንሰ ሐሳቦችና ተግባራትን በሚያውቁት ዕውቀትና ክሂሎት በመጀመር የተለያዩ የማስረዳት ዘዴዎችን በመጠቀም ማስረዳት፣
- አስፈላጊ የሆነ ዕውቀትና ክህሎት በመጠቀም ማስተማር:: ለምሳሌ፣ የአቻ ለአቻ ትምህርት (peer tutoring)፣ የባለሙያዎች /ስፔሻሊስቶችን (specialists) ወዘተ ምክርና አገልግሎት ማግኘት፣

- የተለያዩ የመርጃ መሣሪያዎችን በጋራ መጠቀም፣
- የጊዜ ሰሌዳና የተግባራት ክንውን ቻርት(chart) በመጠቀም የተሰጡ ተግባራትን እንዲያከናውኑ መርዳት፣
- መማር የማይፈልጓቸውን የትምህርት ዓይነቶች በግድ አለማስተማር:: (ለምሳሌ፡ ሙዚቃ፣ ስፖርት፣ ወዘተ ሊሆን ይቻላል):: መማር የማይፈልጓቸውን የትምህርት ዓይነቶች ደረጃ በደረጃ እንዲወዱት ዕገዛ ማድረግ::

## 5.9. የተማሪዎችን የትምህርት ቅስሞሽ ምዘናን ማስማማት

ተማሪዎቹ ያመጡትን የትምህርት፣ የባሕሪይ፣ የማህበራዊ፣ የአመለካከትና የተግባቦት ለውጦች በምዘና ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ለዚህም የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን መጠቀም የግድ ይላል:: የምዘና ውጤት ለተለያዩ ተግባራት እንዲውሉ ተደርገው መሠራት አለባቸው:: ከብዙ በጥቂቱ:-

- የመማር-ማስተማር ሂደትን ለማሻሻል፣
- ለተማሪዎችና ለወላጆች ስለተማሪዎቹ የትምህርት ውጤት መረጃ ለመለዋወጥ፣
- በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የዓላማና ግብ ስኬት ሁኔታን ለመተንተን፣
- እያንዳንዱ ተማሪ በምን ዓይነት ሁኔታ ቢማር የተሻለ የትምህርት ቅስሞሽ ሊኖር እንደሚችል ለመረዳት፣
- የነፍስወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብር (individualized educational program) ለማዘጋጀትና ለመተግበር ይጠቅማል::

የተማሪዎችን የትምህርት ቅስሞሽ ለመመዘን የተለያዩ ዘዴዎችን በማስማማት መጠቀም ይቻላል:: ለምሳሌ:-

- በግብረ-መልስ (feedback)
- በተከታታይ ምዘና (ለምሳሌ በሙከራ፣ ድንገተኛ ፈተና(quiz)፣ የቤት ሥራ፣ የክፍል ሥራ፣ ወዘተ)፣
- በምልከታ (ለምሳሌ በተናጠል ተግባር፣ በጋራ ተግባር፣ ወዘተ)
- የተለያዩ የምልከታ ዘዴዎችን በመጠቀም መመዘን:: ለምሳሌ ቼክሊስት (checklist) መጠቀም፣
- የቀን ተቀን (የየዕለት) ተግባራትን በማሰባሰብ (portfolio) መመዘን፣
- የተማሪው/ዋ/ አቻዎች መረጃዎችን በመጠቀም መመዘን፣
- ተማሪው/ዋ/ በመማሩ /ሯ/ የመጣውን ለውጥ ራስን በራስ እንዲመዝን (ትመዝን) የማድረግ ዘዴን በመጠቀም፣

- በየጊዜው የሚሠሩ ተግባራትንም ውጤት መሰብሰብና መተንተን፣
- ከመጠን ይልቅ በጥራት ላይ ትኩረት ማድረግ፣
- በአመታት በሚለካ መማር ላይ ሣይሆን በግለሰቡ የዕለት ተዕለት ሁለንተናዊ ዕድገት ለውጥ ላይ ትኩረት ማድረግ፣
- ግልጽና ቀላል ምሳሌዎችን በማሣየትና በማለማመድ ተማሪውን በመማር ለውጥ መመዘን:: ለምሳሌ የተማሪውን አካዳሚክ፣ የባሕሪይ፣ የአመለካከት ለውጥ መኖር አለመኖሩን መመዘን፣
- በአቻዎች የምዘና ዘዴን መጠቀም፡፡ ለምሳሌ አቻዎች የተማሪውን አካዳሚክ፣ የባሕሪይ፣ የአመለካከት ለውጥ መኖር አለመኖሩን በቃለ-ምልልስና በሌሎች ዘዴዎች የምዘና ዘዴ መጠቀም፣
- አማራጭ የምዘና ዘዴዎች(alternative assessment methods) መጠቀም፡፡ ለምሳሌ እንዲያሣዩ ማድረግ፣ ቪዲዮ ሪኮርደር (video recorder)፣ ካሜራ (camera)፣ ቴፕ ሪከርደር (tape recorder) ወዘተ መጠቀም፣
- በምዘና ወቅት እረፍት የሚያስፈልጋቸው ከሆነ የእረፍት ሰዓት መስጠትና ተግባሩን ቀስ በቀስ እንዲጨርሱ ማድረግ፣ አስፈላጊ የሆኑ መርጃ መሣሪያዎችና ፍንጭም በመስጠት መመዘን፡፡

## 6. የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሐ ግብር መጠቀም (Individualized Educational Program)

የነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሐ ግብር (IEP) ማለት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎችን እንደየችሎታዎቻቸው ፍላጎቶቻቸው ለማስተማር የሚያግዝ ሰነድ ነው፡፡ ሰነዱ፣ የትምህርቱን ዓላማ፣ ግብ፣ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ጥቆማ፣ የምዘና አጠቃቀምን፣ መርጃ መሣሪያዎችን ያካተተ ነው፡፡ እያንዳንዱ የኦቲዝም ችግር ያለበት ተማሪ እንደ ችሎታውና ፍላጎቱ እንዲማር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡ ለዚህም ተግባር የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሐ-ግብር መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሐ ግብር ለተለያዩ ተግባራት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ለምሳሌ፡-

- የእያንዳንዱን ተማሪ ፍላጎትና ችሎታ መሠረት በማድረግ ለማስተማር፣
- የእያንዳንዱን ተማሪ በፍላጎትና በችሎታ መሠረት የመማር መብት ያስከብራል፣
- መምህራንና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ያላቸውን ቁሳቁስና ባለሙያ በመጠቀምና ተጨባጭ ተግባር በማከናወን እያንዳንዱ ተማሪ እንዲማር ለማድረግ ይረዳል፣
- የተማሪዎች የክፍል መድገምና መጠነ ማቋረጥን ይቀንሳል፣
- መምህራንና ወላጆች የራሳቸውን ድርሻ በመወጣት ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸውና ችሎታቸው እንዲማሩ ያግዛል፣
- የተለያዩ የነፍስወከፍ ትምህርት መርሀ-ግብር አባላት (ባለድርሻ አካላት) እውቀት፣ ክህሎት፣ ሪሶርስና ሌሎች ነገሮችን በመካፈልና የልምድ ልውውጥ በማድረግ በጋራ እንዲሠሩ ያግዛል፡፡

### 6.1. የነፍስወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብር እንዴት ታቅዶ ይከናወናል?

የነፍስወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብርን አቅዶ ለመተግበር የተለያዩ ደረጃዎችን ያካተተ ተግባር ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ ይኸውም፣

- የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎችን ጠንካራ ጎን፣ ደካማ ጎን፣ ለመማር-ማስተማር እንቅፋትና ምቹ የሆኑ ሁኔታዎችን፣ ወዘተ ለይቶ ለማወቅ፣
- ለመለየቱ ተግባር ከመምህራን፣ ከወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ከትምህርት ቤቱ አመራር አካላት፣ ከተማሪዎች/ የክፍል አቻዎች፣ ወዘተ መረጃ መሰብሰብ ያስፈልጋል፡
- መረጃው ከተሰበሰበ በኋላ  የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብር ቡድን አባላት መመሥረት ያስፈልጋል፡ አባላቱም ከወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ከመደበኛ ትምህርት መምህራን፣ ከልዩ ፍላጎት/ተንቀሳቃሽ መምህር፣ ከተማሪው/ዋ/፣ ከት/ቤቱ አመራር

አባላት፣ ቴራፒስቶች(therapists)፣ የትምህርት ቤቱ ጋይዳንስ ካውንስለር፣ የት/ቤቱ የማህበራዊ ተግባራት ባለሙያ (social worker)፣ ወዘተ መሆን አለበት::

- የነፍስወከፍ ቡድን የትምህርት መርሃ-ግብር አባላት ስብጥር ከኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪ ችሎታ፣ ፍላጎት፣ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ወዘተ ሊለያይ ይችላል።
- በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ቡድኑ ከተመሠረተ በኋላ የመርሃ-ግብር ዕቅድ ማውጣትና መተግበር ይጠበቃል። ዕቅዱ በአንድ የተለየ የመማር-ማስተማር ተግባር ላይ ማተኮር ይኖርበታል። ለምሳሌ የተማሪዎቹ ዋነኛው ችግር የተግባቦት ችግር ከሆነ ይህን ችግር ደረጃ በደረጃ ለመፍታት ማተኮር አለበት። በዚህ ጊዜ ሌላ ነገር በማቀላቀል የዕቅድና ተግባርን ውጤታማነት ማበላሸት አይገባም። ለምሳሌ የተግባቦት ችግር ላይ እናተኩራለን ብለን የማህበራዊ መስተጋብር ችግርን ወይም የባህርይ ችግር አብረን ለመፍታት/ለመቀነስ ብለን መሥራት አይገባም። እነዚህ ችግሮች ለየብቻቸው በዕቅዱ መሠረት መከናወን መቻል አለባቸው።

## 6.2. የነፍስወከፍ ትምህርት መርሃ-ግብር ቡድን አባላት የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

### 6.2.1.ተማሪው/ዋ/

- የነፍስወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብር አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ራሱ/ራሷ ተማሪው/ዋ/ የቡድኑ አባል መሆን ይኖርበታል/ባታል። ተማሪው/ዋ የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጣ/ድትወጣ ቡድኑ መንቀሳቀስ ይገባዋል።
- ስለራሱ/ራሷ/ አጠቃላይ ሁኔታ ግብዓት ሊሆን የሚችል መረጃ በመስጠት፣
- በመርሃ ግብሩ ዕቅድ ክንውን ውሳኔ ላይ መሣተፍ።

### 6.2.2. የተማሪው/ዋ/ወላጆች/አሳዳጊዎች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

ወላጆች/አሳዳጊዎች ከማንም የበለጠ ስለልጃቸው አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ አላቸው፡ በመሆኑም የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት አለባቸው።

- ስለልጃቸው ታሪካዊ ዳራ፣ ጠንካራ ጎን፣ ውሱንነት፣ ፍላጎት፣ ችሎታ ወዘተ መረጃ መስጠት፣
- ልጃቸው ለወደፊቱ እንዲሆንላቸው የሚፈልጉትን፣ ሥጋታቸውን፣ ለትምህርትና ሌሎች ዕድገት ማድረግ የሚችሉትን ተግባራት ወዘተ ድጋፍ መስጠት፣
- በነፍስወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብር የሚደረገውን ድጋፍና ትምህርት በቤት ውስጥም ከመምህራን ጋር በመተጋገዝ ማድረግ እንደሚገባቸው ማመንና መተግበር፣
- በቤት ውስጥ እየተደረገ ያለውን ድጋፍና ትምህርት ለቡድኑ ሪፖርት ማድረግ።

### 6.2.3. የትምህርት ቤቱ ርዕስ መምህር/ተወካይ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

የትምህርት ቤቱ አመራር አካላት ለነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብር ተግባራዊት ቁልፍ ሚናና ኃላፊነት አለባቸው:: የት/ቤቱ ርዕስ መምህር የሚከተሉት ተግባራትን ያከናውናል፡፡

- የመርሃ-ግብሩን ዕቅድና ትግበራ ሂደት ማስተባበርና መደገፍ፣
- ትምህርት ቤቱን ለመርሃ-ግብሩ ተግባራዊነት ማመቻቸት፣
- የትምህርት ቤቱን አስተዳደር፣ አስፈላጊ ቁሳቁሶች፣ የልዩ ፍላጎት ሁኔታ ወዘተ ለውይይት ማቅረብና ማስወሰን፣
- የመርሃ-ግብሩ ዕቅድ ተግባራዊ እንዲሆን በኃላፊነት መንቀሳቀስ፡፡

### 6.2.4. የክፍል ወይም የትምህርት ዓይነት መምህር የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

የክፍል/የትምህርት ዓይነት መምህር የመርሃ-ግብሩ አባል መሆን ይገባዋል፡፡ መምህሩ ተማሪው/ዋን/ በቅርብ የሚከታተል ስለሆነ የመርሐ-ግብሩ ዋና ተዋናይ መሆን ይገባዋል፡፡ ስለሆነም መምህሩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አለበት፡፡

- ሥርዓተ-ትምህርቱ ለተማሪው/ዋ/ ተስማሚ መሆኑን፣
- ሥርዓተ-ትምህርቱን እንዴት በተማሪው ፍላጎትና ችሎታ ማስማማት እንደሚገባና እንደሚቻል፣
- አስፈላጊ ቁሳቁስና ድጋፍ እንዴት ማቅረብና መጠቀም እንደሚቻል፣
- ተማሪውን /ዋን/ በሥርዓተ-ትምህርትና ተጨማሪ ትምህርት (extra-curricular) ተግባራት ላይ እንዴት በንቃት ማሳተፍ እንደሚቻል፣
- በመርሃ-ግብሩ ተግባራዊነት እንቅስቃሴ ውይይት ማድረግ፣
- በመርሃ-ግብሩ መሰረት የተማሪው/ዋ/ በመማር ለውጥ እንዴት መመዘን እንደሚቻል ውይይት ማድረግ፣
- ለወላጆች/አሳዳጊዎች ተማሪው/ዋን/ እንዴት በቤት ውስጥ ማስተማርና መደገፍ እንደሚቻል የምክር አገልግሎት መስጠት፣
- ከልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህር/ተዘዋዋሪ መምህር ጋር መተባበር፣
- ከተለያዩ ባለሙያዎች፣ ወላጆችና የሥራ ባልደረቦች ጋር በትብብር መሥራት፡፡

### 6.2.5. የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህር /ተዘዋዋሪ መምህር የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

የልዩ ትምህርት መምህር/ተዘዋዋሪ መምህር የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎችን ለማስተማር የሚከተለውን ሚና ይጫወታል፡-

- የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ስለሚማሩበት መንገድ ያለውን ጠቃሚ መረጃና ልምድ ያካፍላል፣
- ተማሪዎቹ በተገቢው ሁኔታ እንዲማሩ ለመርዳት ይቻል ዘንድ ሥርዓተ ትምህርት እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል ያለውን እውቀት ያካፍላል፣
- ተማሪዋ/ው የተማረችውን/የተማረውን የችሎታዋን/ውን እንድታሳይ/እንዲያሳይ የፈተና ማሻሻያ መንገዶችን ያመለክታል፣
- አስፈላጊ ስለሆኑ ተጨማሪ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች መረጃ ይሰጣል፣ የትና እንዴት እንደሚገኙም ይጠቁማል፣
- የተማሪዎቹን ልዩ ፍላጎት ለማርካት የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የት እንደሚገኙም ይጠቁማል፣
- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች።
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህር/ተዘዋዋሪ መምህር የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብሩን ለመተግበር የኦቲዝም ችግር ካለባቸው ተማሪዎች ጋር የመስራት ኃለፊነት አለበት/ባት።

**ስለዚህም**

- የድጋፍ መስጫ ክፍል ወይም ልዩ ክፍል ውስጥ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ከሚጠቀሙ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ጋር ይሰራል/ትሠራለች፣
- ከመደበኛው ትምህርት መምህር ጋር በመሆን በክፍል ውስጥ ያስተምራል/ታስተምራለች፣
- የትምህርት ቤቱ መምህራን በተለይም የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ልዩ ፍላጎት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ማስተማር በሚችሉበት መንገድ ዙሪያ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል/ትሰጣለች።

# 7. የሌሎች ባለሙያዎች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

የነፍስ-ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ከዚህ በተጨማሪ እንደ ተማሪዎቹ የችግር ደረጃ የሌሎች ባለሙያዎችን ዕውቀትና ሙያ በማስተባበር መሥራት ይጠይቃል፡፡ ምናልባትም የሚከተሉትን ባለሙያዎች ሊጨምር ይችላል፡፡

- የተንዳኝ አገልግሎቶት ባለሙያዎች፣ ለምሳሌ የወጌሻ ባለሙያዎች፣ ማህበራዊ ሠራተኞች፣ የጤና አጠባባቅ ተወካይ (አስፈላጊ የሆነና የሚገኝ ከሆነ)፣
- ምቹ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለማዘጋጀት እንዲቻል የግምገማ ውጤቶችን የሚተነትን/ ምትተነትን ባለሙያ ናቸው፡፡

## 7.1.የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን ስብሰባ

በአጠቃላይ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር እቅድ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር የቡድኑ አባላት ስለ ተማሪዎቹ ችግሮች፣ ስለ ትምህርት ቅስሞሽ ሂደቶችና እየተሰጠ ስላለው ድጋፍ ባላቸው እውቀት ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ የቡድኑ አባል በእቅዱ ወቅት የራሱ/ራሷን አስተዋጽኦ ማበርከት ይጠበቅበታል/ባታል፡፡

የትምህርት ቤቱ አስተዳዳር ከነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ-ግብር ስብሰባ የጊዜ ሠሌዳ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሠረት፡-

- ከቡድኑ አባላት ጋርወላጆችን ጨምሮ ግንኙነት ያደርጋል፣
- ከወላጆች ጋር ግንኙነት በመፍጠር በስብሰባው ላይ መገኘታቸውን ያረጋግጣል፣
- ለወላጆችና ለትምህርት ቤቱ ምቹ የሆነ የጊዜ ሠሌዳ ያዘጋጃል፣
- ለወላጆች የስብሰባውን አላማ፣ ቦታና ጊዜ ያሳውቃል፣

**በስብሰባውም፡-**

- የተማሪዋ/ውን ሁኔታ ይገለጻል፣
- እያንዳንዱ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር አባል ስለተማሪው ሁኔታ ያለውን ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል፣
- ለእያንዳንዱ ቡድን አባላት ሃሳቦችና ግብዓቶች ዋጋ ይሰጣል፣
- የተማሪዋ/ውን ፍላጎት እንዴት ማርካት ይቻላል በሚለው ሃሳብ ዙሪያ ውይይት ያደርጋል፣

- ለተማሪዋ/ው የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ይዘጋጃል፡፡

## 7.2. የነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሃ ግብርን ማዘጋጀት

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር በቡድኑ አባላት ሲዘጋጅ በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ሊተኮር ይገባል፡-

- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር የተዘጋጀበትን ቀን፣
- የተማሪዋ/ው ግለ ታሪክ መረጃ፣
- ተማሪዋ/ው ብቃት፣
- በትምህርት ቤት የተማሪዋ/ው ሁኔታና የመማር ችግሮች መግለጫ፡፡

**ግቦች**

- የረጅም ጊዜ ግቦች፣
- የአጭር ጊዜ ግቦች፣
- ዘዴዎች፣
- የቁሳቁስ አቅርቦት፣
- አደረጃጀትና የትምህርት ቅስሞሽ አካባቢ፣
- የሚሰጥ ድጋፍ፣
- ምዘና ፣
- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ግምገማ ሥርዓትን ያካትታል፡፡

### 7.2.1. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ብቃት (competence)

- የሚታቀደው ዕቅድ የተማሪዋ/ው ጠንካራ ጎኖችንና ክሂሎትን መሠረት ማድረግ አለበት፣
- የተማሪዋ/ው የትምህርት፣ ማህበራዊ ሥነልቦናዊ ችሎታ(ብቃት) ግንዛቤ ውስጥ መግባት ይኖርበታል::

### 7.2.2. በትምህርት ቤት የተማሪውን ሁኔታና የመማር ችግሮች መግለጫ

- ተማሪዋ/ው በአሁኑ ጊዜ በትምህርት ቤት/ ከትምህርት ቤት ውጭ እየሰራች/እየሰራ ያለችበት/ያለበት ሁኔታ ለእቅድ አወጣጡ በጣም አስፈላጊ ነው፣
- ተማሪው/ዋ ትምህርት በሚማርበት/ምትማርበት ወቅት የሚያጋጥሙትን የተለያዩ ችግሮች ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል (ይህም በትምህርት፣ በስሜት ወይም በማህበራዊ ግንኙነት ክሂሎት አካባቢዎች ያሉትን ለማለት ነው፡፡)

### 7.2.3. የነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሃ ግብር የአጭርና ረጅም ጊዜ ግቦች

- በዕቅዱ መጀመሪያ ላይ ግቦች በጥቅል መቀመጥ ይኖርባቸዋል፣
- እያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት በሚመለከት የተጣሉ ግቦችን ለማሳካት በሚያስችሉ ክህሎትና ችሎታ ላይ ማተኮር ይገባል፣
- ግቦቹ የተማሪዋ/ውን ፍላጎት ማርካት በሚችሉ መልኩ መጣል ይኖርባቸዋል፣
- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ግቦች ተግባራዊ ክህሎትን ኢላማ ያደረጉና የአጠቃላይ ሥርዓት ትምህርቱ ማዕቀፍ አካል መሆን ይኖርባቸዋል፣
- የተማሪዎቹን አላማዎችና ግቦች በክፍል ተግባራት ውስጥ ለማካተት የሚያስችሉ፣ ዓላማዎቹና ግቦቹ ሊተገበሩ የሚችሉና እድሜን የሚመጥኑ መሆን ይኖርባቸዋል፣
- የነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሃ ግብር መመዘንና መለወጥ ያለበት የተማሪዋ/ውን እድገትና ፍላጎቶች መሰረት በማድረግ መሆን ይኖርበታል።

**የረጅም ጊዜ ግቦች እቅድ :-**

- እቅድ መጀመሪያ ይታቀዳል፣
- ለአንድ ትምህርት ዘመን ሳይለወጥ ልንጠቀምበት እንችላለን፣
- ተማሪዋ/ው በምታዳብራቸው/ በሚያዳብራቸው ክሂሎትና በሚያጋጥሟት/ በሚያጋጥሙት ችግሮች ላይ ትኩረት ይሰጣል፣
- በነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ የተጣሉት የትምህርት ግቦች ከአገር አቀፍ ሥርዓት ትምህርቱ ጋር የተጣጣሙ መሆን ይኖርባቸዋል፣
- ግቦቹን ማሻሻል ቢያስፈልግም ተማሪዋ/ውን የነፍስ ወከፍ ችሎታና መሰረት ማድረግ ይኖርበታል።

**የአጭር ጊዜ ግቦች እቅድ :-**

- ተግባር ተኮር ሆነው ግን ከረጅም ጊዜ ግቦች ጋር መጣጣም አለባቸው።
- በነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ስብሰባ ላይ ግቦቹን ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል ጥያቄዎች ከተነሱ በተማሪዋ/ው ላይ ተከታታይ ምልከታ ካደረጉ ሰዎች ጋር በመወያየት መሆን ይኖርበታል።

## 7.3. የነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሃ ግብር ክንውን ዘዴዎች

- ተማሪዋ/ውን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል የሚወስኑትን የረጅምና አጭር ጊዜ ግቦች ማንፀባረቅ አለበት፣
- ግቦቹን ለማሳካት በጣም ውጤታማና ምቹ የሆኑ ድጋፍ መስጫ ዘዴዎች ምን እንደሆኑ ያብራራል፣
- ተማሪዋ/ውን ለማስተማር የትኞቹ ስትራቴጂዎች/ዘዴዎች እንደሚያስፈልጉ ይገልፅል፣
- ምን አይነት የማስተማር ማስማማቶች ያስፈልጋሉ ለሚለው ምላሽ ይሰጣል፡፡

### 7.3.1. የቁሳቁሶች አቅርቦት

- ለተማሪው/ዋ የሚቀርቡ የነፍስ ወከፍና አጠቃላይ ቁሳቁስን ያመላክታል፣
- ምን ዓይነት ተጨማሪ የማስተማሪያ መሣሪዎች ያስፈልጋሉ ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል፣
- ከክፍል ጓደኛዋ/ው ጋር ስትነፃፀር/ሲነፃፀር ተማሪዋ/ው አንድ አይነት/ ተመሳሳይ/ ቁሳቁስ ለምን ያህል ጊዜ ትጠቀማለች/ ይጠቀማል ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ይሆናል፣
- ምን ዓይነት አማራጭ የማስተማሪያ ቁሳቁስ ይገኛሉ የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል፣
- የማስተማሪያ ቁሳቁስ እንዴትና በማን ይዘጋጃሉ ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል፡፡

### 7.3.2. አደረጃጀትና የትምህርት ቅስሞሽ አካባቢን ማስማማት

- ግቦቹን ለመምታት በጣም ውጤታማና ለተማሪዋ/ው ድጋፍ አሰጣጥ ምቹ የሆኑ መንገዶች ምን እነደሆኑ ይገልፃል፣
- የክፍል ውስጥ ወይም የትምህርት ቤቱን ሁኔታ ይገልፃል፣
- ተማሪው/ዋ ከምክር አገልግሎት እንዲጠቀም/ድትጠቀም ምን ዓይነት ተግባራዊ ድጋፎች እንዳሉ የማወቅ (ምቹ መቀመጫና ቦታ፣ ምቹ መሳሪያዎችና የሚያስፈልገው ድጋፍ)፣
- የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን አባላት ልምዶች እኩል ዋጋ ያላቸውና በውይይት ወቅት ጠቃሚ ናቸው፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማስተማር ዘዴዎች ዙሪያ ለሚነሱ ጥያቄዎች ማባራሪያ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

### 7.3.3. በትምህርት ቤት ውስጥና ከትምህርት ቤት ውጭ የሚደረግ ድጋፍ

- ምን ዓይነት ድጋፍ እንደሚያስፈልግና/እንዳለ መገንዘብ፣

- የተዘዋዋሪ መመህራንን ድጋፍ ሰጭነት ሚና መረዳት፣
- ከመምህሩ/ሯ ሃሳብ/ምክር የተሰጣቸው ወላጆች ለልጆቻቸው የትምህርት ድጋፍ መስጠት እንደሚችሉ መረዳት፣
- ሌላ የሚሰጥ ተጨማሪ ድጋፍ ካለ ለምሣሌ ከጤና አጠባበቅ ዘርፍ፣ ከማህበራዊ ሠራተኞች፣ ከማህበረሰብ ሠራተኞች መግለፅ አስፈላጊ ነው::

### 7.3.4. ውጤቶችና የትምህርት ቅስሞሽ ምዘና

ምዘና ተማሪዋ/ው በምታስመዘግበው/ በሚያስመዘግበው ውጤቶችና በትምህርት ቅስሞሽ ሂደቶች ላይ እንዲያተኩር መደረግ አለበት፡-

- ተማሪዋ/ው ያሳየችውን/ያሳየውን ለውጥ እንዴት መገምገም እንደሚቻል ያብራራል፣
- ግምገማው መቼ መካሄድ እንዳለበት ይገልፃል፣
- ተማሪዋ/ው ያለችበትን/ያለበትን ደረጃ ለማወቅና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ስራ ለመስራት ማን እንደሚገመግመው ይገልፃል፣

## 7.4. የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር አተገባበር (implementation)

የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ከተዘጋጀ በኋላ መተግበር ይኖርበታል፡፡ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሀ ግብር ቡድን ለተማሪዋ/ው የተጣሉትን ግቦች በተሻለ ሁኔታ ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑት ተጨማሪ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፣ አገልግሎቶች፣ የፕሮግራም መሻሻሎችና የመሳሰሉትን በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ ተማሪዋ/ው መሻሻል እንድታሳይ/እንዲያሳይ ይረዳታል/ይረዳዋል፡፡

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን ለመተግር በአገልግሎት አሰጣጥ ውስጥ የተካተቱን የእያንዳንዱን ግለሰብ ኃላፊነት በግልፅ ማሳየት አለበት፡፡ ይህም ተማሪዎች በእቅዱ መሠረት አገልግሎት እንዲያገኙ ይረዳቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ የነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሀ ግብር አባላት እንደ አስፈላጊነቱ ለማሻሻልና ለማካተት የለይዋቸውን ነገሮች ለመጨመር ያስችላል፡፡

ሀ) የቡድን ሥራ የነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሃ ግብርን ለመተግበር ጠቃሚ ሚና ይጫወታል፡፡ ለተማሪዋ/ው ድጋፍና ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት ብዙ ነገሮችን በትኩረት መመልከት የእያንዳንዱን ሰው ሥራ ከማቅለሉም ባሻገር የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ውጤት እንደሚያሻሽል በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

ለ) ትምህርት ቤቶች ለመምህራን፣ ድጋፍ ሰጪ አካላት፣ ወላጆችና ወይም ለሌሎች ባለሙያዎች በቡድን እንዲሰሩ ጊዜ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም እቅድን ለማዘጋጀት ወይም ሥርዓተ ትምህርቱን በማስማማት የተማሪዎቹን ልዩ ፍላጎት ለማርካት ያስችላል፡፡

ሐ) በቤትና በትምህርት ቤት መካካል ያለው ግንኙነት በጣም አስፈላጊ ነው። ወላጆች ቤት ውስጥ ምን እየተከናወነ እንደሆነ መረጃ ይሰጣሉ። እንዲሁም ተማሪዋ/ው በትምህርት ቤት የተማረችው/የተማረውን ሃሳብ በመጨመር እውቀታቸውን ይገነባሉ። ተማሪዋ/ው በትምህርት ቤት ችግር ከተፈጠረባት/ከተፈጠረበት ወላጆች የተፈጠረውን ችግር በመለየት ሂደት ውስጥ ለትምህርት ቤቱ ዕገዛ ያደርጋሉ። የመፍትሔ ሃሳብም ይጠቁማሉ። ተማሪዎቹ የሚያገኙትን የድጋፍ አገልግሎት የሚያስተባብር፣ የሚከታተል አንድ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ቢኖር ጥሩ ነው። ከልዩ ፍላጎት ትምህርት በተጨማሪ ተማሪዎቹ ተዛማጅ የሆኑ የተለያዩ አገልግሎቶች ሊያገኙ ይችላሉ። የሚሰጡት አገልግቶች በእቅዱ መሠረት መሆናቸውን የሚከታተል ሰው መኖሩ የነፍስ ወከፍ የትህርት መርሃ ግብር በአግባቡ መተግበሩን ለማረጋገጥ ይረዳል።

የመደበኛ ሪፖርቶች መኖር ወላጆችና ትምህርት ቤቶች ተማሪዋ/ው ከተቀመጠው አመታዊ ግብ አንፃር ለውጥ እያሳየች/እያሳየ መሆኗን/ መሆኑን ለመከታታል ያስችላል። ተማሪዋ/ው የሚጠበቀውን ያህል ለውጥ አለማሳየቷን/ አለማሳየቱን ወይም ከሚጠበቀው በላይ ፈጥና/ፈጥኖ ለውጥ ማሳየቷን/ ማሳየቱን ማወቅ ጠቃሚ ነው። የተማሪዋ/ው ፍላጎቶች ከታወቁ ወላጆችና የትምህርት ቤት ኃላፊዎች እነዚህን ፍላጎቶች ለማርካት በጋራ መስራት ይችላሉ።

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር በትምህርት ቤትም ሆነ በሌሎች አውዶች በዕለት ተዕለት የህይወት እንቅስቃሴ ውስጥ መተግበር አለበት። ተማሪዋ/ው በምትሳተፍባቸው/ በሚሳተፍባቸው ሁሉም ተግባራት ውስጥ የተለያዩ ድጋፎች ሊደረጉላት/ሊደረጉለት ይገባል። ይህም ማለት አብዛኛው ጊዜ ሌሎች ተማሪዎች በአማራጭ የአጠናን አሰራር መንገዶች ሊጠቀሙ ይችላሉ ( ከመፃፍ ይልቅ በንግግር ማቅረብን እንደችሎታዋ/ው በተግባር መሳተፍ)። ለተለያዩ ሁኔታዎች ተግባራዊ የሚሆኑ የመፍትሔ ሃሰቦች በነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር የእቅድ ስብሳባ ላይ ለውይይት መቅረብ ይኖርበታል።

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር በክፍል ውስጥ ለሚከናወኑ ተግባራት እንደማዕቀፍ ሆኖ ያገለግላል። መምህራን በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ሁሉንም ተማሪዎችን ለማርካት የሚያስችል ተግባራዊ የመፍትሔ ሃሳቦችን ማፈላለግ ይኖርባቸዋል። በነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርና በመደበኛው ሥርዓት ትምህርት የሚማሩ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች

በአንድ ክፍል ውስጥ ስለሚገኙ የክፍል ውስጥ የማስተማር ሥራው ከነፍስ ወከፍ የትምህር መርሃ ግብር አባላት ጋር በመሆን በጥንቃቄ መታቀድ አለበት፡፡ እነዚህ የማስተማር ሥራዎች የሥርዓተ ትምህርቱን ይዘቶች ተማሪዋ/ው እንድትማር/እንዲማር ሊረዱ የሚችሉ ክሂሎችና ማስተማርን ያጠቃልላል፡፡

በአካቶ ትምህርት ክፍል ውስጥ በነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሃ ግብር የሚማሩ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ድጋፍ እየደረገላቸው በመደበኛው ትምህርት ውስጥ ከእድሜ እኩዮቻቸው ጋር አብረው ይማራሉ፡፡ ዕቅዱንም ለማሳካትና የሚሰጠው ድጋፍ መጠን ውጤታማና ምቹ በማድረግ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የኑሮ ሁኔታን ለማሻሻል ነው፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብሩ ተማሪዋ/ው በክፍል ውስጥ በሚካሄዱ ተግባራት ውስጥ ምን ያህል መሳተፍ እንዳለበት/እንዳለባት ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

## 7.5. የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን መመዘን

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር የሚመዘነው የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ያመጡትን ለውጥ ከተቀመጠው አላማ ጋር በማወዳደር ነው፡፡ ይህም ማለት ትምህርቱን እንዴት መቀጠል እንደሚቻል ውሳኔ ለመስጠት ማለት ነው፡፡ ምዘና የአንድ ጊዜ ሥራ ሳይሆን ተከታታይ ሂደት ነው፡፡ የዚህ ምዘና ሂደት አላማም ስለተማሪዋ/ው የትምህርት አሰራር አቀባበልና ያሳየችው/ው ለውጥ ለመምህራንና ለወላጆች መረጃ ለማቅረብ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ምዘናው በቀጣይ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ያመለክታል፡፡

## 7.6. የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር የምዘና መርሆዎች

የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን ስንጠቀም፣ ቡድኑ የተለያዩ ጠቃሚ ክሂሎችን መመዘኑ ጠቀሜታ አለው፡፡ እነዚህ ሂደቶችም ከአንድ ዓይነት ባሕርይ ይልቅ ሰፊ ዓላማዎች ያሉትን የትምህርት ቅስሞሽ ውጤቶችን ያሳያሉ፡፡ ይህም በነፍስ ወከፍ የሚሰጠውን ድጋፍ ለማሻሻል ይረዳል፡፡ የሚመዘኑት ምን ዓይነት ፍላጎቶች ናቸው?

- የትምህርት ክሂሎት፣
- ማህበራዊ ክሂሎት፣
- የባህርይ ክሂሎትና፣
- የግንዛቤ ክሂሎት ናቸው፡፡

ግቦቹ በሚገለፁበት ጊዜ ምዘናው ግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል፡፡ የማህበራዊና ባህርይ ግቦች እንደተጨማሪ እንጂ የሥርዓተ ትምህርቱንና ተዛማጅ ግቦችን የሚተኩ ሆነው መታየት የለባቸውም፡፡ ተማሪዎች ስለራሳቸው ያላቸውን ግምትና የግንዛቤ ክሂሎት እንዲያዳብሩ ምዘና

እንዲያካሂዱ ይበረታታሉ፡፡ ምዘና ማስረጃን የመፈለግና የመተንተን ሂደት ሲሆን ይህም ተማሪዎቹ በትምህርታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ በቀጣይ ወደ የት ሊሄዱ እንደሚችሉና የሚሄዱበት ቦታ ምን ያህል ምቹ እንደሆነ ለመወሰን ለተማሪዎቹም ለመምህራኑም ይረዳል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ባለሙያዎች ተማሪዋ/ው ያገኘችውን/ያገኘውን/ መልካም አጋጣሚ ተጠቅማ/ሞ የሥራ ውጤቷን/ ውጤቱን በአግባቡ ማሳየት መቻሉን ሊያምኑበት ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር የተማሪዋን/ውን የትምህርት ውጤትና የተግባር ክንውኖች በአግባቡ ለመመዘን በግል የምትሰራበት/ የሚሰራበት ምቹ ቦታ ሊያስፈልግ ይችላል:: የምዘና መርሆዎች በነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቅፅ ውስጥ መገለፅ አለባቸው፡፡

- ምዘና የነፍስ ወከፍ መርሃ ግብሩን ግቦች መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፣
- የሚለኩ ወይም በገለፃ መልክ ሊመዘኑ የሚችሉ ግቦችን መምረጥ ይገባል፣
- ወደ ግቦቹ ለመድረስ እየተደረገ ያለው መሻሻል እንዴት እንደሆነ ተከታታይ ምልከታና ግምገማ ማካሄድና፣
- ግለ-ምዘና መካተቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

የነፍስወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር በሚዘጋጅበት ወቅት ቡድኑ ስለክትትል በእቅዱ ሰነድ ውስጥ በግልፅ ማስቀመጥ አለበት፡፡ ይህም የሚከተሉትን ይጨምራል:-

- ክትትል በምን ላይ ይደረጋል፣
- ክትትል የሚያደርገው ማነው ፣
- መቼና የት ክትትሉ ይደረጋል፣
- መረጃው እንዴት ሪፖርት ይደረጋል የሚሉትን መመለስ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡

## 7.7. የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ሰነድን መፈራረም

በሚከተሉት የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ላይ በመፈራረም ሁሉም ተሣታፊዎች ለሂደቱ መሣካት ቁርጠኝነታቸውን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

- የትምህርት ቤት አመራሮች ለተማሪው የነፍስ ወከፍ መርሃ ግብር ድጋፍ ለመስጠት ጥረት እንደሚያደርጉ ማረጋገጥ አለባቸው፣
- ወላጆች/አሳዳጊዎች በሥርዓተ ትምህርቱና በምዘና ሂደቱ ላይ የተደረገውን ለውጥ መቀበል አለባቸው፡፡

## 8. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ዕቅድና ክንውን፣ ጠቃሚ ምክር/መረጃ (Tips for Teachers of Students with Autism)

- ተግባራትን ግልጽና አጭር (specific) በማድረግ በቅደም ተከተል ማስተማር፣
- በቀላል ቋንቋና በተጨባጭ ምሳሌዎች ማስረዳት፣
- የማህበራዊ ግንኙነት ህግና ደንብ በቀላልና በተናጠል(specific) በማድረግ ማስረዳት፣
- ጥቂት አማራጮችን መስጠት፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎቹ ብዙ አማራጮች ካገኙ ትኩረታቸው ስለሚረበሽ/ ስለሚምታታባቸው ነው፣
- ለማንኛውም አዎንታዊ ምላሽ ማበረታቻ መስጠት፣
- የሽሙጥ፣ ወዘተ ቋንቋ ( figurative speech) አለመጠቀም፡፡ ምክንያቱም እንደነዚህ ያሉ ተጨባጭ ያልሆኑ (ለመረዳት ከባድ ትርጉሞች) በተማሪዎቹ የማምታታት ወይም የመረዳት ችግር ስለሚፈጥርባቸው ነው፣
- ግልጽ የሆኑ አማራጮች መስጠት፡፡ ለምሳሌ ማንበብ ወይስ መጻፍ ትፈልጋለህ?
- ትዕዛዛትን(instructions) መደጋገምና መረዳታቸውን ማረጋገጥ፣
- ግልጽ የሆነ ሥርዓት (structure) ማስቀመጥና ማሣየት፣
- ጀምሮ የመጨረስና ሌላ ተግባር የመጀመር ልዩነቶችን በምሳሌና በፎቶግራፍ ማስረዳት፣
- ተማሪውን/ዋን በየጊዜው ስም በመጥራት ወይም በሌላ መንገድ በማሳሰብ ትዕዛዝ መስጠት፡፡ ምክንያቱም ለምሳሌ ክፍሉን ሙሉ የክፍል ሥራ ሥሩ ቢባል የኦቲዝም ችግር ላላቸው ተማሪዎች ትዕዛዙ እነሱንም የሚመለከት መሆኑን ላይረዱ ስለሚችሉ ነው፣
- የተለያዩ የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎችን መጠቀም፡፡ ለምሳሌ፣ የዕይታ መርጃ መሣሪያ (visual aids)፣ ሞዴል(model)፣ ማስመሰል (simulation) ወዘተ መጠቀም፣
- በፍርሃት ምክንያት የባህሪይ ወይም ተመሣሣይነት ያለው ችግር ሊፈጠር ስለሚችል የፍርሃት (anxiety) መነሻዎችን መቀነስ ወይም ማስወገድ፣
- ቁጣ ወይም የማስፈራራት ምልክት አለማሳየት፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎቹ ይህን ላይረዱ ስለሚችሉና እንደ ጥፋትም ሊገነዘቡት ስለማይችሉ ነው፣

- ትኩረታቸውን የሚረብሹ ነገሮችን ማስወገድ። ለምሳሌ ድምጽ፣ ብርሃን፣ የተለያዩ መሣሪያዎች ክምችትን፣ ወዘተ መቀነስና ማስወገድ፣
- የሚሰጣቸውን ተግባር ከተማሪዎች ፍላጎትና ችሎታ ጋር በማጣጣም ማቅረብ፣
- ከአቻዎቻቸው(peers) የሚደርስ ማናደድ (teasing)፣ ስድብ፣ ወዘተ አቻዎቻቸውን በማስተማር ጥሩ የክፍልና ትምህርት ቤት አካባቢ መመሥረት፣
- የሚጠሉትን ነገር በግድ አለማሠራት። ነገር ግን በተለያዩ ዘዴዎች የሚጠሉትን ነገር እንዲወዱት ማድረግ፣
- የሚፈለግ ነገር ወይም ባህሪይ(desirable behavior) ሲያሣዩ የሚወዱትን ነገር እንደማበረታቻ (reward) መስጠት።

## 9. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ላይ መደረግ ያለባቸውና መደረግ የሌለባቸው ተግባራት (Do’s and Don’ts During Teaching of Students with Autism)

የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ፍላጎትና ችሎታ መሠረት በማድረግ የመግባባትና የአያያዝ ዘዴ መጠቀም እንዳለብዎ ያስታውሱ፡፡

- የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የማህበራዊ ግንኙነት ህግና ደንብን መሠረት በማድረግ የመግባባት ችግር ሊገጥማቸው እንደሚችል አይዘንጉ፡፡
- የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ነገሮችን በግርድፉ ሊረዱ እንደሚችሉና በአግባቡ ሊረዱ እንደማይችሉም ተገንዝበው እርስዎ ተገቢ እርዳታ ያድርጉ፡፡ ከተማሪው/ዋ ጋር ሲግባቡ ቀላልና ግልፅ በሆነ ቋንቋ ይጠቀሙ፡፡
- ተማሪው/ዋ የተሰጠውን/ጣትን መረጃ ለመረዳት ጊዜ የሚፈልግ/ምትፈልግ መሆኑን አይርሱ፡፡
- በተማሪው/ዋ ፍላጎትና ችሎታ መሠረት ተስማሚ የመማሪያ አካባቢ ይፍጠሩ፡፡
- ተማሪው/ዋ እርስዎ የሚሉትን ወይም እንዲማር/ድትማር የፈለጉትን ነገር እስኪረዳ/ክትረዳ ድረስ ጊዜ ይስጡት/ጧት፡፡ ምክንቱም አንዳንድ ኦቲዝም ያለባቸው ተማሪዎች ብዙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሊረዱ ሙከራ እንደሚያደርጉ አይርሱ፡፡
- ተማሪዎቹ ጠይቆ የመረዳት ችግር ሊኖርባቸው ስለሚችል እንዲጠይቁና እንዲረዱ ያበረታቱ፡፡
- ለሥራ ባልደረቦችዎና ለተማሪው/ዋ አቻዎች ስለኦቲዝም ችግር አጠቃላይ ባህሪያት በየጊዜው ከማስረዳት አይቆጠቡ፡፡
- ተማሪው/ዋ የሚፈለጉ ባህሪያትን ሲያሣይ/ስታሳይ ወይም ተፈላጊ ተግባራትን ሲያከናውን/ስታከናውን የማበረታታት ተግባር መከወን እንዳለብዎ አይርሱ፡፡ የማበረታታቱ ተግባር ወዲያውኑ መሆን እንዳለበትም አይርሱ፡፡
- በተማሪው/ዋ ከተግባር ወደ ተግባር ወይም ከሁኔታ ወደ ሌላ ሁኔታ ሽግግር ወቅት ይርዱት/ዷት፡፡
- በተማሪው/ዋ ጠንካራ ጎኖች ላይ ትኩረት በማድረግ ደካማ ጎኖችን ለመቅረፍ ጥረት ያድርጉ፡፡
- የተማሪውን/ዋን በዓይን መግባባት አለመቻል ችግር እንደተማሪው/ዋ የክፋት ምልክት አይወስዱት፡

- ከተማሪው/ዋ ጋር ተግባቦት ወቅት አሽሙር፣ ስለቅ፣ ወዘተ የተግባቦት ዘዴዎች አይጠቀሙ፡፡
- የፍጥነትና የተድበሰበሱ አነጋገር ዘዴዎች አይጠቀሙ፡፡
- የፍርሃትና የጭንቀት ምልክት በማሳየት ተማሪውን/ዋን ለማስተማር አይሞክሩ፡፡
- በምልክት ቋንቋና በሰውነት እንቅስቃሴ መግባባት ላይ ሙሉ እምነት አይጣሉ፡፡
- ተማሪው/ዋ በሚሰጠው/ምትሰጠው መልስ ወይም አስተያየት ላይ አሉታዊ አመለካከት አያሳድሩ፡፡ ምክንቱም የተማሪው/ዋ የዓለም አመለካከት ከእርስዎ አመለካከት የተለየ ሊሆን ስለሚችል ነው፡፡
- ተማሪው/ዋ በጊዜ ሰሌዳ መሠረት ተግባራትን የማከናወን ችግር ሊገጥመው/ማት ስለሚችል የማስረዳት እርዳታ እንደሚያስፈልግም አይርሱ፡፡
- ከወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ጋር በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በትብብር የመሥራት አስፈላጊነት ይገንዘቡ፡፡

# 10. የትምህርት ቤት ማኅበረሰብ የሥራ ድርሻና ሃላፊነት

## 10.1. የትምህርት ቤት አመራር

አመራሩ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል

- የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂን በትምህርት ቤት ደረጃ ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመተግበር የሚያስችል ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ለዕቅዱ ማስፈፀሚ በጀት ይመድባል፤
- የትምህርት ቤት አካባቢ፣የትምህርት አመራርና አስተዳደር፣ የትምህርትና ፈተና አሰጣጥ የኦቲዝም ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ምቹና ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
- መምህራን፣ የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየትና በመመዘን የመማር ፍላጎታቸውን ማሟላት የሚችሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
- የኦቲዝም ችግር ላለባቸው ተማሪዎች እንዳስፈላጊነቱ የቲቶሪያል፤ የጋይዳንስና ካውንስሊንግ ወዘተ ድጋፎችን የሚያገኙበትን ብሎም የትምህርት ተሳትፏቸውንና ውጤታማነታቸውን የሚያጎለብቱበትን ስልት ይነድፋል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፤
- እንዳስፈላጊነቱ የኦቲዝም ችግር ላለባቸው ተማሪዎች የነፍስ-ወከፍ ትምህርት መርሀ ግብር እንዲዘጋጅና እንዲተገበር ያስተባብራል፤
- የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት የፖሊቲካ፤ የማህበረሰብ እና የሃይማኖት መሪዎች፤ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ፤ የወላጅ-መምህር -ተማሪ ህብረት አባላትና ወላጆች በተለያዩ የኦቲዝም ችግር ባለባቸው ተማሪዎች ላይ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ያደርጋል፤
- የተሻለ የትምህርት ውጤት የሚያስመዘግቡ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የሚሸለሙበት ስርዓት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤
- ከቀበሌ አስተዳደርና የትምህርትና ስልጠና ቦርድ ጋር በመሆን በአካባቢ ማህበረሰቦች የሚገኙ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ዜጎች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡ ወላጆቻቸውን የመቀስቀስና የማሳመን ስራ ያከናውናል፤
- በትምህርት ቤቱ የሚገኙ የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ስታቲስቲካዊ መረጃ በመደበኛነት በሚሰባሰብባቸው መሳሪያዎች ውስጥ ያካትተታል፤ መረጃውን ለወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ይልካል፤

- ተገቢነት ያላቸው ድጋፎች በመስጠትና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመስራት የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎችን የትምህርት ማቋረጥና ክፍል የመድገም መጠን እንዲቀንስ በሂደትም እንዲወገድ ጥረት ያደርጋል፤
- የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎችን በትምህርት ቤት ደረጃ በመፍጠርና ተጨማሪ ሀብት ከለጋሾች የሚገኝበትን ስልት ነድፎ በመንቀሳቀስ የኦቲዝም ችግር እንዲቀረፍ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂን ትግበራ ያጠናክራል፤
- የትምህርት ቤቱ አመራር መምህራንና ወላጆች የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በሚያጋጥሟቸው ችግሮች ላይ የሚወያዩበትና የጋራ መፍትሄዎች የሚፈልጉበትን መደበኛ የምክክር ስብሰባ ጊዜ እንዲኖር ያቅዳል፤
- በትምህርት ቤት ደረጃ በሚካሄደው ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም ውስጥ የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ጉዳዮች መካተታቸውን ያረጋግጣል፤
- የኦቲዝም ችግር ባለባቸው ተማሪዎች ወላጆችና በትምህርት ቤት መካከል ጠንካራ ግንኙነት እንዲፈጠር ያደርጋል፤
- የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ወላጆች ለልጆቻቸው ትምህርት አስፈላጊውን ድጋፍ የማድረግ ሃላፊነታቸውን እንዲቀበሉና በተግባር እንዲወጡ ያበረታታል፤
- መደበኛና ተዘዋዋሪ መምህራን የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የትምህርት ፍላጎቶችን ከማሟላት አኳያ የተሰጧቸው ሃላፊነቶችና ግዴታዎችን በአግባቡ መወጣታቸውን ያረጋግጣል፤
- የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ፤ ወላጆችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በየመንፈቅ ዓመቱ እየተሰባሰቡ ትምህር ቤቱ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎችን አያያዝ በመተግበር ረገድ ያከናወናቸውን ስራዎች በጋራ የሚገመግሙበት መድረክ ያዘጋጃል፤
- የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የትምህርት ቅስሞሽ ምዘና ከፍላጎታቸው ጋር በተገናዘበ መልኩ መፈፀሙን ያረጋግጣል፤ (ለምሳሌ የኦቲዝም ችግር ያለበት ተማሪ ከመደበኛው የበለጠ ተጨማሪ  የፈተና ጊዜ ሊያስፈልገው ይችላል፤ ወይም በአንድ ቀን ውስጥ አንድ ፈተና ብቻ እንዲወስድ ሊደረግ ይቻላል። ከዚህም በተጨማሪ፤ እንደ ፖርትፎሊዮ የፕሮጀክት ስራ፤ ግለ-ምዘና፤

ምልከታ ያሉ የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች በተጨማሪነት ወይም በአማራጭነት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡

## 10.2. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የያዘ ቡድን ተግባራት

ቡድኑ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል

- የኦቲዝም ችግር መነሻና ችግሩን የሚከተሉ የባህሪ ችግሮችን ለመለየትና ለማወቅ ጥናት ያካሂዳል፤
- ቡድኑ ችግር ፈቺ የሆነ የኦቲዝም ችግር አያያዝ ዕቅድ እንዲተገበር በመረጃ የተደገፈ እንቅስቃሴ ያደርጋል፤
- የኦቲዝም ችግርን ለመቀነስ ችግሩ ያለበት ተማሪ ተሳትፎ መኖሩን ያረጋግጣል፤
- ከወላጆች የይሁንታ ፈቃድ ማግኘትንና የወላጅ ተሳትፎም እንዳለበት ያረጋግጣል፤
- የኦቲዝም ችግርንና ጣልቃ መግባትን በሚመለከት ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብና ለወላጆች ሥልጠና ይሰጣል፤
- ሥራው በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተከናወነ መሆኑን ያረጋግጣል፤
- የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አስፈላጊው እገዛ ማግኘት እንዲችሉ ለትምህርት ቤቱ አመራር ሪፖርት ያቀርባል፣
- በውጤቱ ላይ ክትትልና ግምገማ በማካሄድ ቀጣዩን ተግባር ይወስናል ፡፡

## 10.3. የመደበኛ ክፍል መምህር

መደበኛ የክፍል መምህራን የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ

- በመምህራን ትምህርት ተቋማት ቆይታቸው በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ላይ የተሰጡትን ስልጠናዎች መሰረት በማድረግ የኦቲዝም ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ድጋፍ ይሰጣሉ፤
- ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ሲያጋጥማቸው ተዘዋዋሪ መምህሩ/ሯን በማማከር እንዲቃለሉ ያደርጋል፤
- የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎችን የትምህርት ቅስሞሽ ለማሳለጥ ከወላጆች ጋር በቅርብ በመመካከር ይሰራሉ፤
- በመማር-ማስተማሩ ሂደት የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸውን የትምህርት ቅስሞሽ ችግሮችን ለመቅረፍ ተግባራዊ ጥናትና ምርምር ያካሂዳሉ፤

- የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የነፍስ-ወከፍ ችሎታ እንዲሁም የትምህርት ቅስሞሽና አካባቢያዊ ችግሮችን በመለየትና በመመዘን ችግሮቹ የሚቃለሉበትን መንገድ ያቅዳል/ታቅዳለች፤ አስፈላጊውን ድጋፍም ይሰጣል/ትሰጣለች፤እና
- የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ፍላጎቶችን ለማርካት የራሱን/ሷን ፈጠራ በማከል የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ይጠቀማል/ትጠቀማለች፤ ለምሳሌ:- በትብብር መማማር፤ የአቻ መማማር፤ ቡድን ምስረታ ( በችሎታ ላይ በመመስረት፤ በመቀላቀል፤ በፍላጎት ላይ በመመስረት) ወዘተ ናቸው፡፡

## 10.4. የድጋፍ መስጫ ማዕከል (resource centers)

- በአጠቃላይ ሲታይ ድጋፍ መስጫ ማዕከላት ለመምህራን፤ ለትምህርት ቤት አስተዳደር፤ ለወላጆችና ለነፍስ-ወከፍ ተማሪዎች ሙያዊ ድጋፍ ከመስጠታቸው ባሻገር የኦቲዝም ችግር ላለባቸው ተማሪዎች የትምህርት መርጃ ቁሳቁሶችን ያቀርባሉ፡፡ በማዕከሉ ውስጥ የኦቲዝም ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ድጋፍ የሚያደርጉ የተለያዩ ባለሙያዎች ማለትም ተዘዋዋሪ መምህራንና የስነ-ልቦና ባለሙያዎች ይገኛሉ፡፡ የእነዚህ ባለሙያዎች ሃላፊነትና የስራ ድርሻ ከዚህ በታቻ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 10.5. ጋይዳንስ ካውንስለር (ለ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት)

ጋይዳንስ ካውንስለር የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል/ታከናውናለች

- በትምህርት ቤቱ ለሚገኙ የኦቲዝም ችግር ላለባቸው ተማሪዎች የጋይዳንስና ካውንስሊንግ አገልግሎት ይሰጣል/ትሰጣለች፤
- መምህራን የኦቲዝም ችግር ያለባቸውን ተማሪዎችን የነፍስ-ወከፍ የትምህርት ቅስሞሽ ችሎታ እንዲመዝኑና አካባቢያዊ እንቅፋቶችን እንዲለዩ ድጋፍ ያደርጋል/ታደርጋለች፤ መምህራንም ከዚህ በመነሳት ተማሪዎቻቸውን ለመርዳት የታዩትን እንቅፋቶች ለማስወገድ እንዲያቅዱ ይረዳቸዋል/ትረዳቸዋለች፤
- በተማሪዎች ውጤት ላይ በመመርኮዝ የተማሪዎችን ወላጆች ጠርቶ/ታ ያነጋግራል/ታነጋግራለች፣
- ለሁሉም የኦቲዝም ችግር ላላቸው ተማሪዎች ወላጆች አስፈላጊውን የጋይዳንስና የምክር አገልግሎት ይሰጣል/ትሰጣለች፤እና

- የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎችን የችግሩን መንስኤ በሚመለከት ጥናትና ምርምር ያካሂዳል/ታካሂዳለች፡፡

## 10.6. ተዘዋዋሪ መምህር

ተዘዋዋሪ መምህር ማለት በልዩ ፍላጎት ትምህርት ከመሰልጠኑም ባሻገር አንድ ወይም ከዚያ በላይ ክሂል (ለምሳሌ ብሬል፣ ምልክት ቋንቋ ወዘተ) ያለው ሆኖ በየትምህርት ቤቱ በመዘዋወር ለመምህራንና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ተገቢ ዕገዛ የሚያደርግ ባለሙያ ነው፡፡

ተዘዋዋሪ መምህር የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል/ታከናውናለች

- በትምህርት ቤት ደረጃ ልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ስትራቴጂን ለመተግበር የትምህርት ቤቱ አመራር ዕቅድ ሲያወጣና በጀት ሲመድብ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎችም ትኩረት እንዲሰጣቸው ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ ይሰጣል/ትሰጣለች፤
- የመደበኛው ክፍል መምህራን በክፍላቸው ውስጥ የሚማሩትን የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ፍላጎቶችን ለማርካት ይችሉ ዘንድ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን (ለምሳሌ በትብብር መማር፤ የአቻ መማማር፤ ወዘተ ቡድን ምስረታ (በችሎታ ላይ፤ በመቀላቀል፤ በፍላጎት ወዘተ) እንዲጠቀሙ ስልጠናና ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል/ትሰጣለች፤
- መምህራን የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎችን  የነፍስ ወከፍ የትምህርት ቅስሞሽ ችሎታ እንዲመዝኑና አካባቢያዊ እንቅፋቶችን እንዲለዩ ተዘዋዋሪ መምህራን ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት ተማሪዎቹን ለመርዳት የታዩትን እንቅፋቶች ለማስወገድ እንዲያቅዱ ይረዳቸዋል/ትረዳቸዋለች፤
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ክፍል ውስጥ በመግባት የክፍል መምህሩን ይረዳሉ፤ ከዚህም በተጨማሪ፤ ከፍተኛ የመማር ችግር ያጋጠመውን ተማሪ ወይም ተማሪዎች ወደ ድጋፍ መስጫ ማዕከል በመውሰድ ተጨማሪ ድጋፍ ይሰጣል/ትሰጣለች፤
- የነፍስ-ወከፍ የትምህርት መርሀ ግብር ከሚያወጣው ቡድን ጋር በቅርበትና በትብብር ይሰራል፤እና
- በድጋፍ መስጫ ማዕከሉ አቅራቢያ ከሚሰሩ የመሰረተ-ማህበረሰብ ተሃድሶ (community based rehabilitation) አገልግሎት ሰጪዎች ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

## 10.7. ወላጆች

- ከትምህርት ቤቱና ከመምህራን ጋር በቅርበት በመስራት ስለልጃቸው ባህርይ፤ ጥንካሬና ችሎታ መረጃ ይሰጣሉ፤
- ለልጃቸው በቤት ውስጥ ማህበራዊ፤ አካላዊ፤ ስነልቦናዊና በትምህርቱ ዙሪያ እና ወደ ትምህርት ቤት ሲንዝ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋሉ፤
- ለሚኖሩበት ማህበረሰብ የልጃቸውን ጠንካራ ጎኖችና የተለያዩ ችሎታዎች (talents) ይገልፃሉ (ያስተዋውቃሉ)፤ ለምሳሌ የልጁን የፈጠራ ችሎታ፤ በአርት ፤በስፖርት ወዘተ ያለውን ችሎታ፤እና
- በነፍስ-ወከፍ የትምህርት መርሀ ግብር ቡድን ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ።

# ዋቢዎች (References)


1. American Psychiatric Association (2014).Diagnostic and Statistical Manual for Mental Diaorders (4th Ed.).Washington DC, Author.
2. Argote, L. and Ingram, P. (2000). Knowledge transfer: A basic for competitive advantages.Decision process, 82 (1), 150-169. doi 10.1006 obhd 2000. 2893
3. Committee on Educational Interventions for Children with Autism.National Reseach Counsel(2001).Educating Children With Autism Loard,Caterine and James P.McGee, Eds. National Academy Press : Washington ,DC. Available online at http://www.nap.edu/catalog.php?record_id=10017#toc
4. Ministry of Education, Special Programs Branch (2000). Teaching Students with Autism: A Resource Guide for Schools. Rhonda Garside, Autism Society of British Columbia.
5. Missouri Autism Guidelines Initiative (2012). Autism Spectrum Disorders: Guide to Evidence based interventions. Available online at http://www.nap.edu/catalog.php?record_id=10017#toc http://www.autismguidelines.dmh.mo.gov/documents/Intervention Summary. Pdf
6. MoE (2012).Guideline for curriculum differentiation and individual educational program. Addis Ababa: Federal Ministry of Education (2012). Special needs/inclusive education strategy. The Federal Democratic, Republic of Ethiopia, Ministry of Education, Addis Ababa.
7. National Autism Center's (2009).Evidence- Based Practice and Autism in the Schools: A Guide to Providing Appropriate Interventions to Students with Autism Spectrum Disorders. Retrived from http://www.nationalautismcenter.org/ pdf/NAC% 20Ed%20Manual _FINAL. Pdf
8. Province of Nova Scotia (2012). Developing and implementing programming for Students with Autism Spectrum Disorder. Nova Scotia, Department of Education.
9. Saskatchewan Education Special Education Unit (1999). Teaching Students with Autism: A Guide for Educators.
10. Steege,M.W. and Watson,T.S(2009).Conducting school –based functional behavioral assessments: a practioner's guide(second Editon).New York: The Guild Ford Press.

11. Verginia Deparment of Education Office of Special Education and students Service (2011).
12. Models of Best Practic In the education of Students With Autism Spectrum Disorders.Available online a http://www.doe.virginia.gov/special_ed/ disabilities / autism technical_asst_documents/autism_models_of_best_practice. Pdf Virginia Department of Education Office of Special Education and students Service (2010).
13. Guidelines for educating students with Autism Spectrum Disorders. Available online athttp://www.doe.virginia.gov/ special_ed/disabilities/ autism/technical_asst_ documents/autism_guidelines. Pdf
14. Tirussew Teferra (2000). Human Disabilities: developmental, educational, and psychosocial implications. Addis Ababa University, Addis Ababa University Printing Press.

## አባሪ 1: ለወላጆች የሚቀርብ ቃለ-መጠይቅ ፎርም /ቅጽ/

**1.የተማሪ ግለሰባዊ መረጃ (personal information) :-**

1.1. የተማሪው/ዋ/ ስም..............................................................

1.2. ፆታ....................................................................

1.3. ዕድሜ ..................................................................

1.4. የክፍል ደረጃ:-..........................................................

1.5. የትምህርት ቤቱ ስም......................................................

1.6. የትምህርት ቤቱ የሚገኝበት አድራሻ ........................................

1.7. ተግባቦትና ቋንቋ (communication and language) ችግሮች ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎን" ከሆነ ሁኔታው ይገለጽ:: --------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

1.8. የማህበራዊ ግንኙነት ችግሮች ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ ሁኔታው ይገለጽ::

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

1.9. ሥነ-ባህሪይ ወይም ስሜት ዕድገት ችግሮች ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ ሁኔታው ይገለጽ:: -----------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------

1.10. ከዓለም ሁኔታ ጋር በመጣጣም የራስን ህይወት መምራት (adaptive problem) ችግሮችሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ ሁኔታው ይገለጽ -----------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

1.11. የአዕምሮ ዕድገት (cognitive development) ችግሮች ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ ሁኔታው ይገለጽ:: -----------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

1.12. የአካል እንቅስቃሴ ብቃት ችግሮች ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ ሁኔታው ይገለጽ:: -----------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

1.13. በተማሪው/ዋ/ ሌላ የጤና ችግር ነበር ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ ሁኔታው ይገለጽ:: -----------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------

## አባሪ 2: ለመምህራን የሚቀርብ ቃለ-መጠይቅ ፎርም /ቅጽ/

**1.የተማሪው/ዋ/ ግለሰባዊ መረጃ**

1.1 የተማሪው/ዋ/ ስም..........................

1.2. ዕድሜ -------------------------------------------

1.3. የተማሪው/ዋ/ የክፍል ደረጃ --------------------

1.4. የትምህርት ቤት ስም -----------------------------

1.5. የትምህርት ቤቱ አድራሻ-------------------------

2. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ወቅት ተግባቦትና ቋንቋ (communication and language) ችግር ሁኔታን በተመለከተ

2.1.ትዕዛዝ (instruction) የመቀበል ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ:: --------------- -------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

2.2. ስማቸው ሲጠራ የመሮጥ ወይም የመሸሽ ችግር/ ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

2.3. የጊዜና የተግባር ሠሌዳ ላይ በማተኮር (attention) መረዳት ያለመቻል ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ:

------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

2.4. በሰውነት እንቅስቃሴ ቋንቋ (body language) የመረዳት ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

2.5. በማህበረሰቡ ተቀባይነት የሌለው ሰዎችን የመጠጋት ወይም የመቀራረብ ችግር አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

2.6. የመደጋገም (echolalia) ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

2.7. የማህበረሰቡን ባህልና ወግ በመከተል የመግባባት ችግር (pragmatism) ችግር/ ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::-

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**3. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ወቅት የማህበራዊ ግንኙነት (social interaction) ችግር ሁኔታ በተመለከተ**

3.1. ከሌሎቹ ጋር ለመጫወት ያለመፈለግ ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::---------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

3.2. ሌሎች ሲያዝኑ/ሲከፉ የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የመሣቅ ወይም ስሜት አልባ የመሆን ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------- --

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

3.3. የሌሎች ሰዎች ስሜት መለዋወጥ ወይም አቀራረብ ሁሉ ሊጎዳና ሊያስከፉ እንደመጡ አድርጎ የማሰብ ችግር ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

3.4. የሌሎችን ሰዎች ድርጊትና ባህሪይ የማስተካከልና የመተቸት ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

3.5. ከአንድ ሰው ያለመለየት ወይም የመጥላት ፍላጎት፣ ችግር ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

3.6. የሌሎችን የግብዣ ወይም የደስታ ሥነሥርዓት የመቃወም ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

3.7. ሁሉንም ነገር በማሸነፍ በቁጥጥር ሥር የማዋል ፍላጎት ችግር/ ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

3.8. የሌሎች ሰዎችን የመውደድ ወይም የማቅረብ (affection) ፣ የመቃወም ወይም ያለቦታው የመፈልግ (seeking inappropriately) ችግር /ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

---------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**4. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ወቅት የሥነ-ባህሪይ እና ስሜታዊ ዕድገት ችግሮች (Behavioral and Emotional problems) ሁኔታ በተመለከተ**

4.1. የጠብ አጫሪነት ችግር (Aggressive Behavior Problem) ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

4.2. ቅጽበታዊ ቁጣ (Tantrums) ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) መልስዎ “አዎ” ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**5. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ወቅት የአዕምሮ ዕድገት (cognitive development) ችግር ሁኔታ በተመለከተ**

5.1. የአእምሮ ዕድገት (cognitive development) ችግር ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ “አዎ” ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**6. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ወቅት በመማር-ማስተማር ሂደት ወቅት የሚፈጠሩ ችግሮች ሁኔታ በተመለከተ**

6.1. ወደ ትምህርት ቤት ያለመግባት ፍላጎት ችግር/ ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ “አዎ” ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

6.2. ከትህርት ቤት የመሸሻ (Running away) ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ “አዎ” ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

6.3. በክፍል ውስጥ በአንድ ነገር ላይ ትኩረት የማድረግ ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ “አዎ” ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

6.4. ተረጋግቶ በመቀመጥ ትምህርታቸውን ለመከታተል ተቃውሞ/ ችግር/ ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ “አዎ” ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

6.5. የቤት ሥራና ሌሎች የተሰጡ ተግባራን ላለመስራት የመቃወም ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ “አዎ” ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

6.6. አንድ ነገርን ሳያቋርጥ በትኩረት መሥራት ወይም መከታተል (perseverates) ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) መልስዎ “አዎ” ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

6.7. በአዋቂዎች ላይ ጥገኛ የመሆን ችግር (Dependency on Adults)አለ ?

ሀ) አዎ ለ) የለም

መልስዎ “አዎ” ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

6.8. ከአንድ ተግባር ወደ ሌላ ተግባር ሽግግርን መቃወም (Problems Related with Transition from Activity to Activity) ችግር ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ “አዎ” ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**7. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ወቅት ተገቢ ሥነ-ፆታዊና ተያያዥ ጉዳዮች ዕድገት (problems in sexuality) ችግር ሁኔታ በተመለከተ**

7.1. ተገቢ የሥነ-ፆታዊና ተያያዥ ጉዳዮች ዕድገት (problems in sexuality) ችግር ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ “እዎን” ከሆነ የችግር ሁኔታውና ምክንያት ይገለጽ::

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**8. የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ወቅት ከዓለም ሁኔታ ጋር በመጣጣም የራስን ህይወት መምራት (Developing Adaptive/Coping skills) ችግር ሁኔታ በተመለከተ**

8.1.ራስን በራስ የመመምራት (self-direction and management) ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

8.2. ነገሮችን በደረጃ (label) በተመሳሳይ፣ በመጠን፣ ወዘተ፣ የመለየት ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

8.3. ራስን የመንከባከብና የመጠበቅ ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

8.4. የመዝናኛና የጊዜ ማሳለፊያ ዘዴዎችን የመጠቀም ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

8.5. በማህበረሰብ (community) ውስጥ ተሣትፎ ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**9. በኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች አያያዝ ወቅት የአካል እንቅስቃሴ ብቃት ችግር ሁኔታ በተመለከተ**

9.1. የአካል እንቅስቃሴ ብቃት ችግር/ሁኔታ አለ? ሀ) አዎ ለ) የለም መልስዎ "አዎ" ከሆነ የችግሩ ሁኔታና ምክንያቱ ይገለጽ::

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## አባሪ 3: የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ምሳሌ

ለነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር አሠራር ለሁሉም ሁኔታዎች የሚያገለግልና ደረጃውን የጠበቀ መመሪያ ባይኖርም ከዚህ በታች በምሳሌነት የተቀመጠው የነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሃ ግብር ቅፅ ጠቃሚ መረጃ እንደሚሰጥ ይታመናል:: ቅፁ የነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሃ ግብር ሂደት ምን ዓይነት መረጃዎችን ማካተት እንዳለበት አቅጣጫ ይሰጣል፡ ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ትምህርት ቤትና የነፍስ ወከፍ ትምህርት መርሃ ግብር ቡድን የራሱን ቅጽ ሊያዘጋጅ የሚችል መሆኑ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

### 1. ግለ ታሪክ መረጃ

ተየማሪዋ/ው ስም፡- --------------------- አድራሻ:- ---------------------

የተወለደ/ች/በት ቀን፡- -------------------

ወላጅ/ አሳዳጊ :---------------------- ስልክ ቁጥር፡---------------------

አድራሻ፡- ----------------------

የትምህርት ቤቱ ስም፡- ---------------------

- ይህ ሰነድ የተዘጋጀበት ቀን :- -----------
- ይህ ሰነድ የተሸሻለበት ቀናት:- -----------

የመምህሯ/ሩ ስም፡- ---------------------

### 2. ግቦች፣ የሚሰጡ የድጋፍ አይነቶች እና ምዘና

ብቃት (competence)

መገለፅ ያለበት የኦቲዝም ችግር ያለባቸው ተማሪዎች

- የብቃት ወይም የክሂሎት ደረጃ
- በትምህርት ቅስሞሽ ወቅት የሚታዩ ጠንካራ ጎኖች
- መማሪያ አማራጭ መንገዶች
- ማህበራዊ ክሂሎት
- የሚያስደስቱ/ቷ/ትና የሚያዝና/ኗ/ኑት ነገሮች ይሆናሉ፡፡

**በትምህርት ቤት የተማሪዋ/ው ሁኔታና የመማር ችግሮች**

**መግለጫ**

*መገለፅ ያለበት*

- የኦቲዝም ችግር ያለያለበት ተማሪ/ዋ በአሁን ጊዜ በትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ውጪ እንዴት በመሥራት ላይ እንዳለች/እናደለ በትምህርት ቅስሞሽ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ናቸው።

**የረጅም ጊዜ ግቦችና ይዘቶች**

*መገለፅ ያለበት*

የኦቲዝም ችግር ያለባት/ለበት ተማሪ ውጤት እንድታስመዘግብባቸው/እንዲያስመዘግባቸው በነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብር ቡድን የተጣሉ የረጅም ጊዘ ግቦች የትኞቹ እንደሆኑ ይዘረዝራል፡፡

ግቦቹም

- የተማሪዎቹን ፍላጎቶች መሠረት ያደረጉ መሆን አለባቸው፣
- በተማሪው ጠንካራ ጎኞች ላይ የተገነቡ መሆን ይኖርባቸዋል፣
- የሚለኩና
- የሚተገበሩ መሆን አለባቸው::

**ማካተት ያለባቸውም**

- የተግባቦትና ቋንቋ (communication and language) ሁኔታ
- የማህበራዊ ግንኙነት(social interaction) ሁኔታ
- የሥነ-ባህሪይ እና ስሜታዊ ዕድገት (Behavioral and Emotional development) ሁኔታ
- የአዕምሮ ዕድገት (cognitive development) ሁኔታ
- የትምህርት ቅስሞሽ ክህሎት ሁኔታ
- ተገቢ ሥነ-ያታዊና ተያያዥ ጉዳዮች ዕድገት ሁኔታ
- ከዓለም ሁኔታ ጋር በመጣጣም የራስን ህይወት የመምራት (Developing Adaptive/Coping skills) ሁኔታ
- የአካል እንቅስቃሴ ብቃት ሁኔታ
- ሌላም ከላይ ያልተጠቀሰ ጉዳይ ካለ ይጠቀሳል::

ለእያንዳንዱ ግብ ቁጥር መስጠት ይቻላል: :በተለይም ተማሪው የሽግግር ወቅት ላይ ሲደርስ የረጅም ጊዜ ግቦች መጣል አስፈላጊ ነው፡፡ ግቦቹን መጣል ያለባቸው በጥልቅ መልኩ ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ግብ ይቀመጣል፡፡

**የአጭር ጊዜ ግቦችና ይዘታቸው፣**

ከ1 እስከ 6 ወራት ወይም ከዚህ ለሚያጥር ጊዜ የሚነደፉና የአጭር ጊዜ ውጤቶችን ዒላማ ያደረጉ ግቦች የአጭር ጊዜ ግቦች ናቸው:: የሚያካትቱትም፣ተማሪዋ/ው ውጤት እንድታስመዘግባባቸው/ እንዲያስመዘግባቸው በነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብ ቡድን የተጣሉ የአጭር ጊዘ ግቦች ምን ምን እንደሆኑ ነው፡፡

ግቦቹም

- የረጅም ጊዜ ግቦችን መሠረት ያደረጉና የተጣጣሙ መሆን አለባቸው፣
- ተማሪዋ/ው ፍላጎቶች ላይ መመስረት አለባቸው፣
- የሚለኩ መሆን አለባቸው፣
- ሊተገበሩ የሚችሉ መሆን አለባቸው፣
- በአጭር ጊዜ ውጤት የሚመዘገብባቸው መሆን አለባቸው (ከ1-6 ወራት)::
- የእነሱም ሂደት ከጊዜና ግብ አኳያ የሚለካ ሆኖ መዘጋጀት አለበት፣
- እያንዳንዱ የረጅም ጊዜ ግብ ቢያንስ አንድ የአጭር ጊዜ ግብ ይኖረዋል፣
- የአጭር ጊዜ ግቦች ቁጥሮች የረጅም ጊዜ ግቦች ቁጥሮች ነፀብራቅ መሆን አለባቸው፡፡

**የነፍስ ወከፍ የትምህርት መርሃ ግብርን የመተግበር/የማስተማር ዘዴዎች**

የማስተማር ዘዴዎች የረጅማና የአጭር ጊዜ ግቦች ውስጥ በጥንቃቄ ተዘጋጅተው መካተት አለባቸው፡፡ ይህም ተማሪዎቹን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ለመወሰን ያስችላል፡፡ ዓላማውም፣ተማሪዎቹን ለማስተማር የሚያስፈልጉ ስትራቴጂዎችን/ ዘዴዎችንና፣ ትምህርቱን በማስማማት ለማስተማር የተዘጋጀውን እቅድ መግለፅ ይሆናል፡፡

**የቁሳቁሶች አቅርቦት**

ሊገለፅ የሚገባው፣

- አስፈላጊ የሆኑ/ምቹ/ተስማሚ የማስተማሪያ ቁስቁሶችንና፣
- በተጨማሪነት የሚያስፈልጉ የማሰተማሪያ ቁሰቁሶችና አገልግሎቶችን ነው፡፡

**አደረጃጃትና የትምህርት ቅስሞሽ አካባቢ**

መግለፅ የሚገባው፡-

- የተቃዱ፣ ምቹ የአደረጃጃት ሁኔታዎችና፣
- የትምህርት ቅስሞሽ አካባቢን ምቹ ለማድረግየተዘጋጀ ነገር ካለ ነው፡፡

**በት/ቤትና ከት/ቤት ውጪ የሚሰጥ ድጋፍ**

እዚህ የሚካተተው

- ተማሪዋ/ው የምታገኛቸው/ የሚያገኛቸው የአገልግሎት አይነቶች፣
- ለምን ያህል ጊዜ አገልግሎት እንደምታገኝ/ እንደሚያገኝ ለምሳሌ በሳምንት ሁለት ጊዜ. በየቀኑ…ወዘተ፣
- ይህ ድጋፍ የሚሰጠው ከየት እንደሆነና፣
- ሰጭው ክፍል/አካል/ ማን እንደሆነ ይገለፃል፡፡

**የምዘና መርሆዎች**

ምዘና ተማሪዋ/ው በምታስመዘግበው/በሚያስመዘግበው ውጤቶችና በትምህርት ቅስሞሽ ሂደቶች ላይ እንዲያተኩር መደረግ አለበት::

እዚህ መገለፅ ያለበት፡-

☞ የተማሪዋ/ው መሻሻል እንዴት እንደተገመገመ /እንዴት እንደተመዘነ
☞ ግምገማው/ምዘናው መቼ እንደሚካሄድና እነደተካሄደ

☞ ማን እንደገመገመውና ተጨማሪ የማሻሻል ስራ ቢያስፈልግ ይዘቱ ምን መሆን እንዳለበት ይገለፃል፡፡

የሚቀጥለው የማሻሻያ ቀን

የቡድኑ አባላት ፊርማ

1) ርዕስ መምህር፣---------------------------
2) የክፍል መምህር፣---------------------------
3) የልዩ ትምህርት መምህር፣-----------------------
4) ጋይዳንስ ካውንስለር፣--------------------------
5) ተዘዋወሪ መምህር፣---------------------------
6) ወላጅ/ አሳዳጊ ፣--------------------------
7) ተማሪዋ/ው፣ ---------------------------
8) ሌሎች፣---------------------------